ዳል፤ ይወለዳል፤ ይሞታል፡ ተብሎ፡ ተናግሯል።

በአሕዛብስ፡ ስለአራት፡ ነገር፡ እንደምነው፡ ቢሉ፤ አሕዛብ፡ አምላክ፡ ሕዝብ፡ ነው፡ እንጂ፡ አምላክ፡ አሕዛብ፡ አይደለም፡ ይላሉ፤ ግድ፡ አምላክ፡ አሕዛብ፡ ወሕዝብ፡ እንደሆነ፡ ተናግሮባቸዋልና፤ ሁለተኛ፡ በደብያት፡ እንዲጠፉ፡ ተናግሮባቸዋል፤ በፍዳ፡ ማለቱ ነው፤ ሦስተኛ፡ አፍርሆ፡ ነው፤ እስራኤል በአሕዛብ፡ መከራ፡ ሲያጸናባቸው፡ አይተው፡ ሕግ፡ ባልተሠራላቸው፡ በአሕዛብ፡ እንዲህ፡ መከራ፡ ያጸናባቸው፡ በደብረ፡ ሲና፡ የተሠራልንን፡ ሕግ፡ ብናፈርስ፡ መከራውን፡ እንዴት፡ ያጸናብን፡ ይሆን፡ ብለው፡ ይፈራሉና።

አራተኛ፡ ትእምርት፡- (ትምህርት) ነቢዩ፡ ሕዝቡም፡ አሕዛቡም፡ ይጠፋሉ፡ ብሎ፡ ይናገራል፤ ኋላ፡ እስራኤል፡ አሕዛብ፡ ሲጠፉ፡ አይተው፡ ያ፡ ነቢይ፡ የተናገረው፡ ነገር፡ አልቀረም፤ እኒያ፡ አሕዛብ፡ ጠፉ፤ እኛም፡እንጠፋ፡ይሆናል፡ ብለው፡ ምልክት፡ ያደርጓቸዋልና፡ እንዲህ፡ አለ፤ ይህስ፡ አይደለም፤ አፍርሆና፡ ትእምርትስ፡ (ትምህርትስ) አንድ፡ ወገን፡ ናቸው፡ ይጐራበታሉ ብሎ፡ አራተኛ፡ በነቢይ፡ በካህን፡ ሳያናግር፡ እንዳያጠፋቸው፡ ተናግሮባቸዋል።

ስረይነ፡ ሰብአ፡ ወኢያህየውነ፡ ወኮነ ጽድቅነ፡ ከመ፡ ጸርቀ፡ ትክቶ፡ ፈወስናሃ ለባቢሎን፡ ወኢተፈወሰት፡ እንዲል፤ ይኸም፡ ተጽፎ፡ ሲነበብ፡ ሲተረጐም፡ ከነቢያት፡ እስከ፡ ሐዋርያት፡ ደረሰ፤ ሐዋርያትም፡ ለቀሌምንጦስ፡ ሰማንያ፡ አንዱን፡ መጽሐፍ፡ ቈጥረው፡ ሲሰጡት፡ ዐሥራ፡ ሁለት፡ ደቂቀ፡ ነቢያት፡ ብለው፡ ቆጥረው፡ ሰጥተውታል፤ ደቂቀ፡ ነቢያት፡ መባላቸው፡ የነቢያት፡ ልጆች፡ ሁነው፡ አይደለም፤ ከነቢያት፡ ወገን፡ ስለተወለዱ፤ አንድም፡ ከነቢያት፡ ስለተማሩ፡ ደቂቀ፡ ነቢያት፡ ተብለዋል፤ አንድም፡ ትንቢታቸው፤ ትምህርታቸው፡ ስለ፡ አጠረ፡ ደቂቅ፡ ነቢያት፡ ተብለዋል።

ይህንንም፡ የሚያስረዳ፡ አሞፅ፡ የኢሳይያስ፡ አባት፡ ነው፤ ኢሳይያስን፡ ከዓበይት፡ ነቢያት፡ አሞጽን፡ ከደቂቅ፡



ነቢያት፡ ጋራ፡ ይቈጥረዋል፤ አንድም፡ በእውነት፡ የነቢያት፡ ልጆች፡ ናቸው፤ ከደቂቅ፡ ነቢያት፡ አንዱ፡ አሞፅ፡ አንሰ፡ ኢኮንኩ፡ ነቢየ፡ ወኢወልደ፡ ነቢይ፡ አለሳ፡ ቢሉ፤ እሱ፡ ባይሆን፡ ሌሎች፡ ናቸው፤ አንድም፡ እሱ፡ ራሱ፡ ትምህርቱን፡ ትንቢቱን፡ እንደ፡ አጥንት፡ እንደ፡ ጅማት፡ ከእናት፡ ከአባቴ፡ አላገኘሁትም፡ ሲል፡ ነው፡ እንጂ፡ የነቢይ፡ ልጅ፡ ነው፤ ትውልዱም፡ ከነገደ፡ ኤፍሬም፡ ነው፤

አሌ፡ ሎ፡ ኤፍሬም፡ ሥጋየ፡ ውእቱ፡ በማለቱ፡ ይታወቃል፤ ይኸም፡ ለከንቱ፡ አልተጻፈም፤ እኛ፡ ልንመከርበት፤ እኛ፡ ልንገሠጽበት፡ ነው፤ ወኵሉ፡ ዘተጽሕፈ፡ ለተግሣጽ፡ ዚአነ፡ ተጽሕፈ፡ ከመ፡ በትዕግሥትነ፡ ወበተወክሎተ፡ መጽሐፍ፡ ንርከብ፡ ተስፋነ፡ እንዲል፤ ሮሜ.፲፭-፬፤

እስከዚህ፡ አርእስት፡ ነው፤ ሠለስቱ፡ ምእት፡ ለመጻሕፍት፡ አርእስት፡ ሲሰጡ፡ አርእስት፡ ሰጥተውታል፤ እሱ፡ ግን፡ ነገሩን፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ብሎ፡ ያመጣል።

## - ምዕራፍ ፩ -

፩፤ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኮነ፡ ኀበ፡ ሆሴዕ፡ ወልደ፡ ብኤርም፤

ዘሆሴዕ፡ ያሉ፡ ሠለስቱ፡ ምእት፡ ናቸው፤ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኮነ፡ ያሉ፡ በኋላ፡ የተነሡ፡ ናቸው፤ አንድም፡ ዘሆሴዕ፡ ያሉ፡ በኋላ፡ የተነሡ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኮነ፡ ያሉ፡ ሠለስቱ፡ ምእት፡ ናቸው፤ እሱ፡ ግን፡ ቀዳሜ፡ ቃሉ፡ ብሎ፡ ይጀምራል፤

ዘመጽአ፡ ዘተነግረ፡ ሲል፡ ነው፤ ከብኤርም፡ ልጅ፡ ከሆሴዕ፡ ዘንድ፡ የመጣ፡ የተነገረ፡ የእግዚአብሔር፡ ቃል፡ ይህ፡ ነው፤

በመዋዕለ፡ ያዝያን፡ ወኢዮአታም፡ ወአካዝ፡ ወሕዝቅያስ፡ ነገሥተ፡ ይሁዳ፤

እለ፡ ነግሡ፡ በይሁዳ፡ እለ፡ ነግሡ፡ ለይሁዳ፡ ነገሥታተ፡ ይሁዳ፡ ይላል፤

በይሁዳ፡ በነገሡ፡ በነዚህ፡ ዘመን፡ የተነገረ፡ የእግዚአብሔር፡ ነገር፡ ይህ፡ ነው፤ ስለምን፡ እነዚህን፡ አነሣቸው፡ ቢሉ፡ መነሣቱ፡ በሊህ፡ ዘመን፡ ነውና፤ አንድም፡ በነዚህ፡ ዘመን፡ ብመክራቸው፡ ባስተምራቸው፡ አንሰማም፡ ብለው፡ ተማረኩ፡ ለማለት፤

www.ethiopianorthodox.org

ወበመዋዕለ፡ ኢዮርብአም፡ ወልደ፡ ዮአስ፡ ንጉሠ፡ እስራኤል፤

በእስራኤል፡ በነገሥ፡ በዮአስ፡ ልጅ፡ በኢዮርብአም፡ ዘመን፡ የመጣ፡ የተነገረ፡ የእግዚአብሔር፡ ቃል፡ ይህ፡ ነው፤ ይህ፡ ካልዕ፡ ኢዮርብአም፡ ነው፤

፪፤ ቀዳሜ፡ ቃሉ፡ ለእግዚአብሔር፡ ዘኮነ፡ ኀበ፡ ሆሴዕ፤

ቀዳማዊ፡ ሲል፡ ነው፤ ወእንተሰ፡ ጥበብ፡ እምላዕሉ፡ ቀዳሚሃ፡ ንጽሕት፡ ይእቲ፤ ያዕ.፫፡፲፯፡ ወለውእቱ፡ መቅድመ፡ ቃል፡ ይባርክዎ፡ ቀዳሚሁ፡ ቃል፡እንዲል፤ ዮሐ.፩፥፩፤

ቀዳሜ፡ ቃሉ፡ ብሎ፡ እሱ ነገሩን፡ ይጀምራል፤ እግዚአብሔር፡ መጀመሪያ፡ ከሆሴዕ፡ ዘንድ፡ የተናገረው፡ ነገር፡ ይህ፡ ነው፤ አንድም፡ ኋላ፡ ከተናገረው፡ የሚቀድም፡ መጀመሪያ፡ የተናገረው፡ ይህ፡ ነው፤

ወይቤሎ፡ እግዚአብሔር፡ ለሆሴዕ፡ ሑር፡ አውስብ፡ ብእሲተ፡ ዘማ፡ ወአዋልደ፡ ዘማ፤

ይቤለኒ፡ ሲል፡ ነው፤ ዋዌውን፡ ጥሦ፡ ይጽሕፍ፡ አቡልዲስ፡ ለፍቁሩ፡ ወለእግዚኡ፡ በርደጊስ፡ እንዲል፤ ሂደህ፡ የሴሰኛ፡ ልጅ፡ ሴሰኛ፡ አግባ፡ አለኝ፤ ነቢዩ፡ እግዚአብሔር፡ ምነው፡ የሴሰኛ፡ ልጅ፡ አገባህ፡ ቢሉት፤ ለተግሣጽ፡ ለዘለፋ፤ እናንተ፡ ሁሉ፡ ኃጢአት፡ ብትሠሩ፤ ጣዖት፡ ብታመልኩ፡ ትስለቻላችሁ፡ ለማለት፤ አንድም፡ ሰስና፡ የታከተች፡ሰስና፡ ያልታከተች፡ አግባ፡ አለኝ፡ ነቢዩ፡ እግዚአብሔር፤ ምነው፡ ሰስና፡ ያልታከተች፡ ሰስና፡ የታከተች፡ አገባህ፡ ቢሉት፤ እናንተስ፡ ኃጢአት፡ ሠርታችሁ፤ ጣዖት፡ አምልካችሁ፡ ብትመለሱ፡ ይቅር፡ አይላችሁምን፡ ለማለት፤ በእውነት፡ አግብቷል፡ ቢሉ፡ አዎን፡ አግብቷል፤ ጌታ፡ አግባ፡ ቢለው፡ እዳ፡ ይሆንበታልን፤ አንድም፡ ለምሳሌ፡ ነው፡ እንጂ፡ አላገባም፤ ዘማ፡ አዋልደ፡ ዘማ፡ ማለቱ፡ ግን፡ ከነፈርግብ፡ ገበዋተ፡ ድንግል፡ እንደ፡ ማለት፡ ነው፡ እንጂ፡ አንዲት፡ ናት፤ አንድም፡ ሁለት፡ ናቸው፤ በአንዲቱ፡ ዐሥሩን፡ ነገድ፤ በአንዲቱ፡ ሁለቱን፡ ነገድ፡ ለመዝለፍ፤

እስመ፡ ዘምዎ፡ ትዜሙ፡ ምድር፡ እምድኅረ፡ እግዚአብሔር፤

ምድር፡ ከእግዚአብሔር፡ ተለይታ፡ የማይገባ፡ ሥራ፡ ትሠራለችና፡ የሰዎችን፡ ለምድር፡



ሰጥቶ፡ ተናገረ፡ ዝሙት፡ ብቻ፡ የወንድና፡ የሴት፡ አይደለም፤ እግዚአብሔር፡ ያላዘዘውን፡ ሥራ፡ መሥራት፡ ዝሙት፡ ነው፤ አንድም፡ እምድኅረ፡ ኃደገት፡ እግዚአብሔርሃ፡ በሕግ፤ በአምልኮት፡ እግዚአብሔርን፡ ከተወች፡ በኋላ፤ አንድም፡ እምድኅረ፡ አምለከት፡ እግዚአብሔርሃ፡ እግዚአብሔርን፡ ካመለከች፡ በኋላ፤ አንድም፡ ብእሲተ፡ ዘማ፡ ታላቂቱ፤ ወአዋልደ፡ ዘማ፡ ታናሽቱን፡ ከታላቂቱ፡ ጋራ፡ ጨምሮ፡ አዋልድ፡ ብሎ፡ አበዛ፤

፫፤ ወሖረ፡ ወአውሰበ፡ ጎሜርሃ፡ ወለተ፡ ቤዴልይም፤

ሖርኩ፡ ወአውሰብኩ፡ ሲል፡ ነው፤ ሄጄ፡ የቤዴልይምን፡ ልጅ፡ ጎሜርን፡ አገባሁ፤

ወፀንሰት፡ ወወለደት፡ ሎቱ፡ ወልደ፤

ሊተ፡ ሲል፡ ነው፤ ፀነሰች፤ ወንድ፡ ልጅ፡ ወለደችልኝ፤

፬፤ ወይቤሎ፡ እግዚአብሔር፡ ሰምዮ፡ ስሞ፡ ኢይዝራኤል፤

ስሙን፡ ኢይዝራኤል፡ በለው፡ አለኝ፤ ነቢዩ፡ እግዚአብሔር፡ አንተ፡ እስራኤላዊ፤ ልጅህ፡ እስራኤላዊ፤ ምነው፡ ልጅህን፡ ኢይዝራኤል፡ አልኸው፡ ቢሉት፤ እናንተ፡ ሁሉ፡ ሕዝበ፡ እግዚአብሔር፡ ትባሉ፡ የነበረ፡ ኃጢአት፡ ሠርታችሁ፤ ጣዖት፡ አምልካችሁ፡ ኢእስራኤል፡ ተብላችሁ፡ የለም፡ ለማለት፤

እስመ፡ ዓዲ፡ ኅዳጠ፡ እትቤቀል፡ ደሞ፡ ለኢይዝራኤል፤

ገና፡ ተበቅዬ፡ የእስራኤልን፡ ደማቸውን፡ አፈስሳለሁና፤

ወእስዕር፡ መንግሥተ፡ እምቤተ፡ እስራኤል፤

ከእስራኤልም፡ መንግሥትን፡ አጠፋለሁ፡ ብሏልና፤ አንድም፡ ስሙን፡በኢይዝራኤላዊ፡ በናቡቴ፡ ቦታ፡ ስም፡ ጥራው፡ አለኝ፤ ደሞ፡ ለናቡቴ፤ ደሞ፡ ለኢይዝራኤል፤ ደሞ፡ ለናቡቴ፡ ኢይዝራኤላዊ፡ ይላል፡ አብነት፤ የናቡቴን፡ ደም፡ ተበቅዬ፡ ኢእስራኤል፡ በተባሉበት፡ ቦታ፡ አጠፋቸዋለሁ፤

ወእሥዕር፡ መንግሥተ፡ እምቤተ፡ አክዓብ፡ ይላል፤ ከአክዓብ፡ ወገን፡ መንግሥትን፡ አጠፋለሁ፤

፭፤ ወይከውን፡ ይእተ፡ አሚረ፡ እቀጠቅጥ፡ ቀስተ፡ እስራኤል፡ በቈላተ፡ ኢይዝራኤል፤

ያንጊዜ፡ እንዲህ፡ ይሆናል፤ ይከውን፡ ያለውን፡ እቀጠቅጥ፡ ብሎ፡ አመጣው፤ ኢእስራኤል፡ በተባሉበት፡ ቦታ፡ የእስራኤልን፡ ሥልጣን፡ አጠፋለሁ፤ አንድም፡

www.ethiopianorthodox.org

ኢይዝራኤል፡ ቢል፡ በኢይዝራ ኤላዊ፡ በናቡቴ፡ ቦታ፤ አንድም፡ አክዓብ፡ በሞተበት፡ አውራጃ፡ የእስራኤልን፡ ሥልጣን፡ አጠፋለሁ፤

፮፤ ወፀንሰት፡ ካዕበ፡ ወወለደት፡ ወለተ፤

ዳግመኛ፡ ፀነሰች፡ ሴት፡ ልጅ፡ ወለደች፤

ወይቤሎ፡ እግዚአብሔር፡ ስምያ፡ ስማ፡ ኢሥህልት፤

ይቤለኒ፡ ሲል፡ ነው፤ ስሟን ምሕረት ዘአልባ፡ በላት አለኝ፡ ነቢዩ፡ እግዚአብሔር፤ ምነው፡ ልጅህን፡ ምሕረት፡ ዘአልባ፡ አል ሃት፡ ቢሉት፡ እናንተ፡ ሁሉ፡ ሥሁላን፡ ትባሉ፡ የነበረ፡ ኃጢ አት፡ ሠርታችሁ፤ ጣዖት፡ አም ልካችሁ፡ ኢሥሁላን፡ ተብላችሁ፡ የለምን፡ ለማለት፤

እስመ፡ ኢይደግም፡ እንከ፡ ተሣህሎ ቶሙ፡ ለቤተ፡ እስራኤል፤

የእስራኤልን፡ ወገኖች፡ ዳግመኛ፡ ይቅር፡ አልላቸውምና፤

ዳዕሙ፡ ተናክሮ፡ እትናከሮሙ፤

ተሌልዮ፡ እትሌለዮሙ፡ ተፈልጦ፡ እትፈለጦሙ፡ ሲል፡ ነው፤ ፈጽሜ፡ እለያቸዋለሁ፡ እንጂ፡ ይቅር፡ አልላቸውምና፡ ምሕረት፡ ዘአልባ፡ በላት አለኝ፤

፯፤ ወእሣሃሎሙ፡ ለደቂቀ፡ ይሁዳ፡ ወአድኅኖሙ፡ አነ፡ እግዚአብሔር፡ አምላኮሙ፤

ነገደ፡ ይሁዳን፡ ይቅር፡ እላቸ ዋለሁ፤ ፈጣሪያቸው፡ እኔ፡ እግዚአብሔር፡ አድናቸዋለሁ፤

ወኢያድኅኖሙ በቀስት፡ ወበኲናት፤

የማድናቸውም፡ በሰው፡ ቀስት፡ በሰው፡ ጦር፡ አይደለም፤

ወኢበሠረገላት፡ ወኢበጸባዒት፤

በሰው፡ ሠረገላ፡ በእግረኛ፡ አይደለም፤

ወኢበአፍራስ፤

በፈረስ፤

ወኢበመስተጽዕናን፤

በፈረስ፡ በተቀመጡ፡ ሰዎች፡ አይደለም፤ አሳ፡ በሰይፈ፡ መል አክ፡ ያለበት፡ ነው፤ በመልአክ፡ ሰይፍ፡ ነው እንጂ፤

፰፤ ወአኀደግዋ፡ ጥበ፡ ለኢሥ ህልት፤

ምሕረት፡ ዘአልባን፤ ጡት፡ አስጣልኋት፤ አንድም፡ ፀንሰት፡ የሚል፡ ነውና፤ አንድም፡ ሥላሴ፡ ይቅርታን፡ ነሷት፤

ወፀንሰት፡ ወወለደት፡ ወልደ፤

ፀነሰች፤ ወንድ፡ ልጅ፡ ወለደች፡

፱፤ ወይቤሎ፡ እግዚአብሔር፡ ስምዮ፡ ስሞ፡ ኢሕዝብየ፤

ይቤለኒ፡ ሲል፡ ነው፤ ስሙን፡ ኢሕዝብየ፡ በለው፡ አለኝ፡ ነቢዩ፡



እግዚአብሔር፤ አንተ፡ ሕዝበ፡ እግዚአብሔር፤ ልጅህ፡ ሕዝበ፡ እግዚአብሔር፡ ምነው፡ ልጅ ህን፡ ኢሕዝብየ፡ አልኸው፡ ቢሉት፤ እናንተ፡ ሁሉ፡ ሕዝበ፡ እግዚአብሔር፡ ትባሉ፡ የነበረ፡ ኃጢአት፡ ሠርታችሁ፤ ጣዖት፡ አምልካችሁ፤ ኢሕዝብየ፡ ተብላችሁ፡ የለምን፡ ለማለት፤

እስመ አንትሙ፡ ኢኮንክሙ፡ ሕዝብየ፡ ወአነሂ፡ ኢኮንኩ አምላክክሙ፤

እናንት፡ ወገኖቼ፡ አይደላችሁምና፡ እኔም፡ አምላካችሁ፡ አይደለሁም፤

፲፤ ወይከውን፡ ኍልቆሙ፡ ለደቂቀ፡ እስራኤል፡ ከመ፡ ኆፃ፡ ባሕር፡ ዘኢይሰፈር፡ ወዘኢይትኌለቍ፤

የእስራኤል፡ ልጆች፡ ቍጥራ ቸው፡ እንደማይሰፈር፡ እንደ ማይቈጠር፡ እንደባሕር፡ አሸዋ፡ ይሆናል፡

ወይከውኑ፡ በውእቱ፡ ብሔር፡ በነበ፡ ይቤሎሙ፡ ኢኮንክሙ፡ ሕዝብየ፤

ይበዝኑ፡ ሲል፡ ነው፤ ሕዝበ፡ እግዚአብሔር፡ አይደላችሁም፡ በተባሉበት፡ ቦታ፡ ይበዛሉ፤

እስመ፡ እሙንቱ፡ ውሉደ፡ እግዚአብ ሔር፡ ሕያው፡ ይሰመዩ፤

እኒህ፡ የሕያው፡ እግዚአብሔር፡ ልጆች፡ ይባላሉና፤

፲፩፤ ወእምዝ፡ ይትጋብኡ፡ ደቂቀ፡ ይሁዳ፡ ወደቂቀ፡ እስራኤል፡ ኅቡረ፤

ከዚህ፡ በኋላ፡ ዐሥሩ፡ ነገድ፡ ሁለቱ፡ ነገድ፤ አንድ፡ ሁነው፡ ይሰበሰባሉ፤

ወይሠይሙ፡ ሎሙ፡ አሐደ፡ መልአከ፡ ወየዓርጎሙ፡ እምድር፤

ዘሩባቤልን፡ ያነግሣሉ፤ ከባቢሎን፡ ያወጣቸዋል፤ ይሠየም፡ ሎሙ፡ ቢል፡ ዘሩባቤል፡ ይነግሥላቸዋል፤

እስመ፡ ዓባይ፡ ዕለቱ፡ ለእስራኤል፤

እስራኤል፡ የወጡባት፡ ዕለተ፡ ሚጠት፡ ደግ፡ ናትና፤ አንድም፡ ወይከውን ኍልቆሙ፡ ብለህ፡ መልስ፤ የምእመናን፡ ቍጥራ ቸው፡ እንደማይሰፈር እንደማ ይቈጠር፡ እንደባሕር፡ አሸዋ፡ ይሆናል፤ ሕዝበ፡ እግዚአብ ሔር፡ አይደላችሁም፡ በተባሉ በት፡ ቦታ፡ ይበዛሉ፤ እኒህ፡ የእግዚአብሔር፡ ልጆች፡ ይባ ሉና፤ ከዚህ፡ በኋላ፡ ይሁዳ፡ ዘነፍስ፤ እስራኤል፡ ዘነፍስ፡ አንድ፡ ሁነው፡ በገነት፡ ይሰበ ሰባሉ፤ ወይሠይሙ፡ ሎሙ፡ አሐደ፡ መልአከ፤ ክርስቶስን፡

www.ethiopianorthodox.org

ይሾማሉ፤ እነሱ፡ የሚሾሙት፡ ሆኖ፡ አይደለም፤ በሥጋ፡ መሾሙ፡ ስለነሱ፡ ነውና፤ አንድም፡ ይሠየም፡ ቢል፡ ይሾምላቸዋል፡ በሥጋ፡ ከሲዖል፡ ያወጣቸዋል፤ እስራኤል፡ ዘነፍስ፡ የወጣባት፡ ዕለተ፡ ትንሣኤ፡ ደግ፡ ናትና።

## - ምዕራፍ ፪ -

፩፤ ወበልዎ፡ ለእኁክሙ፡ ሕዝብየ፡ ወለእኅትክሙ፡ ሥህልት፤

ኢሕዝብየ፡ የተባለ፡ ወንድማችሁን፡ ሕዝብየ፡ በሉት፤ ምሕረት፡ ዘአልባ፡ የተባለች፡ እኅታችሁንም፡ ምሕረት፡ ዘባ፡ በሏት፤

፪፤ ተዋቀሥዋ፡ ለእምክሙ፤

ነገሥታቱን፣ ካህናቱን፡ ተከራከሯቸው፣ እምክሙ፡ አለ፣ እናት፡ ልጇን፡ ሠርታ፡ ቀጥታ፡ እንድታኖር፡ እሊህም፡ ሠርተው፡ ቀጥተው፡ ያኖሯቸው፡ ነበርና፤

እስመ፡ ይእቲ፡ ኢኮነት፡ ብእሲትየ፡ አነሂ፡ ኢኮንኩ፡ ምታ፤

ማደሪያዬ፡ አልሆነችምና፡ እኔም፡ አላድርባትም፤

ወናሁ፡ ይእዜ፡ እከሥት፡ ዝሙታ፡ ቅድመ፡ ገጸ፤

የማይገባ፡ ሥራዋን፡ ከፊቷ፡ አጠፋለሁ፤

ወመሐዛኒሃ፡ እማዕከለ፡ አጥባቲሃ፤

ወዳጆቿን፡ ከደረቷ፡ አጠፋለሁ፡ ማለት፡ ጣዖቷን፡ ከአጠገቧ፡ አጠፋለሁ፤

፫፤ ወእቀፍጻ፡ እራቃ፤

ራቁቷን፡ ትሆን፡ ዘንድ፡ ልብሷን፡ እገፋታለሁ፤ ተዋርዶዋን፡ መናገር፡ ነው፤

ወእሬስያ፡ ከመ፡ መዋዕለ፡ ንዕሳ፤

እንደ፡ ሕፃንነቷ፡ ወራት፡ አደርጋታለሁ፡ ማለት፡ በሕፃንነቷ፡ ወራት፡ ራቁቷን፡ ስትሆን፡ አታፍር፡ እንደነበረ፡ ራቁቷን፡ ሁና፡ እንድትማረክ፡ አደርጋታለሁ፤

ወከመ፡ ዕለት፡ ቀዳሚት፡ እንተ፡ ባቲ፡ ተወልደት፤

እንደተወለደችበት፡ ቀን፡ አደርጋታለሁ፡ ማለት፡ ለአንገቷ፡ ድባ፣ ለወገቧ፡ ጨርቅ፡ ይዛ፡ እንዳልተወለደችበት፡ ጊዜ፡ ከገንዘቧ፡ ሁሉ፡ የምታገኘው፡ የለም፤

ወእገብራ፡ ከመ፡ ምድር፤

ምድር፡ እንድትረገጥ፡ በመከራ፡ እንድትረገጥ፡ አደርጋታለሁ፤



አንድም፡ እንደገራህተ ሠሉስ፡ አደርጋታለሁ፤ አንድም፡ እንደ፡ ሰዶም፡ እንደ፡ ገሞራ፡ አደርጋታለሁ፤

ወእሬስያ፡ ከመ፡ በድው፡ ዘአልቦ፡ ማይ፤

ውሀ፡ እንደሌለበት፡ ምድረ፡ በዳ፡ አደርጋታለሁ፤

ውሀ፡ የሌለበት፡ ምድረ፡ በዳ፡ ተክል፡ ልምላሜ፡ እንዳይገኝበት፡ ከተድላ፡ ከደስታ፡ ትለያለች፤

ወእቀትላ፡ በጽምዕ፤

በጽም፡ ተይዛ፡ እንድትጠፋ፡ አደርጋታለሁ፤

፬፤ ወኢይሠሃሎሙ፡ እንከ፡ ለደቂቃ፡ እስመ፡ ትውልደ፡ ዘማ፣ እሙንቱ፤

የዘማውያን፡ ልጆች፡ ናቸውና፡ ልጆቿን፡ ይቅር፡ አልላቸውም፤

፭፤ እስመ፡ ዘመወት፡ እሞሙ፡ ወአስተኀፈረቶሙ፡ ወላዲቶሙ፤

እሞሙ፡ ወላዲቶሙ፡ አንድ፡ ወገን፣ ነገሥታቱ፡ ካህናቱም፡ የማይገባቸውን፡ ሥራ፡ ስለሠሩ፡ አሳፍረዋቸዋልና፤

እስመ፡ ትቤ፡ አሐውር፡ እትልዎሙ፡ ለመሐዛንየ፡ እለ፡ ይሁቡኒ፡ ስቴየ፡ ወመብልዕየ፤

መብሉን፡ መጠጡን፡ የሚሰጡኝ፡ ጣዖታቱን፡ አመልካለሁ፡ ብላለችና፤

ወይኤርዙኒ፡ አልባስየ፡ ወመዋጥህየ፤

መጎናጠፊያውን፡ ቀሚሱን፡ የሚያለብሱኝ፤

ወይሁቡኒ፡ ቅብዕየ፡ ወኵሉ፡ ዘይደሉ፡ ሊተ፡ ያመጽኡ፤

ዘይቱን፡ የሚሰጡኝ፡ ለኔ፡ የሚገባውን፡ ሁሉ፡ የሚያመጡልኝ፡ ጣዖታቱን፡ እከተላለሁ፡ ብላለችና፣ ጣዖት፡ ባመለኩበት፡ ወራት፡ ያገኙትን፡ ሁሉ፡ ጣዖቱ፡ ሰጠን፡ ይላሉና፤

፮፤ በእንተ፡ ዝንቱ፡ ናሁ፡ አነ፡ አሐፅር፡ ፍኖታ፡ በሦክ፡ ወእፌጽም፡ መንገዳ፤

ስለዚህ፡ ነገር፡ ጐዳናዋን፡ በጦር፡ አጥረዋለሁ፡ መንገዷን፡ በጦር እዘጋዋለሁ፤

ወተኃጥዕ፡ ምኅላፈ፤

የምትወጣበት፡ ቀዳዳ፣ የምትኖርበት፡ ሜዳ፡ አሳጣታለሁ፤ አንድም፡ የምትሠወርበት፡ ቅጠል፡ የምትንጠለጠልበት፡ ገደል፤ አንድም፡ የምትይዘው፡ ጋሻ፣ የምትገባበት፡ ዋሻ፡ ታጣለች፤

፯፤ ወትዴግኖሙ፡ ለመሐዛኒሃ፡ ወኢትእኅዞሙ፤

ጣዖታቱን፡ ትከተላቸዋለች፡ አትይዛቸውም፤

www.ethiopianorthodox.org

ተኃሥሦሙ፡ ወኢትረከቦሙ፤

ትሻቸዋለች፡ ሲራዷት፡ አታገ
ኛቸውም፤

ወትብል፡ እንከስ፡ አሐውር፡ ኀበ፡
ምትየ፡ ዘትካት፤

እንግዲህስ፡ ወዲህ፡ ወደቀደ
መው፡ ፈጣሪዬ፡ እመለሳለሁ፡
ትላለች፤

እስመ፡ ይኄይሰኒ፡ ዘቀዲሙ፤

እምይእዜ፡ ዘቀዲሙ፡ ዘይእዜ፡
አንድ፡ ወገን፣ የቀደመው፡ ፈጣ
ሪዬ፡ ይሻለኛልና፤ አንድም፡
እምዘ፡ ቀዲሙ፣ ከቀደመው፡
ጣዖት፣ ዘይእዜ፡ የዛሬው፡
ፈጣሪዬ፡ ይሻለኛልና፤

፰፤ ወይእቲሰ፡ ኢያእመረት፡ ከመ፡
አነ፡ ወሀብክዋ፡ እክለ፡ ወወይነ፡
ወቅብዓ፤

እሷ፡ ግን፡ እህሉን፡ ወይኑን፡
ዘይቱን፡ እኔ፡ እንደ፡ ሰጠ
ኋት፡ አላወቀችም፤

ወአብዛኅኩ፡ ላቲ፡ ወርቀ፡ ወብሩረ፤

ወርቁን፡ ብሩን፡ አበዛሁላት፡፡

ወይእቲሰ፡ ገብረቶ፡ ለበዓል፤

እሷ፡ ግን፡ ስጦታውን፡ ለጣዖት፡
አደረገችው፤ አንድም፡ ገብረቶ፡
በዓለ፣ ወርቁን፡ ብሩን፡ አበዛሁ
ላት፣ ጣዖት፡ አድርጋ፡ ሠራ
ችው፤ አንድም፡ ለበዓል፡ በዓለ፣
ለጣዖቱ በዓል አደረገችው፤

፱፤ በእንተዝ፡ እትመየጥ፡ ወእስ
ተጋብዕ፡ እክልየ፡ ዘበበጊዜሁ፤

ስለዚህ፡ ነገር፡ ወደቸልታ፣ ወደ
ሥዋሬ፣ ወደ፡ ትዕግሥት፡ እመ
ለሳለሁ፣ በየጊዜው፡ የምሰ
ጣት፡ የመከሩን፣ የበልጉን፡
እህል፡ እሰበስባለሁ፡ ማለት፡
እነሣታለሁ፤ በበጊዜሁ፡ አለ፡
በመስከረም፣ በጥቅምት፡ ገብሱ፡
ባቂላው፣ በኅዳር፡ በታኅሣሥ፡
ጤፉ፣ ማሽላው፣ በጥር፣ በየ
ካቲት፡ ስንዴው፣ ሽምብራው፡
ነውና፣

ወወይንየ፡ ዘለለዕለቱ፤

ዕለት፡ ዕለት፡ የሚለቀመውን፡
ወይኑን፡ እነሣታለሁ፣ ዘጠኝ፡
ወር፡ በጋ፡ የሚለቀም፡ ወይን፡
አለና፤

ወእሰልብ፡ አልባሲሃ፡ ወመዋጥኒሃ፡
ከመ ኢትክድን፡ ኃፍረታ፤

ምሥጢሯን፡ እንዳትሠውር፡
ቀሚሷን፡ መጐናጸፊያዋን፡ እገ
ፍፋታለሁ፤

፲፤ ወናሁ፡ ይእዜ፡ እከሥት፡ ኃፍ
ረታ፡ በቅድመ፡ መሐዛኒሃ፤

እነሆ፡ ዛሬ፡ ምሥጢሯን በጣ
ዖቱ፡ ፊት፡ እገልጣለሁ፤

ወአልቦ፡ ዘያድኅና፡ እምእዴየ፤

ከኔ፡ ሥልጣን፡ የሚያድናት፡
የለም፤



፲፩፤ ወእመይጥ፡ ኵሎ፡ በዓላቲሃ፤

በዓለ፡ ሰዊትን፡ በዓለ፡ መጸለትን፤

ወፍሥሐሃ፤

በዓለ፡ ፋሲካን፤

አስሕርቲሃ፤

እሸት ነዶዋን፤

አስርኅቲሃ፤

ሠርቀ ወርኂን፡ እለውጠዋለሁ፤

ወሰንበታቲሃ፤

ያመቱን፡ ቅዳሜ፡ ቆጥሮ፤ አን
ድም፡ እሑድን፡ በትንቢት፡
ጨምሮ፡ ቆጥሮ፡ ሰንበታት፡ ብሎ፡
አበዛ፣ ይህን፡ ሁሉ፡ ወደኀዘን፡
እመልሰዋለሁ፤

ወኵሎ ሕገጋቲሃ፤

ሥርዓት፡ መንግሥትን፡ ሥርዓተ፡
ክህነትን፡ እለውጠዋለሁ፤

፲፪፤ ወአጠፍዕ፡ ወይና፡ ወበለሳ፤

ወይኑን፡ በለሱን፡ አጠፋባ
ታለሁ፤

ወኵሎ፡ ዘትቤ፡ ደነስየ፡ ውእቱ፡ ዘወ
ሀቡኒ፡ መሐዛንየ፤

ወዳጆቼ፡ ጣዖታቱ፡ ሰጡኝ፡ የም
ትለው፡ አስበ፡ ዝሙቷን፡ ሁሉ፡
አጠፋዋለሁ፤ አንድም፡ ጣዖታቱ፡
የሰጡኝ፡ አስበ፡ ተቀንዮየ፡ ነው፡
የምትለውን፡ ሁሉ፡ አጠፋ
ባታለሁ፤

ወእሬስያ፡ በድወ፤

ምድረ፡ በዳ፡ አደርጋታለሁ፤

ወእነብሮ፡ ስምዐ፡ ይኩና፤

ጥፋቷን፡ ምስክር፡ አድርጌ፡
አኖረዋለሁ፤ አንድም፡ ምስ
ክር፡ ይሆንባት፡ ዘንድ፡ ኃጢአ
ቷን፡ አኖረዋለሁ፤ በእንተ፡
ምንት፡ ገብራ፡ ለዛቲ፡ ሀገር፡
ዘከመ፡ ትቤሉ፡ በእከዮሙ ለእለ
ይነብርዋ፡ እንዲሉ፡ አደርጋ
ታለሁ፤

ወይበልዕዋ፡ አራዊተ፡ ገዳም፤

ጅብ፡ ቀበሮ፣

ወአዕዋፈ፡ ሰማይ፤

በሰማይ፡ የሚበሩ፡ አዕዋፍ፣

ወአራዊተ፡ ምድር፤

ውሻ፡ ድመት፡ ያጠፏታል፤
አንድም፡ አራዊተ፡ ገዳም፡ አሕ
ዛብ፣ አዕዋፈ፡ ሰማይ፡ ኃያላኑ፡
አራዊተ፡ምድር፡ሞዓብ፡ አሞን፡
ያጠፏታል፤

፲፫፤ ወእትቤቀላ፡ እምጣነ፡- መዋ
ዕለ፡ በዓሊም፡ ዘሦዓት፡ ሎሙ፤

የሠዋችላቸው፡ ጣዖታቱን፡ ባመ
ለከችበት፡ ዘመን፡ ልክ፡ ተበ
ቅዬ፡ አጠፋታለሁ፤

ወተሠርገወት፡ አዕኑጊሃ፡ ወባዝግናሃ፤

ንፎ፡ መንደልቶዋን፡ ዝርግፏን፡
አጌጠች፤

ወሖረት፡ ወተለወቶሙ፡ ለመሐዛኒሃ፤

ሂዳ፡ ጣዖታቱን፡ ተከተለች፤

www.ethiopianorthodox.org

ወሊተሰ፡ ረስዓተኒ፡ ይቤ፡ እግዚ አብሔር፤

እኔን፡ ግን፡ ዘነጋችኝ፡ አለ፡ እግ ዚአብሔር፤

፲፬፤ በእንተ፡ ዝንቱ፡ ናሁ፡ አነ፡ አንጐግዋ፤

ስለዚህ፡ ነገር፡ እንድትቅበዘ በዝ፡ አደርጋታለሁ፤

ወአሐውራ፡ በድወ፤

ተማርካ፡ በምድረ፡ በዳ፡ እን ድትሄድ፡ አደርጋታለሁ፤

ወአዘነግዕ ልባ፤

አእምሮዋን፡ አሳጣታለሁ፤

፲፭፤ ወእሁብ፡ ጥሪታ፡ ዘእምህየ፤

እሁብ፡ ባቲ፡ ሲል፡ ነው፤ ገን ዘቧን፡ ለአሕዛብ፡ እሰጥባታለሁ፤ አንድም፡ ዘእምህየ፤ በግብፅ፡ ትቀበለው፡ የነበረውን፡ መከራ፡ አመጣባታለሁ፤ አንድም፡ ዘእ ምኔሃ፡ ሲል፡ ነው፤ ከሷ፡ የተ ገኘውን፡ መከራ፡ አመጣባ ታለሁ፤

ወእምኔሆሙ፡ አውፅዕዎሙ፡ ከመዝ፡ እንዲል፤

ወእከሥት፡ ምክራ፡ በቈላተ፡ አካን፤

ያካንን፡ ምክር፡ በገለጥሁበት፡ ቦታ፡ ምክሯን፡ እገልጥባታለሁ፤

በቈላተ፡ አካን፡ ባለው፡ ቈላተ፡ ኤሜቃኮር፡ ይላል፤ ቈላተ፡ ሥራዊ፡ ማለት፡ ነው፤

ወተኃሥር፡ በህየ፡ ከመ፡ አመ፡ መዋ ዕለ፡ ንዕሳ፤

እንደ፡ ሕፃንነቷ፡ ወራት፡ ጊዜ፡ በዚያ፡ ወራት፡ ትዋረዳለች፤

ወከመ፡ ዕለተ፡ ልደታ፡ እምከርሠ፡ እማ፤

ሳንገቷ፡ ፈትል፤ ለወገቧ፡ ጨርቅ፡ ሳትይዝ፡ ከናቷ፡ ማኅ ፀን፡ እንደ፡ ተወለደችበት፡ ቀን፡ አዋርዳታለሁ፤

ወከመ፡ አመ፡ ተዐርግ፡ እምግብፅ፤

ከግብፅ፡ እንደወጣችበት፡ ወራት፡ ትዋረዳለች፤

፲፮፤ ወይከውን፡ ይእተ፡ ዕለተ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር። ትብለኒ፡ ምትየ፤

ያን፡ ጊዜ፡ እግዚአብሔር፡ ፈጣ ሪዬ፡ ነህ፡ ትለኛለች፡ አለ፤

ወኢትብል፡ እንከ፡ በዓሊም፤

በዓል፡ ያለውን፡ በዓሊም፡ ብሎ፡ አበዛ፡ ጣዖቱ እንዳያድን፡ አያ ድነኝም አትለኝም፤

፲፯፤ ወእሥዕር፡ አስማቲሆሙ፡ ለበዓሊም፡ እምአፉሃ፤

ጣዖታቱን፡ እንዳታመሰግን፡ አደርጋታለሁ፤

ወኢትዜክር፡ አስማቲሆሙ፡ እንከ፤

እንግዲህ፡ ወዲህ፡ ቤል፡ ዳጎን፡ ብሉ፡ ስማቸውን፡ አታነሣም፤



፲፰፤ ወእትካየድ፡ ኪዳነ፡ ይእተ፡ ዕለተ፡ ምስለ ኵሉ፡ አራዊተ፡ ገዳም፤

ያንጊዜ፡ ከጅብ፡ ከቀበሮ፡ ጋራ፤

ወምስለ፡ አዕዋፈ፡ ሰማይ፤

ከአዕዋፈ፡ ሰማይ፡ ጋራ፤

ወምስለ፡ አራዊተ፡ ምድር፤

ከውሻ፡ ከድመት፡ ጋራ፡ እማ ማላለሁ፡ ማለት፡ ከአሕዛብ፡ ከኃያላኑ፡ ከሞዓብ፤ ከአሞን፡ ጋራ፡ እማማላለሁ፡ ማለት፡ እኒህ፡ ሁሉ፡ እንዳያጠፏት፡ አደርጋለሁ፤

ወእሥዕር፡ ቀስተ፡ ወኲናተ፡ ወፀብዐ፡ ምድር፤

ቀሥታዊ፡ ፀብዓዊ፡ ሲል፡ ነው፤ ቀስተኛውን፤ አርበኛውን፡ አጠፋለሁ፤

ወአነብረኪ፡ ተአሚነኪ፤

ጠላት፡ ጠፍቶልሽ፡ ተዘልለሽ፡ እንድትኖሪ፡ አደርግሻለሁ፤

፲፱፤ ወእፍኅረኪ፡ ሊተ፡ ብእሲተ፡ ለዓለም፡ በጽድቅ፡ ወበርትዕ፡ በሣህል፡ ወበምሕረት፡ ወእፍኅረኪ፡ ሊተ፡ በሃ ይማኖት፤

እፍኅረኪና፡ እፍኅረኪ፡ አንድ፡ ወገን፤ በሃይማኖት፡ ፀንተሽ፡ ጽድቅን፤ ርትዕን፡ ጸሎት፡ አድ ርገሽ፡ ብትገኚ፡ ይቅርታን፤ ቸር ነትን፡ ማጫ፡ ማስመሪያ፡ አድ ርጌ፡ ለዘለዓለም፡ ማደሪያዬ፡ ልትሆኚ፡ አጮሻለሁ፤

፳፤ ወተአምርኒ፡ እንከ፡ ይቤ፡ እግ ዚአብሔር፤

ይቅርታን፡ ቸርነትን፡ አድርጌ ልሽ፡ ፈጣሪሽ፡ እኔ፡ እንደሆ ንሁ፡ ታውቂኛለሽ፤

## ጉባኤ

፳፩፤ ወይከውን፡ ይእተ፡ ዕለተ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፤

ያን፡ ጊዜ፡ እንዲህ፡ ይሆናል፡ አለ፤

እሰጠዎ፡ ለሰማይ፤

ይከውን፡ ያለውን፡ እሰጠዎ፡ ብሎ፡ አመጣው፤ ሰማይን፡ ዝናም፡ ለዘር፤ ጠል፡ ለመከር፡ ስጥ፡ ብዬ፡ አዝዘዋለሁ፤

ወሰማይኒ፡ ይሰጠዋ፡ ለምድር፤

ሰማይም፡ ለምድር፡ ዝናም፡ ለዘር፤ ጠል፡ ለመከር ይሰጣል፤

፳፪፤ ወምድርኒ፡ ትሰጠዎሙ፡ ለእ ክል፡ ወለወይን፡ ወለቅብዕ፤

ምድርም፡ የዘሩባትን፡ ታበቅ ላለች፤ የተከሉባትን፡ ታጸ ድቃለች፤

ወእሙንቱ፡ ይሰጠውዎሙ፡ ለእስራኤል፤

እሊህ፡ አዝርዕት፡ አትክልት፡ ለእስራኤል፡ ምግብ፡ ሁነው፡

www.ethiopianorthodox.org

ይሰጧቸዋል፤ አንድም፡ እስ
ጠዎ፡ ብለህ፡ መልስ፤ ነቢያ
ትን አስተምሩ፡ ብዬ፡ አዝዛቸ
ዋለሁ፣ ነቢያት፡ እስራኤልን፡
ያስተምራሉ፣ እስራኤልም፡
ትምህርቱን፡ ይቀበላሉ፣ እኒህ፡
ሕግጋቱ፡ እስራኤልን፡ ይጠብ
ቋቸዋል፣ ዛሬ፡ ሰው፡ አምባ
ውን፡ ከሚጠብቀው፡ ይልቅ፡
አምባው፡ ሰውን፡ እንዲጠብ
ቀው፣ ኢነዓቅቦሙ፡ ለሕግጋት፡
አላ፡ እሙንቱ፡ ሕግጋት፡ የዐ
ቅቡነ፡ እንዲል፤ አንድም፡
ሰማይ፡ ገብርኤልን፡ ድንግል፡
ትፀንሲ፡ ወትወልዲ፡ ወልደ፡
ብለህ፡ ንገራት፡ ብዬ፡ አዝዘዋ
ለሁ፣ ይኸስ፡ በዳግም፡ ሕግ፡
ነው፡ እንጂ፡ ከዚህ፡ የለም፡
ብሎ፡ ሰማይ፡ መለኮትን፡
ውረድ፡ ተወለድ፡ ብዬ፡ አዝዘ
ዋለሁ፣ ሰማዕኩ፡ እንዘ፡ ይኤ
ዝዞ፡ እግዚእ፡ ለእግዚእየ፡
ወይብሎ፡ ኅልፍ፡ እንተ፡ አር
ባዕቱ፡ አናቅጽ፡ ሰማይ፡ ወረድ፡
ኀቤሁ፡ ለመልአከ፡ ሞት፡ እን
ዲል፣ ሰማይ፡ መለኮትም፡ ከእ
መቤታችን፡ ከሥጋዋ፡ ሥጋ፣
ከነፍሷ፡ ነፍስ፡ ነሥቶ፡ ሰው፡
ይሆናል፣ ሥግው፡ ቃል፡ ሐዋ
ርያትን፡ ያስተምራቸዋል፣ በግብ
ራቸው፡ እክል፡ ወይን፡ ቅብዕ፡
አላቸው፤ አንድም፡ ሥጋውን፡
ደሙን፡ ያስገኛል፤ አንድም፡
እሰጠዎ፡ ሐዋርያትን፡ አስተ
ምሩ፡ ብዬ፡ አዝዛቸዋለሁ፣
ሐዋርያት፡ ምእመናንን፡ ያስ
ተምራሉ፣ ምእመናንም፡ ትም
ህርቱን፡ ይቀበላሉ፣ እስራኤል፡
ዘነፍስም፡ ሥጋውን፡ ደሙን፡
ይቀበላሉ፤

፳፫፤ ወእዘርዕ፡ ላቲ፡ ሰላመ፡
ውስተ፡ ምድር፤

ምድር፡ የዘሩባትን፡ እንድታ
በቅል፤ አንድም፡ ትምህርቱን፡
በምእመናን፡ ልቡና፡ አሳድራለሁ፤

ወእሣሀላ፡ ለእንተ፡ ኢኮነት፡ ሥሕልተ፤

ሰባ፡ ዘመን፡ ይቅር፡ ያላልኋት፡
ቤተ፡ እስራኤልን፡ ይቅር፡ እላ
ታለሁ፤ አንድም፡ አምስት፡
ሽህ፡ ካምስት፡ መቶ፡ ዘመን፡
ይቅር፡ ያላልኋት፡ ምእመንን፡
ይቅር፡ እላታለሁ፤

ወአፈቅራ፡ ለእንተ፡ ኢኮነት፡
ፍቅርትየ፣

ሰባ፡ ዘመን፡ ወዳጄ፡ ያልነበ
ረች፡ ቤተ፡ እስራኤልን፡ እወዳ
ታለሁ፤ አንድም፡ አምስት
ሽህ፡ ካምስት፡ መቶ፡ ዘመን፡
ወዳጄ፡ ያልነበረች፡ ምእመ
ንን፡ እወዳታለሁ፤



፳፬፤ ወእብሎ፡ ሕዝብየ፡ ለዘኢ
ኮነ፡ ሕዝብየ፣

ሰባ፡ ዘመን፡ ወገኔ፡ ያልሆነ
ውን፡ ወገኔ፡ እለዋለሁ፤ አን
ድም፡ አምስት፡ ሽህ፡ ካምስት፡
መቶ፡ ዘመን፡ ወገኔ፡ ያልሆነ
ውን፡ ወገኔ፡ እለዋለሁ፤

ወውእቱ፡ ይብለኒ፡ እግዚእየ፡ ወአምላ
ኪየ፡ አንተ፣

እሱም፡ ጌታዬ፡ ፈጣሪዬ፡ አንተ፡
ነህ፡ ይለኛል፡፡

## - ምዕራፍ ፫ -

፩፤ ወይቤለኒ፡ እግዚአብሔር፡
አፍቅር፡ ብእሲተ፡ እንተ፡ እከይ፡ ወዝ
ሙት፡ ባቲ፣

ድርቅና፡ ሴሰኝነት፡ ያላትን፡
ሴት፡ ውደድ፡ አለኝ፣ አንዱን፡
ግብሯን፡ ተናግሮ፡ አንዱን፡ ግብ
ሯን፡ ትቶ፡ ነበረና፡ እከይ፡ ለማ
ለት፡ ደገመው፤ አንድም፡ ያን
ዲቱን፡ ግብር፡ ተናግሮ፡ ያን
ዲቱን፡ አልተናገረም፡ ነበርና፡
ስለዚህ፡ ደገመው፤ አንድም፡
በዚህች፡ ሴቶችን፡ ይዘልፋል፤
አንድም፡ ያለፈችቱ፡ አንዲት፡
ናት፡ ቢሉ፡ በዚህች፡ ሁለቱን፡
ነገድ፡ ይዘልፋል፤ አንድም፡ ወተ
አሰብኩ፡ የሚል፡ ነውና፤

በከመ፡ አፍቀሮሙ፡ እግዚአብሔር፡ ለደ
ቂቀ፡ እስራኤል፡ ወእሙንቱሰ፡ ይኔ
ጽሩ፡ ኀበ፡ አምላክ፡ ነኪር፤

ወደ ከነዓን፡ ጣዖት፡ ሲመለ
ከቱ፡ እግዚአብሔር፡ እስራኤ
ልን፡ እንደወደዳቸው፣

ወያፈቅሩ፡ ዘይነሥእ፡ ሐፍሰ፡ ወይነ፡
ዘቢብ፤

እፍኝ፡ ዝግኝ፡ ዘቢብ፡ ቢሰጡት፡
የሚቀበል፡ ጣዖትን፡ ሲወዱት፡
እንደወደዳቸው፡ ድርቅና፡ ሴሰ
ኝነት ያላት፡ ሴትን፡ ውደድ፡
አለኝ፣ ምነው፡ ጌታስ፡ ቈቀር፡
ዕጣን፡ ቢሰጡት፡ ይቀበል፡ የለ
ምን፡ ቢሉ፡ ጌታ፡ የሰጭ፡ ተቀ
ባይ፡ ነው፣ እሱ፡ ግን ይቀበ
ላል፡ እንጂ፡ አይሰጥምና፡ ጌታ፡
አሥራት፡ በኵራት፡ አውጡ፡
ይላል፤ እሱ፡ ግን፡ አይልምና፤
አንድም፡ እግዚአብሔር፡ ቢሰ
ጡት፡ ዋጋ፣ ባይሰጡት፡ ፍዳ፡
ያመጣል፣ እሱ፡ ግን፡ ይህን፡
አያደርግምና፤ አንድም፡ እፍኝ፡
ዝግኝ፡ ዘቢብ፡ ቢለምኑት፡ የሚ
ነሣ፡ ጣዖትን፡ ሲወዱ፡ እንደ፡
ወደዳቸው፡ ድርቅና፡ ሴሰኝነት፡
ያላትን፡ ሴት፡ ውደድ፡ አለኝ፤

፪፤ ወተዐሰብኩ፡ ሊተ፡ በዐሡሩ፡
ወሐምሱ፡ ጠፋልሐ፡ ብሩር፣

ዐሥራ፡ አምስት፡ ዝምዝም፡ ብር፡
ሰጥቼ፡ ሚስት፡ አጨሁ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወበመሥፈርተ፡ ቆሮስ፡ ሰገመ፤

ቆሮስ፡ አሥራ፡ ሁለት፡ ጫን፡ የሚይዝ ነው፤ አንድ፡ ቆሮስ፡ ገብስ፡ ሰጥቼ፤

ወበመሥፈርተ፡ ኔባል፡ ወይነ፤

አንድ፡ ፊቀን፡ ወይን፡ ሰጥቼ፡ ሚስት፡ አጨሁ፤ አንድም፡ ወተ ዐሰብኩ፡ ብለህ፡ መልስ፤ በዐ ሥራ፡ አምስት፡ ሌሊት፡ እስራኤልን፡ ከግብፅ፡ አወጣኋ ቸው፤ በዐሥራ ሁለቱ፡ አው ራኅ፡ መና፡ ከደመና፤ ውሃ፡ ከደንጊያ፡ አፍልቄ፡ መገብኋ ቸው፤ አንድም፡ በአምስት፡ ሽህ፡ ካምስት፡ መቶ፡ ዘመን፡ ከሲ ዖል፡ አወጣቸዋለሁ፤ አምስቱን፡ ሽህ፡ አምስቱን፡ መቶ፡ አንድ፤ አምስቱን፡ መቶ፡ አንድ፡ እያሉ፡ ቢቆጥሩት፡ ዐሥር፡ ይሆናል፤ አምስቱ፡ መቶ፡ ባለበት፤ አን ድም፡ በዐሥራ፡ አምስት፡ ሌሊት፡ ከሲዖል፡ አወጣኋቸው፤ በዐሥራ፡ ሁለቱ፡ ሐዋርያት፡ አድሬ፡ ሥጋዬን፤ በሰብዓ፡ አርድዕት፡ አድሬ፡ ደሜን፡ መገብኋቸው፤ እንዲህ፡ ስላለ፡ ግን፡ ማካፈል፡ አይደለም፤

፫፤ ወእቤላ፡ ንበሪ፡ ምስሌየ፡ ብዙኃ፡ መዋዕለ፤

ከኔ፡ ጋራ፡ ብዙ፡ ዘመን፡ ኑሪ፡ አልኋት፤

ወኢትዘምዊ፡ ወኢታብኢ፡ ካልዐ፡ ብእሴ፤

አትሴስኚ፡ ሌላ፡ ወንድ፡ አታ ግቢ፡ ማለት፡ ጣዖት፡ አታ ምልኪ፤

ወአነ፡ እሄሉ፡ ምስሌኪ፤

እኔ፡ ካንቺ ጋራ፡ እኖራለሁ፡ ማለት፡አድርብሻለሁ፡አልኋት፤

፬፤ እስመ፡ ብዙኃ፡ መዋዕለ፡ ይነ ብሩ፡ ደቂቀ፡ እስራኤል፡ ዘእንበለ፡ ንጉሥ፤

የእስራኤል፡ ልጆች፡ ንጉሥ፡ ጠፍቶባቸው፡ ብዙ፡ ዘመን፡ ይኖራሉና፤

ወዘእንበለ፡ መልአክ፤

መስፍን፡ ጠፍቶባቸው፤

ወዘእንበለ፡ መሥዋዕት፤

መሥዋዕት፡ ጠፍቶባቸው፤

ወዘእንበለ፡ ካህናት፤

ካህን፡ ጠፍቶባቸው፤

ወዘእንበለ፡ ራእይ፤

ነቢይ፡ ጠፍቶባቸው፤

ወአልቦ፡ ኤፉድ፤

ልብሰ፡ ተክህኖ፡ ጠፍቶባቸው፤

ወአልቦ፡ ሱራፌን፤

ምሉጣ፡ ቀሚስ፡ ጠፍቶባቸው፡ ብዙ፡ ዘመን፡ ይኖራሉና፤ አን ቺስ፡ ከነዚህ፡ ይብስብሻልን፡ ከኔ፡ ጋራ፡ ኑሪ፡ አልኋት፤ አን ድም፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ ሌላ፡ ሕገ፡ ኦሪትን፡ አትያዥ፤ ሐዲስ፡ ወንጌልን፡ ያዥ፡ አልኋት፤ እስ ራኤል፡ ንጉሥ፤ መስፍን፤ መሥ



ዋዕት፤ ሊቀ፡ ካህናት፤ ነቢይ፤ ልብሰ፡ እንግድአ፤ ልብሰ፡ መት ከፍ፡ ጠፍቶባቸው፡ ኑረዋልና፤ እንደነዚያ፡ እንደ፡ ዘመነ፡ ብሉይ፡ ሰዎች፡ እንዳትሆኚ፡ ሕገ፡ ኦሪትን፡ ትተሽ፡ ሕገ፡ ወንጌልን፡ ያዥ፡ አልኋት፤ አን ድም፡ ይህ፡ ሁሉ፡ ጠፍቶባ ቸው፡ ይኖራሉና፤

፭፤ ወእምዝ፡ ይትመየጡ፡ ደቂቀ፡ እስራኤል፤

ከዚህ፡ በኋላ፡ የእስራኤል፡ ልጆች፡ ወደ አምልኮተ፡ እግዚ አብሔር፡ ይመለሳሉ፤

ወየኀሥሥዎ፡ ለእግዚአብሔር፡ አምላኮሙ፤

ፈጣሪያቸው፡ እግዚአብሔርን፡ በሕግ፡ በአምልኮት፡ ይሹታል፤

ወለዳዊት፡ ንጉሦሙ፤

ንጉሣቸው፡ ዘሩባቤልን፡ ይሹታል፤

ወይዜክርዎ፡ ለእግዚአብሔር፤

እግዚአብሔርን፡ ያስቡታል፡

ወለሠናይቱ፡ በደኃሪ፡ መዋዕል፤

በኋላ፡ ዘመን፡ የሚሰጣቸውን፡ ቸርነቱን፡ ያስባሉ።

## - ምዕራፍ ፬ -

፩፤ ስምዑ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ደቂቀ፡ እስራኤል፤

የእስራኤል፡ ልጆች፡ የእግዚአ ብሔርን፡ ነገር፡ ስሙ፤

እስመ፡ ይትዋቀሦሙ፡ እግዚአብሔር፡ ለእለ፡ ይነብሩ፡ ውስተ፡ ዓለም፡

በዚህ፡ ዓለም፡ የሚኖሩትን፡ ሰዎች፡ እግዚአብሔር፡ ይከራ ከራቸዋልና፤

፪፤ እስመ፡ አልቦ፡ ጽድቅ፤

ጽድቅ፡ ስለሌለ፤

ወአልቦ፡ ምሕረት፤

ምሕረት፡ ስለሌለ፤

ወአልቦ፡ አእምሮ፡ እግዚአብሔር፡ ውስተ፡ ምድር፤

በዚህ፡ ዓለም፡ እግዚአብሔ ርን፡ ማወቅ፡ ስለሌለ፡ ሦስቱ፡ አርእስት፡ ነውና፡ ለሦስቱም፡ ያመጣል፤

ዘእንበለ፡ ሐሰት፤

ሐሰት፡ ነው፡ እንጂ፡ ጽድቅ፡ ስለሌለ፤

ወቀትል፤

ነፍስ፡ መግደል፡ እንጂ፡ ምሕ ረት ስለሌለ፤

ወሰርቅ፤

መስረቅ፡ ነው፡ እንጂ፡ እግዚ አብሔርን፡ ማወቅ፡ ስለሌለ፤

ወዝሙት፡ መልዐ፡ ምድረ፤

ኃጢአት፡ በዓለም፡ በዛ፤

ይደምሩ፡ ደመ፡ ምስለ፡ ደም፤

በአደረ፡ ደም፡ ይሠዋሉ፤ ሽክላ፡ ቢሆን፡ ይሰበሩት፤ ብረት፡ ቢሆን፡

www.ethiopianorthodox.org

ይሰንግሉት፣ ይጠልውሉት፡ ይላልና፤ አንድም ዛሬም፡ ነገም፡ ይገድሏቸዋልና፤ አንድም፡ ዘር፡ ከዘር፡ ይቀላቅላሉ፣ አባት፡ ከደረሰባት፡ ልጅ፣ ልጅ ከደረሰባት፡ አባት ይደርሳል፤ አብ፡ ወወልድ፡ ይበውዑ፡ ውስተ፡ አሐቲ፡ ብእሲት፡ ብሎ፡ እንዲያመጣ፤ አንድም፡ የሰውን፡ ደም፡ ያፈስሳሉ፤ አንድም፡ ላህምስ፡ ኃልቀ፡ ንሥዕ፡ ሉቡእ፡ ይላል፤ አንድም፡ የሎሌ፡ ደመወዝ፡ ይቀማሉ፣ ከነስሙ፡ ደመወዝ፡ አለው፤

፫፤ በእንተ፡ ዝንቱ፡ ትላሁ፡ ምድር፣

ስለዚህ፡ ነገር፡ ምድር፡ ትጠፋለች፤

ወትውኅድ፡ ምስለ፡ ኵሎሙ፡ እለ፡ ይነብሩ፡ ውስቴታ፣

ምድር፡ በሷ፡ ከሚኖሩ፡ ሰዎች፡ ጋራ፡ ትጠፋለች፤

ምስለ፡ አራዊተ፡ ገዳም፣

ከአራዊተ፡ ገዳም ጋራ፤

ወምስለ፡ አዕዋፈ፡ ሰማይ፣

ከአዕዋፈ፡ ሰማይ፡ ጋራ፤

ወምስለ፡ አራዊተ፡ ምድር፣

ከአራዊተ፡ ምድር፡ ጋራ፡ ትጠፋለች፤

ወየኃልቁ፡ ዓሣተ፡ ባሕር፣

ዓሣተ፡ ባሕርም፡ ይጠፋሉ፣ ድርቅ፡ የማያስተባብረው የለምና፤

፬፤ ወአልቦ፡ እንከ፡ መኑሂ፡ ዘይትዋቀስ፡ ወአልቦ፡ ዘይዘልፍ፡ ወኢመኑሂ፣

ከነቢያት፡ ከካህናት፡ ማንም፡ ማን፡ የሚመክር፡ የሚያስተምር፡ የለም፤

ወሕዝብየሰ፡ ካህናት፡ እለ፡ ይትዋሥዑ፡ ኮኑ፡ ከመ፡ ዘኢይትዋሥዑ፣

ይመክሩ፡ ያስተምሩ፡ የነበሩ፡ ወገኖቼ፡ ነቢያት፡ ካህናት፡ እንደማይመክሩ፣ እንደማያስተምሩ ሰዎች፡ ሆኑ፤ አንድም፡ የሚመክሩ፡ የሚያስተምሩ፡ ወገኖቼ፡ ነቢያት፡ ካህናት፡ ከመንጥሶ፡ የማይመክሩ፡ የማያስተምሩ፡ ሰዎችን፡ ሆኑ፤

፭፤ ወይደክሙ፡ በፍኖት፡ ካህን፡ ወነቢይ፡ ወሕዝብ፡ ኅቡረ፣

ተማርከው፡ ሲሄዱ፡ ካህኑም፣ ነቢዩም፣ ሕዝቡም አንድ፡ ሁነው፡ ይደክማሉ፤

ወትመስል፡ እምክሙ፡ ሌሊተ፣

ነገሥታቱ፡ ካህናቱ፡ በመከራ፡ ይጠቁራሉ፤

፮፤ ወይመስሉ፡ ሕዝብየ፡ ከመ፡ ዘአልቦ፡ ልብ፣

ወገኖቼ፡ አዕምሮ፡ እንደሌለው፡ ሰው፡ ይሆናሉ፤

እስመ፡ ለከሂ፡ ኃደገከ፡ ልብከ፡ ወአነሂ፡ ኃደጉከ፣

አእምሮህ፡ ተለይቶኻልና፡ ይመስሉ፡ ላለው፡ ወአነሂ፡ ማንሻ፡ እኔም፡ ተለየሁህ፤ አንድም፡ እኔ፡ በረድኤት፡ ተለይቼሃለሁና፤ አንድም፡ አእምሮ፡ ተለይቶሃልና፤



ወኢትሡዕ፡ ሊተ፣

መሥዋዕቱን፡ አትሠዋልኝ፤

እስመ፡ ረሳዕከ፡ ሕገ፡ አምላክከ፡ ወአነሂ፡ እረስዖሙ፡ ለደቂቅከ፣

የፈጣሪህን፡ ሕግ፡ ዘንግተሃልና፡ እኔም፡ ተለየሁህ፤ አንድም፡ የፈጣሪህን፡ ሕግ፡ ዘንግተሃልና፡ እኔም ልጆችህን፡ እዘነጋቸዋለሁ፤

፯፤ በከመ፡ ብዝኖሙ፡ ከማሁ፡ አበሱ፡ ሊተ፣

እንደ፡ ብዛታቸው፡ መጠን፡ በደሉኝ፣ ሰው፡ ሲበዛ፡ ኃጢአት፡ ይበዛልና፤

ወእሬስዮ፡ ኃሣረ፡ ለክብሮሙ፣

ክብራቸውን፡ በኃሣር፡ እለውጠዋለሁ፤ አንድም፡ ጣዖቱ፡ ኃሣሩን ያመጣባቸዋል፤

፰፤ ወትበልዖሙ፡ ኃጢአቶሙ፡ ለሕዝብየ፣

ወገኖቼ፡ እስራኤልን፡ በኃጢአታቸው፡ ምክንያት፡ መዓት፡ መቅሠፍት፡ ታጠፋቸዋለች፤

ወይነሥእዋ፡ ለነፍሶሙ፡ በጌጋዮሙ፣

በኃጢአታቸው፡ ምክንያት፡ ሥላሴ፡ ሰውነታቸውን፡ በሞት፡ ይወስዷታል፤

፱፤ ወይከውን፡ በከመ፡ ዝንቱ፡ ሕዝብ፡ ከማሁ፡ ካህን፣

ጨዋው፡ እንዲታበይ፡ ካህኑም፡ ይታበያል፤ አንድም፡ ጨዋው፡ ትብትብ፡ ምንጣፍ፡ እንዲሸከም፡ ካህኑም፡ ትብትብ፡ ምንጣፍ፡ ተሸክሞ፡ ይሄዳል፤

ወእትቤቀሎሙ፡ በፍኖቶሙ፣

በሥራቸው፡ ተበቅዬ፡ አጠፋቸዋለሁ፤

ወእትፌደዮሙ፡ በከመ፡ ምግባሮሙ፣

እንደሥራቸው፡ መጠን፡ ፍዳውን፡ እከፍላቸዋለሁ፤

፲፤ ይበልዑ፡ ወኢይጸግቡ፣

ይህ፡ ሊመጣባቸው፡ ይበላሉ፡ አይጠግቡም፤

ይዜምዉ፡ ወኢይፌደፍዱ፡ እንከ፣

ከብዙ፡ ሴት፡ ይደርሳሉ፡ አይበዙም፤

እስመ፡ ሐደግዎ፡ ለእግዚአብሔር፡ አምላኮሙ፣

ፈጣሪያቸው፡ እግዚአብሔርን፡ በሕግ፡ በአምልኮት፡ ትተውታልና፤

፲፩፤ ከመ፡ ይዕቀቡ፡ ዝሙተ፡ ወስታየ፡ ወስካረ፣

ዝሙትን፣ ስካርን፣ መጠጥን፡ ያበዙ፡ ዘንድ፤

እስመ፡ ዝሙት፡ ወወይን፡ ይነሥኡ፡ ልበ፣

ዝሙት፡ ወይን፡ አእምሮ፡ ያሳጣሉና፤

፲፪፤ እስመ አፍቀረ፡ ልቦሙ፡ ለሕዝብየ፡ ሰገለ፡ ይሴአሉ፣

ጥንቆላን፡ ይጠይቁ፡ ዘንድ፡ የወገኖቼ፡ ልቡና፡ ወዷልና፤

www.ethiopianorthodox.org

ወበትሩ፡ ይሰጠዎ፤

ንጉሡ፡ እንዲህ፡ ይሆናል፡ እያለ፡ ትች፡ ይተቻል፤ አን ድም፡ ንጉሡ፡ ለኔም፡ ጠይቁ ልኝ፡ ይላል፤ አንድም፡ ሰገለ፡ ይሴአሉ፤ ጥንቆላን፡ ይጠነቁላ ሉና፡ ዛጉል፡ ጥለው፡ ስንደድ፡ በጥሰው፡ ያሚርታሉ፤

በመንፈስ፡ ዝሙት፡ ስሕቱ፡ ወዘመዉ፡ እምአምላከሙ፤

ዝሙትን፡ በሚሻ፡ ልቡና፡ ሳቱ፡ ከፈጣሪያቸውም፡ ተለይተው፡ በደሉ፤

፲፫፤ ወይሠውዑ፡ ውስተ፡ አድ ባር፡ ወውስተ፡ አውግር፤

በተራራው፡ በኮረብታው፡ ላይ፡ ይሠዋሉ፡ ፀሐይ፡ ጨረቃን፡ ያመልካሉና፡ እንዲቀርባቸው፤ አንድም፡ ሥዕለ፡ ፀሐይን፡ ሥዕለ፡ ጨረቃን፡ ያመልካሉና፡ እንዲቀርባቸው፤ አንድም፡ ተራራ ውን፡ ያመልካሉና፤ አንድም፡ ፈቃዳቸውን፡ ከሰው፡ ተለይ ተው፡ ለመፈጸም፡ ተረፈ፡ መሥ ዋዕቱን፡ በልተው፡ ጠጥተው፡ እሳቱን፡ አጥፍተው፡ ደይ፡ እጼክ፡ ኀበ፡ ዘኀረይከ፡ (ዘፈቀድከ) ይላል፤ ወንድ፡ ልጅ፡ ከእናቱ፤ ሴት፡ ልጅ፡ ከአባቷ፡ ትደርሳለች፤ ለምን፡ እንዲህ፡ አደረጋችሁ፡ ያሏቸው፡ እንደሆነ፡ ባናይ፡ ምን፡ እናድርግ፡ ለማለት፤

ወይዘብሑ፡ ታሕተ፡ ዖመ፡ ባሉጥ፡ ወቡጥም፡፡

ወይራ፡ግራር፡ባሉጥም፡ በቁሙ፡ እንጨት፡ ነው፤

ወገውዝ፡ ወለውዝ፤

ቀይ፡ አበባ፡ ጥቁር፡ አበባ፡ ማለት ነው፤ አንድም፡ ባሉጥ፡ ወቡ ጥም፡ ያለውን፡ ለውዝ፡ ገውዝ፡ ብሎ፡ ተረጉመው፤ ከዛፉ፡ ሥር፡ ሁሉ፡ ይሠዋሉ፤

ወታሕተ፡ ጽላሎተ፡ ዕፅ፡ ዘሠናይ፡ ጽላሎቱ፤

ጥላው፡ ባማረ፡ ዛፍ፡ ሁሉ፡ ይሠዋሉ፤

በእንተ፡ ዝንቱ፡ ይዜምዋ፡ አዋልዲ ክሙ፡ ወይትመሐዛ፡ መራዕዊክሙ፤

ስለዚህ፡ ሴቶች፡ ልጆቻችሁ፡ ይሰስናሉ፤ ወንዶች፡ ልጆቻች ሁም፡ በጫጉላ፡ ቤት፡ ይሰ ስናሉ፤

፲፬፤ ወኢ.ገሠጽክምዎን፡ ለአዋልዲ ክሙ፡ ሶበ፡ ዘመዋ፤

ሴቶችም፡ ልጆቻችሁ፡ በበደሉ፡ ጊዜ፡ አልገሠጻችኋቸውምና፡ ስለ ዚህ፡ ይበድላሉ፤

ወኢለመራዕዊክሙ፡ ሶበ፡ ተመሐዛ፤

ኢገሠጽክምዎሙ፡ ያለበት፡ ነው፤ ወንዶች ልጆቻችሁም፡ በተቀማጠሉ፡ ጊዜ፡ አልቀጣች ኋቸውምና፡ ስለዚህ፡ ይበድላሉ፤



እስመ፡ ተደመሩ፡ ምስለ፡ ዘማውያን፤

ከአሕዛብ፡ ጋራ፡ አንድ፡ ሁነ ዋልና፤

ወሦዑ፡ ምስለ፡ ሕጉላን፡ ሕዝብ፤

አእምሯቸውን፡ ካጡ፡ ሰዎች፡ ጋራ፡ መሥዋዕቱን፡ ሠውተ ዋልና፤

ወሕዝብ፡ ዘይሌቡ፡ ተደመረ፡ ምስለ ዘኢ.ይሌቡ፤

ሕገ፡ እግዚአብሔርን፡ ልብ፡ የሚያደርግ፡ እስራኤል፡ ሕገ፡ እግዚአብሔርን፡ ልብ፡ ከማያ ደርጉ፡ ከአሕዛብ፡ ጋራ አንድ፡ ሆነ፤ አንድም፡ ዘይሌቡ፡ ባለው፡ ዘኢ.ይሌቡ፡ ይላል፤ ሕገ፡ እግ ዚአብሔርን፡ ልብ፡ የማያደ ርግ፡ እስራኤል፡ ከዘማውያን፡ ጋራ፡ አንድ ሆነ፤

፲፭፤ ወአንተሂ፡ እስራኤል፡ ኢትዕበድ፤

አንተም፡ እስራኤል፡ አትስነፍ፤

ወአንተሂ፡ ይሁዳ፡ ኢትሑር፡ ገልገላ፤

አንተም፡ ይሁዳ፡ ኃጢአት፡ ለመሥራት፡ ወደ፡ ገልገላ፡ አትሂድ፤

ወኢትዕርግ ቤተ፡ አዎን፤

ወደቤተ፡ ጣዖት፡ አትሂድ፤

ወኢትምሐል፡ በሐሰት፡ በስመ፡ እግዚ. አብሔር፡ ሕያው፤

በሐሰት፡ የሕያው፡ እግዚአብሔ ርን፡ ስም፡ ጠርተህ፡ አትማል፤

፲፮፤ እስመ፡ ከመ፡ ዕጉልት፡ እንተ፡ ተኃረብድ፡ ሐርበደ፡ ኤፍሬም፤

ኤፍሬም፡ ጊደር፡ እንድትቀ ናጣ፡ ተቀናጣ፤

ወናሁ፡ ይእዜ፡ ይሬእዮሙ፡ እግዚ.አብ ሔር፡ ከመ፡ አባግዕ፡ ውስተ፡ ዒ.ዖት፤

በግ፡ ወደመስክ፡ ሲሰማራ፡ እን ዲታይ፡ እግዚአብሔር፡ ወደቤተ፡ ጣዖት፡ ሲገሰግሱ፡ ያያቸዋል፤ ከማሁ፡ ማንሻ፤ አንድም፡ በግ፡ ወደመስክ፡ መሄድን፡ እን ዲወድ፤

፲፯፤ ከማሁ፡ አፍቀረ፡ ኤፍሬም፡ ጣዖተ፤

ኤፍሬም፡ ጣዖትን፡ ወደደ፤ አን ድም፡ በግን፡ በምድረ፡ በዳ፡ አሠማርቶ፡ እንዲመለከት፡ በዓ ይነ፡ መዓት፡ ይመለከታቸዋል፡፡

ወሤመ፡ ሎቱ፡ ዕቅፍተ፤

ጣዖቱን፡ አኖረ፤

፲፰፤ ወአብደሮሙ፡ ለከናኔዎን፤

በአሕዛብ፡ አምሳል፡ የተሠሩ፡ ጣዖታትን፡ ወደዱ፤

ዘምዎ፡ ዘመዉ፤

ፈጽመው፡ በደሉ፤

፲፱፤ ወአብደሩ፡ ኃሣረ፡ በእከዮሙ፤ ወበዕልወተ፡ ነፍሶሙ፡ እንተ፡ ይእቲ፡ መንፈሰ፡ ዝሙት፤

ይችም፡ ዝሙትን፡ የምትሻ፡ ልቡና፡ ናት፡ በልቡናቸው፡ ክህደት፤ በኃጢአታቸው፡ ብዛት፡ ጣዖቱን ወደዱ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወይትኃፈሩ፡ በምሥዋዓቲሆሙ፤

ለጣዖት፡ በሠዉበት፡ ቦታ፡ ያፍራሉ።

## - ምዕራፍ ፭ -

፩፤ ስምዑ፡ ዘንተ፡ ካህናት፤

ካህናት፡ ይህንን፡ ተግሣጽ፡ ስሙ፤

ወአጽምዕዎ፡ ቤተ፡ እስራኤል፤

የእስራኤል፡ ወገኖች፡ ስሙ፤

ወይስምዕዎ፡ ቤተ፡ ንጉሢ፤

የንጉሥ፡ ወገኖችም፡ ይስሙ፤

እስመ፡ በእንቲአክሙ፡ ውእቱ፡ ዝንቱ፡ ኵሉ፡ ኵነኔ፤

ይህ፡ ሁሉ፡ መቻያ፡ የመጣ፡ በናንተ፡ ምክንያት፡ ነውና፤

እስመ፡ መሥገርተ፡ ኮንክምዎ፡ ለዘያስተሐይጽ፤

ሕግ፡ እግዚአብሔር፡ ፈረሰብኝ፡ ብሎ፡ ለሚያስተነትን፡ ለነቢዩ፡ ወጥመድ፡ ሆናችሁበታልና፤

፪፤ ወከመ፡ መሥገርት፡ እንተ፡ ሰፍሑ፡ ያሥግሩ፡ ባቲ፡ እለ፡ ይንዕዉ፡ ነዓውተ፡ ተከልዋ፤

ገመዱን፡ ሲያይ፡ ሰፍሑ፡ እንጨቱን፡ ሲያይ፡ ተከልዋ፡ አለ፤

አዳኞች፡ እንዳጠመዱት፡ ወጥመድ፡ ሆናችሁበታልና፤

ወአንሰ፡ ነቢይ፡ መገሥጽክሙ፤

እንዲያው፡ ጠላችሁኝ፡ እንጂ፡ እኔስ፡ መምህራችሁ፡ መካሪያችሁ ነበርሁ፤

፫፤ ወአነ፡ አእመርክዎ፡ ለኤፍሬም፤

እኔ፡ የኤፍሬምን፡ ክፋቱን፡ አወቅሁበት፤

ወእስራኤልኒ፡ ኢርኅቀ፡ እምኔየ፤

እስራኤልም፡ እኔን፡ ከመበደል፡ አልራቀም፤ አንድም፡ እኔ፡ ከማመጣበት፡ መከራ፡ አልራቀም፤

እስመ፡ ይእዜ፡ ዘመወ፡ ኤፍሬም፤

ኤፍሬም፡ ዛሬ፡ ጣዖት፡ አምልኳልና፤

ወረኵሰ፡ እስራኤል፤

እስራኤልም፡ ጣዖት፡ አምልኳልና፤ እኔን፡ ከመበደል፡ አልራቀም፤

፬፤ ወኢሜጡ፡ ልቦሙ፡ ከመ፡ ይግብኡ፡ ኀበ፡ አምላኮሙ፤

በሕግ፡ በአምልኮት፡ ወደ፡ ፈጣሪያቸው፡ ይመለሱ፡ ዘንድ፡ ልቡናቸውን፡ አልመለሱም፤

እስመ፡ መንፈስ፡ ዝሙት፡ ላዕሌሆሙ፤

ዝሙትን፡ የሚሻ፡ ልቡና፡ በላያቸው፡ ላይ፡ ጸንቷልና፤

ወእሙንቱሰ፡ ኢያእመርዎ፡ ለእግዚአብሔር፤

እነሱ፡ ግን፡ እግዚአብሔርን፡ በአምልኮት፡ አላወቁትም፤

፭፤ ወኃሣሩ፡ ለእስራኤል፡ ወጽዕሉ፡ ቅድመ፡ ገጹ፤

አሕዛብ፡ እስራኤልን፡ ፊት፡ ለፊት፡ ይሰድቡታል፤ አንድም፡ ስድቡ፡ ተዋርዶው፡ ገና፡ ነው፡ ወደፊት፡ ይመጣበታል፤



ወይደክሙ፡ እስራኤል፡ ወኤፍሬም፡ በጌጋዮሙ፤

እስራኤል፡ ሕዝቡ፤ ኤፍሬም፡ ንጉሡ፡ በኃጢአታቸው፡ ምክንያት፡ ይደክማሉ፤

ወይሁዳኒ፡ ይደዊ፡ ምስሌሆሙ፤

ይሁዳም፡ ከነዚያ፡ ጋር፡ መከራ፡ ይቀበላል፤

፮፤ ምስለ፡ አልህምት፡ ወአባግዕ፡ ኅቡረ፤

ከአልህምት፡ ከአባግዕ፡ ጋራ፡ ይማረካል፤

ወየሐውሩ፡ ይኅሥሥዎ፡ ለእግዚአብሔር፡ ወኢይረክብዎ፤

በሕግ፡ በአምልኮት፡ እግዚአብሔርን፡ ይሹት፡ ዘንድ፡ ይሄዳሉ፤ በረድኤት፡ አያገኙትም፤

እስመ፡ ኃደጎሙ፤

በረድኤት፡ ተለይቷቸዋልና፤

፯፤ እስመ፡ አለውዎ፡ ለእግዚአብሔር፡ ወተናከርዎ፤

እግዚአብሔርን፡ ስለካዱት፤ ባዕድ፡ ስለሆኑት፤

ወውሉደ፡ ነኪር፡ ኮንዎ፤

የከንዓን፡ ልጆች፡ ስለሆኑ፡ ተለይቷቸዋልና፤ ኢይረክብዎ፡ ብለህ፡ እሠር፤

ወናሁ፡ ይእዜ፡ አናኵዕ፡ ይበልዕዎ፡ ለርስቶሙ፤

እነሆ፡ ዛሬ፡ ኵብኩባ፤ አንድም፡ ናቡከደነፆር፡ ገንዘባቸውን፡ ያጠፋዋል፤

፰፤ ንፍሑ፡ ቀርነ፡ ውስተ፡ አድባር፤

በተራራ፡ ላይ፡ ነጋሪቱን፡ ምቱ፡ አንበጣ፡ ለመከልከል፤ አንድም፡ ጦር፡ ለመሰብሰብ፤ አንድም፡ ምህላ፡ ለመያዝ፤

ወንሥዑ፡ ከበሮ፡ ውስተ፡ አውግር፤

በኮረብታው፡ ላይ፡ ከበሮውን፡ ምቱ፡ አንበጣ፡ ለመከልከል፤ አንድም፡ ጦር፡ ለመሰብሰብ፤

ወወውዑ፡ ውስተ፡ ቤተ፡ አዎን፤

በጣዖቱ፡ ቤት፡ ደንፉ፡ አግሩ፤ አንድም፡ በጣዖቱ፡ ቤት፡ ምሕላ፡ ያዙ፡ ፍና፡ ተሳልቆ፡ ነው፤

፱፤ በነበ፡ ኀሥረ፡ ብንያም፡ ወኤፍሬም፡ ኮነ፡ ለሙስና፤

በነበ፡ ኃሥረ፡ ኤፍሬም፡ ብንያም፡ ኮነ፡ ለሙስና፡ ሲል፡ ነው፤ አሥሩ፡ ነገድ፡ በተዋረደበት፡ ሁለቱ፡ ነገድ፡ ይዋረዳል፤ አንድም፡ ብንያማዊ፡ ሳኦል፡ በተዋረደበት፡ ሁለቱ፡ ነገድ፡ ይዋረዳል፤ አንድም፡ በነበ፡ የኃሥር፡ ብንያም፡ ኤፍሬም፡ ኮነ፡ ለሙስና፤ ኋላ፡ ሁለቱ፡ ነገድ፡ በሚዋረድበት፡ አሥሩ፡ ነገድ፡ ይዋረዳል፤ አንድም፡ ነገደ፡ ብንያም፡ በጠፋበት፡ መቅሠፍት፡ አሥሩ፡ ነገድ፡ ለጥፋት፡ ሆኑ፤ አሥሩ፡ ነገድ፡ ነገደ፡ ብንያም፡ በኰኵሐ፡ ሬሞን፡ ስድስት፡ መቶ፡ ሰዎች፡ ሲቀሩ፡ የቀሩት፡ አልቀዋልና፤

www.ethiopianorthodox.org

በመዋዕለ፡ ይዘልፍዎሙ፡ ለሕዝበ፡ እስራኤል፤

ይኸውም፡ አሕዛብ፡ ከበዋቸው፡ ሳለ፡ ነው፤ አንድም፡ ነቢያት፡ ሲያስተምሯቸው፡ ነው፤

ወበህየ፡ ርኢኩ፡ ዕሙነ፤

በዚያ፡ ጣዖቱን፡ የታመነ፡ ሆኖ፡ አየሁት፤

፲፤ ወኮኑ፡ መላእክተ፡ ይሁዳ፡ ከመ፡ ዘይትዓደ፡ ወሰነ፤

የይሁዳ፡ አለቆች፡ ድንበር፡ እንደ ሚያፈርስ፡ ሰው፡ ሆኑ፤ አን ድም፡ ሕገ፡ እግዚአብሔርን፡ እንደሚያፈርስ፡ ሰው፡ ሆኑ፤ አንድም፡ ሕገ፡ እግዚአብሔ ርን፡ የሚያፈርሱ፡ ሆኑ፤

ወዕክዑ፡ መዓትየ፡ ላዕሌሆሙ፡ ከመ፡ ማይ፤

መዓቴን፡ መቅሠፍቴን፡ እንደ ውሀ፡ አብዝቼ፡ አመጣባቸዋለሁ፤

፲፩፤ ኤፍሬም፡ ኮነ፡ ተዓጋሌ፡ ወኬዳ፡ ለፍትሕ፤

ኤፍሬም፡ ቀማኛ፡ ሆነ፤ ኢት ፍቱ፡ ንዋየ፡ ካልዕከ፡ ያለውን፡ አፈረሰ፤ አንድም፡ አምልኮተ፡ እግዚአብሔርን፡ ቀማ፤ ኢታ ምልክን፡ አፈረሰ፤

እስመ፡ አኃዙ፡ ይትልዉ፡ ፃሕወ፤

ፃሕውን፡ ይከተሉ፡ ዘንድ፡ ጀም ረዋልና፡ ፃሕው፡ አርዌ፡ ነው፤ አራዊት፡ ስለሥስት፡ ነገር፡ ይከ ተሉታል፤ ድምፁ፤ መልኩ፤ መዓዛው፡ ስላማረ፡ መልኩን፡ እናያለን፤ ድምፁን፡ እንሰማ ለን፤ መዓዛው፡ ይሸተናል፡ ብለው፡ ያመልኩታልና፤ አን ድም፡ አሣውን፡ ያመልኩ፡ ዘንድ፡ በቋንቋው፡ ፃሕው፡ ብሎ ታል፤ አንድም፡ ያሣውን፡ ምስል፡ አመለኩ፤ አንድም፡ ዓሣውን፡ ሲበሉ፡ እሾሁ፡ የወጋቸው፡ እን ደሆነ፡ ፈጣሪያችን፡ ቢሆን፡ ብንበድለው፡ ነው፡ ብለው፡ ያመልኩታልና፤

፲፪፤ ወአነ፡ እከውኖ፡ ከመ፡ ነቀዝ፡ ለኤፍሬም፤

እኔ፡ ባሥሩ፡ ነገድ፡ እንደነ ቀዝ፡ እሆንባቸዋለሁ፡ ነቀዝ፡ ጥቂት፡ ጥቂት፡ እያለ፡ ነው፡ የሚበላ፤ ስልምናሶር፡ ጥቂት፡ ጥቂት፡ እያለ፡ ማርኳቸዋልና፤

ወከመ፡ ቊንቊኔ፡ ለቤተ፡ ይሁዳ፤

ለሁለቱ፡ ነገድም፡ እንደብል፡ እሆንባቸዋለሁ፤ ብል፡ ባዩት፡ ጊዜ፡ አምሽኮት፡ ይገኛል፤ ናቡ ከደነፆርም፡ አንድ፡ ጊዜ፡ ማር ኳቸዋልና፤

፲፫፤ ወርእያ፡ ኤፍሬም፡ ለደዌሁ፤

ኤፍሬም፡ ሕግን፡ በነቢያት፡ ስትነገር፡ ሰማት፤

ርእያን፡ ሰምአ፡ ሲል፡ ነው፤ አፅንን፡ ዕዝነከ፡ ለርእየ፡ ሕልመ፡ አቡከ፡ ወርእዮ፡ ሕልመ፡ አቡሁ፡ ገብአ፡ ማቱሳላ፡ እንዲል፤ አን ድም፡ ተደርጋበት፡ አያት፤



ወለፃዕሩ፡ ይሁዳ፡ ርእየ፤

ይሁዳም፡ በነቢያት፡ ስትነገር፡ ሰማት፤ አንድም፡ ተደርጋበት፡ አያት፤ ባይጠብቃት፡ ደዌ፡ ፃዕር፡ የምታመጣበት፡ ስለሆነ፡ ደዌ፡ ፃዕር፡ አለ፤

ወሖረ፡ ኤፍሬም፡ ኀበ፡ ግብፅ፤

ኤፍሬም፡ ርዳኝ፡ እያለ፡ ወደ፡ ግብፅ፡ ሄደ፤ ኀበ፡ ፋርስ፡ ይላል፡ ልገብር፡ ልቀቅል፡ ብሎ፡ ወደ ፋርስ፡ ይሄዳል፤

ወፈነወ፡ ተናብልተ፡ ኀበ፡ ንጉሠ፡ ኢያሪም፤

ልገብር፡ ልቀቅል፡ ብሎ፡ ወደ ስልምናሶር፡ አማላጅ፡ ሰደደ፤

ወውእቱ፡ ኢክህለ፡ ፈውሶተክሙ፤

ፈርኦን፡ እናንተን፡ መርዳት፡ አልተቻለውም፤ አንድም፡ ስል ምናሶር፡ እናንተን፡ መተው፡ አልተቻለውም፤

እስከ፡ ሐልቀ፡ ሕማም፡ በላዕሌክሙ፤

መከራ፡ በናንተ፡ እስኪፈጸም፡ ድረስ፤

፲፬፤ እስመ፡ አነ፡ እከውኖሙ፡ ከመ፡ ነምር፡ ለኤፍሬም፤

ባሥሩ፡ ነገድ፡ እንደ፡ ነብር፡ እሆ ንባቸዋለሁ፤ ነብር፡ ዕለቱን፡ አይ በላም፤ አበስብሶ፡ ነው፤ ስል ምናሶርም፡ ጥቂት፡ ጥቂት፡ እያለ፡ ማርኳቸዋልና፤

ወከመ፡ አንበሳ፡ ለቤተ፡ ይሁዳ፤

በሁለቱ፡ ነገድም፡ እንደ፡ አን በሳ፡ እሆንባቸዋለሁ፤ አንበሳ፡ ዕለቱን፡ ሰብሮ፡ ይበላል፤ ናቡ ከደነፆርም፡ ዕለቱን፡ ማርኳ ቸዋልና፤

ወአነ፡ እመስጠሙ፡ ወእነሥኦሙ፡ ከመ፡ ነምር፤

እንደ፡ ነብር፡ እወረወርባቸዋ ለሁ፤ እንደ፡ አንበሳ፡ እከመ ርባቸዋለሁ፤

ወአልቦ፡ ዘያድኅኖሙ፤

የሚያድናቸው፡ የለም፤

፲፭፤ ወእሠውጥ፡ ወአሐውር፡ ቤትየ፤

ወደ፡ ሰማይ፡ ወደቸልታ፡ ወደ ሥዋሬ፡ እመለሳለሁ፤

እስከ፡ አመ፡ ይጠፍዑ፤

እስኪጠፉ፡ ድረስ።

## - ምዕራፍ ፮ -

፩፤ ወየኃሥሡ፡ ገጽየ፡ በዕለተ፡ ምንዳቤሆሙ፤

በመከራቸው፡ ቀን፡ ገጸ፡ ረድ ኤቴን፡ ይፈልጋሉ፤

ወይገይሡ፡ ኀቤየ፤

በጸሎት፡ ወደኔ፡ ይገሰግሳሉ፤

ወይብሉ፡ ንዑ፡ ንሑር፡ ወንትመየጥ፡ ኀበ፡ እግዚአብሔር፡ አምላክነ፤

ከመሄዳቸው፡ አስቀድመው፡ በሕግ፡ በአምልኮት፡ ወደፈጣ ሪያችን፡ ኑ፡ እንሂድ፡ ይላሉ፤

www.ethiopianorthodox.org

፪፤ እስመ፡ ውእቱ፡ ቀሠፈነ፤

በመከራ፡ ገርፎናልና፡ ይኸነን፡ አይሻውም፤

ወይፌውሰነ፤

ያድነናልና፡ ኑ እንሂድ፡ ይላሉ፤

ወውእቱ፡ አቍሰለነ፤

ከዚህ፡ አስቀድሞ፡ እሱ፡ መከራ፡ አመጣብን፤

፫፤ ወይሜርየነ፡ ወያሐይወነ፡ በሰኑይ፡ መዋዕል፤

በሁለተኛው፡ ትውልድ፡ ፈጽሞ፡ ያድነናል፤ በእስራኤል፡ የቆጠሩ፡ እንደሆነ፡ በኢኮንያን፡ ተማርከዋል፤ የተማረከብትን፡ አይሻም፤ በሰላትያል፡ ተስፋ፡ ሰምተው፡ በዘሩባቤል፡ ወጥተዋል፤ በአሕዛብ፡ የቆጠሩ፡ እንደሆነ፡ በናቡከደነፆር፡ ተማርከዋል፤ የተማረኩበትን፡ አይሻም፤ በኤልማሮዴቅ፡ ተገዝተው፡ በብልጣሶር፡ ወጥተዋል፤

ወአመ፡ ሣልስት፡ ዕለት፡ ንትነሣእ፡ ወነሐዩ፡ በቅድሜሁ፤

በሦስተኛው፡ ትውልድ፡ በረድኤት፡ ተነሥተን፡ በፊቱ፡ እንቆማለን፤ አሁን፡ የተማረኩበትን፡ ጨምሮ፡ መቍጠሩ፡ ነው፤ አንድም፡ ወይቤሉ፡ ንዑ፡ ንሑር፡ ብለህ፡ መልስ፤ ምዕመናን፡ ሁሉ፡ ኑ፡ ወደ፡ እግዚአብሔር፡ እንመለስ፡ ይላሉ፤ አምስት፡ ሽህ፡ ካምስት፡ መቶ፡ ዘመን፡ በመከራ፡ ገርፎናልና፡ ከዚህ፡ በኋላ፡ በሁለተኛው፡ ቀን፡ ያድነናል፤ ሙስና፡ መቃብርን፡ ያጠፋልን፡ ቅዳሜ፡ ነውና፡ ዓርብ፡ ሥጋውን፡ ቈርሶ፤ ደሙን፡ አፍስሶ፡ ዓለሙን፡ አድኗል፤ በአካለ፡ ነፍስ፡ ሲያል፡ ወርዶ፡ ነፍሳትን፡ ከሲያል፤ አውጥቷል፤ ቅዳሜ፡ በመቃብር፡ ስኩብ፡ ሁኖ፡ ሙስና፡ መቃብርን፡ አጥፍቶልናል፤ በሦስተኛው፡ ቀን፡ ተነሥተን፡ በፊቱ፡ እንቆማለን፤ በእሱ፡ ትንሣኤ፡ የእኛ፡ ትንሣኤ፡ ስለታወቀ፤

ናእምር፡ ወንዴግን፡ ከመ፡ ናእምሮ፡ ለእግዚአብሔር፤

አምልኮቱን፡ እናውቃለን፡ እንከተላለን፡ ሕጉን፡ በመጠበቅ፡ እግዚአብሔርን፡ እናውቀው፡ ዘንድ፤

ከመ፡ ጎሕ፡ ድልወ፡ ንረክቦ፤

እንደ፡ ጎህ፡ ደስ፡ በማሰኘት፡ እናገኘዋለን፤

ወይመጽእ፡ ከመ፡ ዝናመ፡ ክረምት፡ ዘቀዳሚ፡ ወዘደኃሪ፡ ላዕለ፡ ምድር፤

ዘቀዳሚ፤ የግንቦት፡ የሰኔ፤

ዘደኃሪ፤

የሐምሌ፡ የነሐሴ፡ ዝናም፡ ደስ፡ እንዲያሰኝ፡ ደስ፡ በማሰኘት፡ ወደዚህ፡ ዓለም፡ ይመጣል፤ አንድም፡ ዘቀዳሚ፡ በሀገራቸው፡ የኅዳር፡ የታኅሣሥ፤ ወዘደኃሪ፡ የጥር፡ የየካቲት፡ ዝናም፡ ነው፤



፬፤ ምንተ፡ እግበር፡ ለከ፡ ኤፍሬም፤

ብከ፡ ሲል፡ ነው፤ ኤፍሬም፡ ምን፡ ያላደረግሁብህ፡ አለና፡ ምን፡ ላድርግብህ፤

ወምንተ፡ እግበር፡ ለከ፡ ይሁዳ፤

ብከ፡ ሲል፡ ነው፡ ይሁዳ፡ ምን፡ ያላደረግሁብህ፡ አለና፡ ምን፡ ላድርግብህ፤

ወናሁ፡ ሣህልክሙ፡ ከመ፡ ደመና፡ ነግህ፤

እነሆ፡ ይቅርታችሁ፡ የነግህ፡ ደመና፡ እንዲጠፋ፡ ጠፍቷል፤

ወከመ፡ ጠለ፡ ጽባሕ፡ እንተ፡ ተሐልፍ፡ ፍጡነ፤

ፀሐይ፡ በወጣ፡ ጊዜ፡ የማለዳ፡ ጠል፡ ፈጥኖ፡ እንዲጠፋ፡ ጠፍቷል፤ ምን፡ ያላደረግሁብህ፡ አለና፡ ምን፡ ላድርግብህ፤ አንድም፡ ምንተ፤ እግበር፡ ለከ፡ ብለህ፡ መልስ፤ ኤፍሬም፡ ምን፡ ያላደረግሁልህ፡ አለና፡ ምን፡ ላድርግልህ፤ ይሁዳ፡ ምን፡ ያላደረግሁልህ፡ አለና፡ ምን፡ ላድርግልህ፤ እነሆ፡ ይቅርታችሁ፡ የነግህ፡ ደመና፡ የማለዳ፡ ጠል፡ ደስ፡ እንዲያሰኝ፡ ደስ፡ የሚያሰኝ፡ ሁኗል፤ ምን፡ ያላደረግሁላችሁ፡ አለና፡ ምን፡ ላድርግላችሁ፤

፭፤ በእንተ፡ ዝንቱ፡ አፀድክዎሙ፡ ለነቢያቲክሙ፡ ወቀተልክዎሙ፡ በቃለ፡ አፉየ፤

ስለዚህ፡ ነገር፡ ነቢያተ፡ ጽድቅን፤ አንድም፡ ነቢያተ፡ ሐሰትን፡ አዝገፎ አጠፋኋቸው፤

ወይመጽእ፡ ፍትሕየ፡ ከመ፡ ብርሃን፤

ክብሬ፡ ረድኤቴ፡ ብርሃን፡ ደስ፡ እንዲያሰኝ፡ ደስ፡ በማሰኘት፡ ይመጣል፤

፮፤ እስመ፡ ምጽዋተ፡ አበድር፡ እምነ፡ መሥዋዕት፤

ከመሥዋዕት፡ ምጽዋትን፡ እወዳለሁና፤

ወአእምሮ፡ እግዚአብሔር፡ እምነ፡ ቍርባን፤

ከቍርባንም፡ እግዚአብሔርን፡ ማወቅ፡ ይበልጣልና፤ ይህን፡ ብታደርጉ፡ ረድኤቴ፡ ይመጣላችኋል፤

፯፤ ወእሙንቱሰ፡ ኮኑ፡ ከመ፡ ብእሲ፡ ዘየዓሉ፡ መሐላሁ፤

እነዚህ፡ ግን፡ መሐላውን፡ እንደሚያፈርስ፡ እንደማናቸውም፡ ሰው፡ ሆኑ፤ አንድም፡ እንደ፡ ስምዖንና፡ እንደ፡ ሌዊ፡ ሆኑ፤

ወበህየ፡ ክህዱኒ፤

ምሎ፡ በሚክድ፡ ሰው፡ አምሳል፤ አንድም፡ በነገሩ፤ አንድም፡ በሌዊና፡ በስምዖን፡ አምሳል፡ ካዱኝ፤

www.ethiopianorthodox.org

፰፤ ገለአድ፡ ሀገር፡ እንተ፡ ትትጌበር፡ ከንቶ፡ ትትሐመግ፡ በደም፤

ማያ፡ ለገለዓድ፡ ሲል፡ ነው፤ ከንቱ፡ ጣዖትን፡ የምትሠራ፡ የገለዓድ፡ ውሃዋ፡ በደም፡ ይታለሳል፤

እነ፡ ናቡከደነፆር፡ ተቀራደው፡ አልቀውባት፤ አንድም፡ ተዋግተውባት፡ አገሪቱ፡ በደም፡ ትታለሳለች፤

ወኃይላኒ፡ ከመ፡ ብእሲ፡ ግዱድ፤

ብርቱ፡ የነበረው፡ ኃይሏ፡ ይማስን፡ ያለበት፡ ነው፤ ደካማ፡ ይሆናል፤ ፈረስ፡ ገይድ፡ እንዲል፤ አንድም፡ ደካማ፡ የነበረው፡ ኃይሏ፡ ብርቱ፡ ይሆናል፤

፱፤ ካህናትሰ፡ ኀሉፋነ፡ ፍኖት፡ ከበቱ፡ ፍኖተ፡ እግዚአሙ፤

ከሶርያ፡ ወደከነዓን፡ የሚሄዱ፡ ስምዖንና፡ ሌዊ፡ በሌዊ፤ ስምዖንን፡ አስጠግቶ፡ መናገር፤ ነው፤ የጌታቸውን፡ ሕግ፡ አፈረሱ፤

አመ፡ ቀተልዋ፡ ለሰቂማ፤

ሰቂማን፤ በወንት፡ ጊዜ፤

እስመ፡ ዓመፃ፡ ገብሩ፡ በቤተ፡ እስራኤል፤

ሴኬምና፡ ኤሞር፡ በእስራኤል፡ ታሪክ፡ ላይ፡ ግፍ፡ አድርገዋልና፤ ታሪክ፡ ይኸስ፡ እንደምነው፡ ቢሉ፡ ያዕቆብ፡ ከሶርያ፡ ወደ፡ ከነዓን፡ ሲመለስ፡ ሰቂማ፡ ደረሰ፤ አሕዛብ፡ በዓል፡ አድርገው፡ አገኘ፤ ባሥራ፡ ሁለቱ፡ ነገድ፡ መካከል፡ የተወለደች፡ ዲና፡ የምትባል፡ ነበረች፤

ወወጽአት፡ ከመ፡ ትርአይ፡ ግዕዛ፡ ለሀገር፡ ይላል፤ አሕዛብ፡ ዘፈን፡ አዋቆች፡ ናቸው፡ ይባላሉና፡ ዘፈን፡ ልታይ፡ ወጣች፤ ሴኬም፡ ወልደ፡ ኤሞር፡ ነጥቆ፡ ወስዶ፡ ከክብር፡ አሳነሳት፡ መልከመልካም፡ ውብ፡ ነበረችና፡ ወደዳት፤ ኤሞር፡ ሄዶ፡ ልጄ፡ ልጃችሁን፡ ወዷታልና፡ ሚስት፡ ትሆነው፡ ዘንድ፡ ያዕቆብን፡ ልጅህን፡ ስጠኝ፡ አለው፤ ልጆቹ፡ አልነበሩምና፡ ልጆቼ፡ ሲመጡ፡ መክሬ፡ እነግርሃለሁ፡ አለው፤ ለልጆቹ፡ ነገራቸው፡ ልጆቹም፡ ግዙራን፡ ከቆላፋን፡ ጋራ፡ አትጋቡ፡ ብሎናል፡ እንጂ፡ ከተገዘሩማ፡ ምን፡ ከፋን፡ አሉ፤ ሴኬም፡ የሀገር፡ ቀንድ፡ ነበርና፡ የሀገሩን፡ ሰው፡ ሁሉ፡ ይዞ፡ ተገዘረ፤ ቍስል፡ ከዕለቱ፡ በማግሥቱ፤ ከማግሥቱ፡ በሣልስቱ፡ ይጸናልና፡ ስምዖንና፡ ሌዊ፡ ተታቢያሙ፡ ይላል፤ አይዞህ፡ አይዞህ፡ ተባብለው፡ አፋ፡ አፋቸውን፡ ታጥቀው፡ ገብተው፡ አጥፍተዋቸዋልና፡ እንዲህ፡ አለ፤ ይኸንስ፡ ዕዳ፡ አላለባቸውም፤ አንድም፡ ወበእንተዝ፡ ተኀርየ፡ ዘርዓ፡ ሌዊ፡ ለክህነት፡ ይላል ብሎ፡ ከሶርያ፡ ወደ



ከነዓን፡ የሚሄዱ፡ ስምዖንና፡ ሌዊ፡ ስለሕግ፡ ብለው፡ ሕግን፡ አፈረሱ፤ እነዚያ፡ ኢትዘሙን፡ ቢያፈርሱ፡ ኢትቅትልን፡ አፈርሰዋልና፡ ሰቂማን፡ በወንት፡ ጊዜ፡ ሴኬምና፡ ኤሞር፡ በእስራኤል፡ ላይ፡ ግፍ፡ አድርገዋልና፤ አንድም፡ ከግብፅ፡ ወደ፡ ከነዓን፡ የሚሄዱ፡ ካህናት፡ የጌታቸውን፡ ሕግ፡ አፈረሱ፤ ሰቂማን፡ በወንት፡ ጊዜ፡ በእስራኤል፡ ላይ፡ ግፍ፡ አድርገዋልና፡ በኢያሱ፡ ጊዜ፤ ምንም፡ ብዙ፡ ባያጠፉ፡ ጥቂት፡ ጥቂት፡ አጥፍተዋልና፤ አንድም፡ ቀሚሳቸውን፡ አንጽተው፤ ሰናፊላቸውን፡ አንሰርተው፡ ከተማ፡ ለከተማ፡ የሚዞሩ፡ ካህናት፡ የጌታቸውን፡ ትእዛዝ፡ አፈረሱ፤ ምከሩ፡ አስተምሩ፡ ያላቸውን፡ ምዕመንን፡ በነፍስ፡ በኅዲት፡ ጊዜ፡ በእስራኤል፡ ዘነፍስ፡ ላይ፡ ግፍ፡ አድርገዋልና፤

፲፤ ወርኢኩ፡ በሀየ፡ ዝሙተ፡ ኤፍሬም፡ ግሩመ፤

በልቡና፡ ግሩም፡ የሆነ፡ የኤፍሬምን፡ ክፉ፡ ሥራውን፡ አየሁ፤

ወርኵሰ፡ እስራኤል፤

የእስራኤልን፡ ጣዖቱን፡ አየሁ፤

፲፩፤ ወይሁዳሰ፡ አኃዘ፡ መቅሰሞ፡ ለከ፡ አመ፡ መጠውኩከ፡ ዜዋ፡ እስራኤል፡ ሕዝብየ፤

ወገኔ፡ አሥሩ፡ ነገድ፡ አንተን፡ ለምርኮ፡ በሰጠሁህ፡ ጊዜ፡ ሁለቱ፡ ነገድ፡ እንግዲህ፡ ወዲህ፡ መከራ፡ የለብንም፤ መከራ፡ በአሥሩ፡ ወገን፡ አለፈ፡ እያለ፡ ሟርቱን፡ ያዘ፤ አንድም፡ ማዕፀደ፡ ይላል፤ ያሥሩን፡ ነገድ፡ አዝመራ፡ ለመሰብሰብ፡ ማጭዱን ያዘ፡፡

## - ምዕራፍ ፯ -

፩፤ ወሶበ፡ ሰፋሕክም፡ ለእስራኤል፡ ትትከሠት፡ ዓመፃሁ፡ ለኤፍሬም፤

እሥራኤል፡ እጁን፡ ዘርግቶ፡ እንዲማረክ፡ ባደረግሁት፡ ጊዜ፡ የኤፍሬም፡ በደሉ፡ ትገለጻለች፤

ወእከያ፡ ለሰማርያ፤

የሰማርያምም፡ ክፋቷ፡ ይገለጣል፤

እስመ፡ ሐሰተ፡ ገብሩ፤

ሐሰት፡ ጣዖትን፡ አምልከዋልና፤

ወያበውእ፡ ሰራቂ፡ ኀቤሁ፤

ሌባውን፡ ወደኔ፡ ግባ፡ አንተ፡ ስረቅ፡ እኔ፡ ላጥልቅ፡ ይለዋል፤

ይስእል፡ ወይሰልብ፡ በፍኖት፤

በጐዳና፡ ይለምናል፤ የቅሚያ፡ መዠመሪያ፡ ልመና፡ ነውና፡ እስኪ፡ ዘንግህን፡ በዘንጌ፡ ብትርህን፡ በብትሬ፡ ለውጠኝ፡ ይለዋል፤ አንድም፡ ከጣዖቱ፡ ይለምናል፤ በጐዳና፡ ይቀማል፤ አንድም፡ ደካማውን፡ ይቀማል፤ ብርቱውን፡ ይለምናል፤

www.ethiopianorthodox.org

፪፤ ከመ፡ ይኅበር፡ ማዕሌቶሙ፤

ያሥሩ፡ ነገድ፡ ወንጀላቸው፡ ከሁለቱ፡ ነገድ፡ ይተባበር፡ ዘንድ፤ አንድም፡ የንጉሡ፡ ወንጀል፡ ከሠራዊቱ፡ ይተባበር፡ ዘንድ፤

ወአእመርኩ፡ ኵሎ፡ እከዮሙ፤

በልቡናቸው፡ ያሰቡትን፡ አወቅሁ፤

ወይእዜኒ፡ የአግቶሙ፤

ኃጢአታቸው፡ በመከራ፡ ይከ ባቸዋል፤

ወተዘከርኩ፡ ኵሎ፡ እከዮሙ፤

ክፋታቸውን፡ ሁሉ፡ አሰብሁ፤

ወጌጋዮሙ፡ በቅድመ፡ ገጽየ፡ ኮኖሙ፤

ኃጢአታቸው፡ በፊቴ፡ ለማስ ማረክ፡ አበቃቸው፤ አንድም፡ እንግዲህ፡ ወዲህ፡ ኃጢአት፡ አይ ሠሩም፡ ተማርከው፡ ይሄዳሉ፤

፫፤ ወተፈሥሑ፡ ነገሥት፡ በእ ከዮሙ፤

ነገሥታቱ፡ በክፋታቸው፡ ደስ፡ አላቸው፤ አንድም፡ በሠራዊቱ፡ ክፋት፡ ደስ፡ አላቸው፤

ወመላእክትኒ፡ በሐሰቶሙ፤

አለቆችም፡ ሐሰት፡ በመናገራ ቸው፡ ደስ፡ አላቸው፤

፬፤ እስመ፡ ኵሎሙ፡ የሐውሩ፡ ኀበ፡ ብእሲተ፡ ብእሲ፤

ሁሉም፡ ወደጐልማሳ፡ ሚስት፡ ይሄዳሉና፤

ከመ፡ ዕቶን፡ ዘአንደዱ፡ ለሐቢዝ፡ ዘያ ንበለብል፡ ነዱ፡ እምሐሪፅ፡ ዘልውስ፡ እስከ፡ ይትበነእ፤

ከዱቄት፡ ወገን፡ የተለወሰውን፡ ለመጋገር፡ ያነደዱት፡ እሳት፡ ነዶ፡ ነዶ፡ እንዲያልቅ፡ መዓት፡ መቅሠፍት፡ ያልቅባቸዋል፤ አንድም፡ ከዱቄት፡ ወገን፡ የተ ለወሰውን፡ ለመጋገር፡ እስኪ ቦካ፡ ያነደዱት፡ እሳት፡ እንዲ ያበራ፡ ጊዜው፡ ጥቂት፡ እን ደሆነ፤

፭፤ መዋዕለ፡ ነገሥቶሙ፤

የነገሥታቱ፡ ዘመን፡ ጥቂት፡ ነው፤

ወአኃዙ፡ መላእክት፡ ይትመዓዑ፡ እምወይን፤

ወይን፡ አጥተው፤ አንድም፡ ወይን፡ ጠጥተው፡ አለቆች፡ ይበሳጩ፡ ጀመረ፤

ወሰፍሐ፡ እደዊሆሙ፡ ምስለ፡ ስሁላን፤

ከተገዳዳሮች፡ ከተቀጣጣቦች፡ ጋራ፡ እጃቸውን፡ ዘረጉ፤

፮፤ እስመ፡ ነደ፡ ልቦሙ፡ ከመ፡ ዕቶን፡ ሶበ፡ ነጽሐሙ፡ ኵሎ፡ ሌሊተ፤

ሌሊቱን፡ ሁሉ፡ በመከራ፡ በጣ ላቸው፡ ጊዜ፡ ልቡናቸው፡ እንደ፡ እሳት፡ ተናዷልና፤ ወይን፡ የገ ደለውን፡ ወይን፡ ያድነዋል፡ ብለው፡ ጠጥተው፡ ለማጨብ ጨብ፤ ሰፍሐ፤ እጃቸውን፡ ዘረጉ፤



ኤፍሬም፡ ፀግበ፡ ወኖመ፡ ኵላ፡ ሌሊተ፤

ኤፍሬም፡ ጠግቦ፡ ሌሊቱን፡ ምሉ፡ ተዘክሮተ፡ እግዚአብ ሔር፡ ጠፍቶበት፡ ተዘርሮ፡ (ተገልብጦ)፡ አደረ፤

ወሶበ፡ ነቅሐ፡ በጽባሕ፡ ነዱ፡ ከመ፡ ነበ ልባለ፡ እሳት፡ ወኵሎሙ፡ ውዕየ፡ ከመ፡ ዕቶን፡ ልቦሙ፤

ማለዳ፡ በተነሱ፡ ጊዜ፡ ሁሉም፡ እንደ፡ እሳት፡ ነደዱ፤ ልቡና ቸው፡ እንደ፡ እሳት፡ ነደደ፤ ወይን፡ አብዝቶ፡ የጠጣ፡ ሰው፡ በነጋው፡ ልቡ፡ ይቃጠላልና፤

፯፤ ወበልዓቶሙ፡ እሳት፡ ለመኳ ንንቲሆሙ፤

መኳንንቱንም፡ መዓት፡ መቅ ሠፍት፡ አጠፋቻቸው፤

ወወድቁ፡ ኵሎሙ፡ ነገሥቶሙ፤

ነገሥታቱ፡ ሁሉ፡ ጠፉ፤

ወአልቦ፡ እምኔሆሙ፡ ዘይጼውዓኒ፤

ከነዚህ፡ ሁሉ፡ እኔን፡ አድነኝ፡ ብሎ፡ የሚለምነኝ፡ የለም፤

፰፤ ኤፍሬም፡ ተደመረ፡ ምስለ፡ ሕዝቡ፤

ንጉሡ፡ ከሠራዊቱ፡ ጋራ፡ ኃጢ አት፡ በመሥራት፡ አንድ፡ ሆነ፤ አንድም፡ ኤፍሬም፡ ተደመረ፡ ምስለ፡ ዘማውያን፤ ኤፍሬም፡ ከዘማውያን፡ ጋር፡ አንድ፡ ሆነ፤

ኤፍሬም፡ ኅቡዓቲከ፡ ገፍትዓተከ፤

ኤፍሬም፡ ሠውረህ፡ የሠራ ሃት፡ ኃጢአትህ፡ አጠፋችህ፤ አንድም፡ ተገፍትአት፡ ብከ፤ ሠውረህ፡ የሠራሃት፡ ኃጢአ ትህ፡ ተገለጠችብህ፤ አንድም፡ ኤፍሬም፡ ቅቡር፡ ኅብስት፡ ይላል፤ ኤፍሬም፡ የተቀበረ፡ አምባሻ፡ ነው፤ ያ፡ በውስ ጥም፡ በላይም፡ እንዲነድበት፡ በነፍስም፡ በሥጋም፡ መዓት፡ መቅሠፍት፡ ይመጣበታል፤

፱፤ ወበልዓ፡ ፀር፡ ኃይሎ፤

ስልምናሶር፡ ናቡከደነፆር፡ ሠራ ዊቱን፡ አጠፋ፤ አንድም፡ ባለጸ ግነቱን፡ አጠፋ፤

ወውእቱስ፡ ኢያእመረ፤

እሱ፡ ግን፡ አላወቀም፤

ወበቈልስ፡ ሲበቲሂ፡ ውስተ፡ ገጹ፤

ሕፃን፡ አእምሮ፡ ነው፡ እንዳል ሰው፡ በፊቱ፡ ሽበት፡ በቀለ፤

ወዓዲ፡ ኢለበወ፤

ዳግመኛም፡ ልብ፡ አላደረገም፤

፲፤ ወየኃሥርዎ፡ ወይጼእልዎ፡ ቅድመ፡ ገጹ፡ ለእስራኤል፤

እስራኤልን፡ ፊት፡ ለፊት፡ ይሰ ድቡታል፡ ያዋርዱታል፤

ወኢተመይጡ፡ ኀበ፡ እግዚአብሔር፡ አምላኩ፤

ወደፈጣሪው፡ ወደ፡ እግዚአብ ሔር፡ አልተመለሰም፤

www.ethiopianorthodox.org

ወበዝንቱ፡ ኵሉ፡ ኢኃሠሥዎ፡ ለእግዚአብሔር፤

በዚህ፡ ሁሉ፡ እግዚአብሔርን፡ በአምልኮት፡ አልፈለጉትም፤

፲፩፤ ወኮነ፡ ኤፍሬም፡ ዓብደ፡ ከመ፡ ርግብ፤

ኮነ፤ ያለውን፡ ዓብደ፡ ብሎ፡ አመጣው፤ ኤፍሬም፡ እንደ፡ ርግብ፡ ሰነፈ፤ ርግብ፡ እንቍላሏን፡ ቢያፈርጡባት፡ ቤቷን፡ ካላፈረሱባት፡ ቦታዋን፡ አትለቅም፤

ወኮነ፡ ከመ፡ ዘአልቦ፡ ልብ፤

አእምሮ፡ እንደሌለው፡ ሰው፡ ሆነ፤

ለግብፅ፡ ይጼውዖሙ፤

ስንፍናው፡ ይህ፡ ነው፤ ግብፃውያንን፡ እርዱኝ፡ እያለ፡ ይልካል፤

ወኀበ፡ ፋርስ፡ የሐውሩ፤

ግብፅን፡ እርዱን፤ ፋርስን፡ እንገብር፡ እንዳሉ፡ ጦር፡ አመጣባቸዋለሁና፡ እንገብር፡ እንቀቅል፡ እያሉ፡ ወደፋርስም፡ ይሄዳሉ፤

፲፪፤ ወበከመ፡ የሐውሩ፡ ከማሁ፡ እዌሩ፡ ላዕሌሆሙ፡ መሥገርትየ፤

እንደ፡ ሄዱ፡ መጠን፡ መዓቴን፡ አመጣባቸዋለሁ፤

ከመ፡ አዕዋፈ፡ ሰማይ፡ አወርዶሙ፤

ነፍጠኛ፡ ዖፍን፡ ከዓየር፡ እንዲያወርድ፡ አወርዳቸዋለሁ፤

ወእቀሥፎሙ፡ ዕዘኒሆሙ፡ በምንዳቤሆሙ፤

በመከራቸው፡ ጊዜ፡ ጆሮ፡ ጆሮዋቸውን፡ በአኵርባጅ፡ እየገረፉ፡ እንዲወስዷቸው፡ አደርጋለሁ፤ መከራ፡ በጆሮ፡ ይጸናልና፤ አንድም፡ ገዶ፡ ጕብሮ፡ እንዲሏቸው፡ አደርጋለሁ፤

፲፫፤ አሴ፡ ሎሙ፡ እስመ፡ ነገዱ፡ እምኔየ፡ ድንጉፃኒሆሙ፡ እሙንቱ፤

የደነገጡ፡ ሁነው፡ ከኔ፡ ተለይተው፡ ሄደዋልና፡ ወዮላቸው፤

እስመ፡ አበሱ፡ ላዕሌየ፤

እኔን፡ ስለበደሉ፤

ወአንሰ፡ አድኃንክዎሙ፤

እኔ፡ አዳንኋቸው፤

ወእሙንቱሰ፡ ሐመዩኒ፡ በሐሰት፤

እነሱ፡ ግን፡ መና፡ ከደመና፡ ውሀ፡ ከደንጊያ፡ አፍልቄ፡ ብመግባቸው፡ ይህ፡ እንደምን፡ ይቻላል፡ ብለው፡ አሙኝ፤ አንድም፡ ዕሩቅ፡ ብእሲ፡ አሉኝ፤

፲፬፤ ወኢጸርሑ፡ ኀቤየ፡ በልቦሙ፡ ዳዕሙ፡ ይገዕሩ፡ በውስተ፡ ምስካቦሙ፤

በልቡናቸው፡ ከኔ፡ ዘንድ፡ አለመኑም፤ በመኝታቸው፡ ሳሉ፡ ይጮሃሉ፡ እንጂ፤

በእንተ፡ እክል፡ ወወይን፡ ወቅብዕ፡ ተቀትሉ፤

ወይ፡ እህል፡ በልተን፤ ወይ፡ ወይን፡ ጠጥተን፡ ወይ፡ ዘይት፡ ተቀብተን፡ እያሉ፡ ሞቱ፤



፲፭፤ ወኢተገሠጹ፡ በኀቤየ፤

በኔ፡ ዘንድ፡ አልተመከሩም፤

ወአነ፡ አጽናዕኩ፡ መዝራዕትየ፡ ከመ፡ እግበር፡ እኩየ፡ በላዕሌሆሙ፤

እኔም፡ በነሱ፡ ላይ፡ ክፉ፡ ነገር፡ አደርግ፡ ዘንድ፡ ሥልጣኔን፡ አጸናሁባቸው፤

፲፮፤ ወተመይጡ፡ ውስተ፡ ከንቱ፤

ወደከንቱ፡ ነገር፡ ተመለሱ፤

ወኮኑ፡ ከመ፡ ቀስት፡ ጠዋይ፤

እንደጠማማ፡ ነፍጥ፡ ሆኑ፤ ነፍጥ፡ ቢንር፡ የጌታውን፡ ጎን፡ ይሰብር፡ እንዲሉ፤ አንድም፡ እንደ፡ ደጋን፡ ሆኑ፤ አንድም፡ እንደ፡ ባሕር፡ ቀስት፡ ሆኑ፤ የባሕር፡ ቀስት፡ ሲይዙት፡ ይሰበሰባል፤ ሲተዉት፡ ይበተናል፤ እነዚህም፡ ሲይዛቸው፡ እንወድሃለን፡ እናመልክሃለን፡ ይሉታል፤ ሲተዋቸው፡ እሱን፡ ትተው፡ ወደ ኃጢአት፡ ወደጣዖት፡ ይሄዳሉ፤

ወይወድቁ፡ መላእክቲሆሙ፡ በኵናት፡ በእንተ ዕበደ፡ ልቦሙ፡ ወልሳኖሙ፤

በአንደበታቸው፡ ከፉ ስለተናገሩ፡ በልቡናቸው፡ ክፉ ስለአሰቡ፡ አለቆቻቸው፡ ይጠፋሉ፤

ከማሁ፡ አበሳሆሙ፡ ወከመ፡ ፃማሆሙ፡ በምድረ፡ ግብፅ፡ ውስተ፡ ሕፅኖሙ፡ ከመ፡ መሬት፤

በግብፅ፡ ሳሉ፡ ይሠሩት፡ እንደ ነበሩ፡ መጠን፡ ጣዖቱ፡ እንደ መሬት፡ በዝቶ፡ በአጠገባቸው፡ አለ፡፡

## - ምዕራፍ ፰ -

፩፤ ወከመ፡ ንስር፡ ውስተ፡ ቤተ፡ እግዚአብሔር፡

በቤተ፡ እግዚአብሔር፡ እንዳለ፡ ሥዕለ፡ ንስር፡ ምናሴ፡ ባምስቱና፡ በስድስቱ፡ ቆመ፡ ብእሲ፡ መካከል፡ ሥዕለ፡ ንስር፡ አቁሞ፡ ነበርና፡

እስመ፡ ዓለዉ፡ ኪዳንየ፤

መሐላዬን፡ አፍርሰዋልና፤

ወአበሱ፡ ላዕለ፡ ሕግየ፡ ይኬልሑ፡ ኀቤየ፤

ሕጌንም፡ አልጠበቁምና፡ ከኔ፡ ዘንድ፡ ይጮሃሉ፤

፪፤ ወይብሉኒ፡ አእመርናከ፡ እግዚኦ፤

አቤቱ፡ በሕግ፡ በአምልኮት፡ እናውቅሃለን፡ ይሉኛል፤

እስመ፡ እስራኤል፡ አግብዓ፡ ሠናይቶ፤

እስራኤል፡ እንተ፡ ትውኅዝ፡ ሀሊበ፡ የሚላት፡ ኢየሩሳሌምን፡ አሳልፎ፡ ለአሕዛብ፡ ሰጥቷታልና፤ አንድም፡ ወለጠ፡ ግዕዞ፡ ይላል፡ ግብሩን ለወጠ፤

፫፤ ወዴገኑ፡ ፀሮሙ፤

የሚገዛን፡ ንጉሥ፡ አንግሥልን አሉ፤

ወነግሡ፡ ለርእሶሙ፤

በራሳቸው፡ ነገሡ፤ ሳኦልን፡ ቢያነግሥላቸው፡ ካነገሠማ፡ ትንቢት፡ ከተነገረለት፡ ከይሁዳ፡

www.ethiopianorthodox.org

ባላነገሠልንም፡ ነበር፡ አሉ፤ አን ድም፡ አንግሥ፡ ለነ፡ ማለት፡ ጌታ፡ አይንገሥብን፡ ማለት ነውና፤

፬፤ ወአኮ፡ በእንቲአየ፡ ዘወጠኑ፣

ይህን፡ ያሉት፡ እኔን፡ ደስ፡ ይበለው፡ ብለው፡ አይደለም፤

ወኢያእመሩኒ፣

በአምልኮት፡ አላወቁኝም፤

ወገብሩ፡ ሎሙ፡ አማልክተ፡ ወርቆሙ፡ ወብሩሮሙ፣

ወርቁን፡ ብሩን፡ ጣዖት፡ አድር ገው፡ ሠሩት፤

ከመ፡ ይሠረዉ፡ ቦቱ፣

በሱ፡ ምክንያት፡ ይጠፉ፡ ዘንድ፤

ጉባዔ

፭፤ ሚጢ፡ ላህመኪ፡ ሰማርያ፣

ሰማርያ፡ ላምሽን፡ መልሺ፡ ማለት፡ ወርቅ፡ በዪው፣ ወር ቁን፡ በላም፡ አምሳል ይሠሩ ታልና፤ አንድም፡ እንዳይማ ረክ፡ አድርጊው፤ አንድም፡ ማርከው፡ ወስደው፡ ላም፡ ያስ ጠብቋቸዋልና፤

ወተሐውከተ፡ መዓትየ፡ በላዕሌሆሙ፣

መዓቴ፡ በነዚያ፡ ላይ፡ ተነሳሳ ችባቸው፤

እስከ፡ ማዕዜኑ፡ ኢይክሉ፡ ነጺሐ፡ እስራኤል፣

እስራኤል፡ ከኃጢአት፡ መን ጻት፡ የማይቻላቸው፡ እስከ መቼ፡ ድረስ፡ ነው? አንድም፡ ጣዖቱን፡ መተው፡ የማይቻ ላቸው፡ እስከመቼ፡ ድረስ፡ ነው?፤

፮፤ ወውእቱኒ፡ ፀራቢ፡ ገብሮ፡ ወኢኮነ፡ አምላከ፣

ይኸውም፡ እንጨት፡ ጠራቢ፡ የሠራው፡ ነው፤ አምላክ፡ አይደለም፤

እስመ፡ ሳኩዮ፡ ላህምኪ፡ ሰማርያ፣

ሰማርያ፡ ላምሽ፡ ተማርኮ፡ ሲሄድ፡ ተቅበዝብዟልና፡ መልሺ፤ አንድም፡ ማርከው፡ ወስደው፡ ወቄት፡ አላድ፡ እያሉ፡ ተካፍለ ውታልና፤

፯፤ እስመ፡ ዘርዑ፡ ነፋሰ፡ ወዓ ረሩ፡ ዓውሎ፣

ነፋስ፡ ዘርተዋልና፣ አውሎን፡ ለቅመዋልና፡ ጣዖት፡ ባመለኩ በት፡ ወራት፡ የሚያገኙትን፡ ነፋስ፡ መዝራት፡ ዓውሎ፡ መል ቀም፡ አለው፤

ወአልቦ፡ ሎሙ፡ ኃይል፡ ለከላስስ ቲሆሙ፣

ለነዶዋቸው፡ ፍሬ፡ የለውም፤



ወኢይወጽእ፡ ሐሪጽ፡ እምውስቴቱ፣

ከውስጡም፡ ዶቄት፡ አይገኝም፤

እመሂ፡ ወጽአ፡ ፀር፡ ይበልዖ፣

ጥቂትም፡ ቢገኝ፡ ናቡከደነፆር፡ ያጠፋዋል፤ አንድም፡ እስመ፡ ዘርዑ፡ ብለህ፡ መልስ፣ ጣዖት፡ አምልከዋልና፡ ለጣዖቱ፡ ካቀ ረቡት፡ መሥዋዕት፡ ጸሎት፣ ክብር፣ ረድኤት፡ አይገኝበትም፤ ጥቂትም፡ ክብር፡ ቢገኝ፡ ዲያ ብሎስ፡ ያጠፋዋል፤

፰፤ ተሠጥመ፡ እስራኤል፣

እስራኤል፡ በባሕረ፡ መከራ፡ ሠጠመ፣ ተያዘ፤

ወኮነ፡ ከመ፡ ግተት፡ በውስተ፡ አሕ ዛብ፡ ለዘምንትኒ፡ ኢይበቍዕ፣

በአሕዛብ፡ ዘንድ፡ ለምንም፡ ለም ንም፡ እንደማይረባ፡ ግትቻ፡ ሆነ፤ አንድም፡ በዚያወጽኡ፡ ቦቱ፡ እዳው፡ ብሎ፡ በደብሳን፡ መጽ ሐፍ፡ ያመለክታል፣ ጉድፉን፡ ትቢያውን፡ እንደሚያወጡበት፡ ግትቻ፡ ሆነ፤

፱፤ እሙንቱስ፡ ዐርጉ፡ ውስተ፡ ፋርስ፣

እነዚህስ፡ ተማርከው፡ ወደፋርስ፡ ሄዱ፤

ሠረፀ፡ ኤፍሬም፣

ከዚህ፡ አስቀድሞ፡ ኤፍሬም፡ በረድኤት፡ ለመለመ፤

ወኮነ፡ ከመ፡ ዓድግ፡ ገዳም፣

እንደ፡ ምድረ፡ በዳ፡ አህያ፡ ገገር፡ የለኝም፡ አለ፤

ወአፍቀረ፡ ሎቱ፡ አምኃ፣

ውኀብ፡ ያለበት፡ ነው፤ ለጣዖቱ፡ እጅ፡ መንሻ፡ መስጠትን፡ ወደደ፤

፲፤ በእንተ፡ ዝንቱ፡ ይትሜጠውዎ፡ አሕዛብ፤

ስለዚህ ነገር፡ አሕዛብ፡ ማር ከው፡ ይወስዷቸዋል፣ አሳልፌ፡ እሰጣቸዋለሁ፤

ወይሴዕሩ፡ ሕቀ፡ ከመ፡ ይቅብዑ፡ ንጉሠ፡ ወመልአከ፣

ንጉሥ፡ ያነግሡ፡ ዘንድ፡ አለቃ፡ ይሾሙ፡ ዘንድ፣ እጅግ፡ አን ሰው ነበረ፤ ወትሴኰስ፡ ፍቅር፡ እምብዙኃን፡ እንዲል፤

፲፩፤ እስመ፡ አብዝኃ፡ ኤፍሬም፡ መሥዋዕቲሁ፡ ለኃጢአት፣

ኃጢአት፡ ሊሆንበት፤ አንድም፡ ለጣዖቱ፡ ኤፍሬም፡ መሥዋዕ ቱን፡ አብዝቷልና፤

ወገብረ፡ ሎቱ፡ መሥዋዕተ፡ ፍቅር፣

ፍቅር፡ የሚገኝበትን፡ መሥ ዋዕት፡ ለጣዖት፡ አደረገ፤ አን ድም፡ የጌታን፡ መሥዋዕት፡ ለጣ ዖት፡ አደረገ፣ ፍቅር፡ አለው፡ በግብሩ፤ አንድም፡ መሥዋዕተ፡ ፍቁር፡ ይላል፣ የፍቁር፡ የጌ ታን፡ መሥዋዕት፡ ለጣዖት፡ አደረገ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፪፤ ወጸሐፊ: ላዕሌሁ: ፍቅረ፣

ፍቅር: አሳደረበት፣ ወሕገጊሁኒ: ሕጉንም: አሳደረበት፤

እስመ: ለነኪር: ኮነ: መሥዋዕተ: ፍቅር፣

የፍቅር: የጌታ: መሥዋዕት: ለጣዖት: ሆኗልና፤ አንድም: የፍቁር: የእስራኤል: መሥዋ ዕት: ለጣዖት ሆኗልና፤

፲፫፤ እመሂ: ሦዑ: መሥዋዕተ: ወበልዑ: ሥጋ: ኢይትዌከፎሙ: ይቤ: እግዚአብሔር፣

መሥዋዕት: ቢሠዉ: ሥጋውን: ቢበሉ: አልቀበላቸውም: አለ፤

ይእዜ: እዜከር: ሎሙ: ኃጢአቶሙ፣

ዛሬ: ኃጢአታቸውን: አስብባ ቸዋለሁ፤

ወእትቤቀሎሙ: በጌጋዮሙ፣

በኃጢአታቸው: ተበቅዬ: አጠ ፋቸዋለሁ፤

ወእሙንቱሰ: ተመይጡ: ውስተ: ግብፅ፣

እነዚህስ: እርዱን: እያሉ: ወደ ግብፅ: ይሄዳሉ፤ አንድም: በግ ብፅ: ይቀበሉት: የነበረውን: መከራ: ይቀበላሉ፤

ወይበልዑ: ኵስሐ: በፋርስ፣

በፋርስም: መከራ: ይቀበላሉ፤

፲፬፤ ወረሥኦ: እስራኤል: ለፈጣሪሁ፤

እስራኤል: ፈጣሪውን: ዘነጋ፤

ወሐነፃ: ለጤሜን፣

ጤሜን: አምባ: ነው፤ አንድም: መቅደስ: ጣዖት: ናት፣ ጤሜ ንን: ሠራት፤

ወይሁዳኒ: አብዝኃ: አህጉረ: ጥቅም፣

ይሁዳም: ቅጽር: ያላቸው: አም ባዎችን: አበዛ፤

ወእፌኑ: እሳተ: ውስተ: አህጉሪሆሙ: ወትበልዖሙ: መሠረታቲሆሙ፣

በሰዎች: ጦር፤ በሀገሩ: ድርቅ: አመጣለሁ፤ ሥር: መሠረታ ቸውን: ታጠፋለች፤ አንድም: የትሑታኑ: መገኛ: የሚሆኑ: ነገሥታቱን: ታጠፋለች።

## - ምዕራፍ ፱ -

፩፤ ኢትትፈሣሕ: ወኢትትሐሠይ: እስራኤል: ከመ: አሕዛብ፣

እስራኤል: እንደ: አሕዛብ: ፈጽመህ: ደስ: አይበልህ፤

እስመ: ዘመውከ: እምአምላክከ፣

ከፈጣሪህ: ተለይተህ: የማይ ገባ: ሥራ: ሠርተሃልና፤

ወአፍቀርከ: ሀብተ: እምኵሉ: ዓውደ: እክል: ወምክያደ: ወይን፣

ከእህሉ: አውድማ: ከወይኑም: አውድማ: የተገኘውን: ለጣዖቱ: መስጠት: ወደሃልና፤

፪፤ እክልኒ: ኢያእመሮሙ፣

እህሉም: አልበረከተላቸውም፤

ወይንኒ: ሐሰዎሙ: ኀበ: ይነብሩ: ምድረ: እግዚአብሔር፣

በሚኖሩበት: በኢየሩሳሌም: ሳሉ: ወይኑ: አልበረከተላቸውም፤



፫፤ ወነበረ: ኤፍሬም: ግብፀ: በፋ ርስ: እንዘ: ይበልዕ: ኵስሐ፣

በፋርስ: ሳለ: ኤፍሬምም: በግ ብፅ: ኖረ: ማለት: በግብፅ: ይቀ በለው: የነበረውን: መከራ: በፋ ርስ: ይቀበላል፤ አንድም: ቀድሞ: በግብፅ: መከራውን: ሲቀበል: ኖረ፣ ዛሬም: በፋ ርስ: መከራውን: ያያል፤

፬፤ ወኢያወጽሑ: ለእግዚአብሔ ር ወይነ: ወጼተሎ:

ወይነ: የወይን: ጠጅ፣ ወጸተሎ: የማር: ጠጅ፣ የማር: ጠጅስ: በሀገራቸው: የለም፣ ብሎ: ጥሩ: ጠጅ: ጉሽ: ጠጅ፤ አንድም: ወይን: አረቄ: ወጼተሎ፣ ደም: አላቀረቡም፤

ወኢያሠነዩ: ሎቱ: ኅብስቶሙ: ከመ: ኅብስተ: ልሔሞሙ፣

ኅብስትና: ልሔም: የተደራ ረበ: ነው፤ ለእግዚአብሔር: የሚ ያቀርቡትን: መሥዋዕት: ለጣ ዖቱ እንደሚያቀርቡት: መሥ ዋዕት: አላሳመሩትም፤ አን ድም: ከመ: ኅብስተ: ርኵ ሶሙ: ይላል፤

ወኵሉ: ዘይበልኦ: ይረኵስ፣

የበላው: ሁሉ: ኃጥእ: ይባላል፤

እስመ: ኅብስቶሙኒ: ለነፍሶሙ: ወኢ ይበውእ: ቤተ: እግዚአብሔር፣

ኅብስቱ: ለራሳቸው: ነውና: ወደ ቤተ: እግዚአብሔር: አይገባም፤

፭፤ ምንተ: ይገብሩ: በዕለተ: ሕጎሙ፣

ሕግ: በሚሠሩበት: ቀን: ምን: ያደርጋሉ፤ አንድም: በዕለተ: ሐጎሙ: ይላል፤

ሐጌ: ማለት: በዓል: ማለት: እንደሆነ፣ በዓለ: ሠዊትን: በዓለ: መጸለትን፤

ወአመ: ዕለተ: እግዚአብሔር፣

በዓለ: ፋሲካን: በሚያከብሩ በት: ቀን: ምን: ያደርጋሉ፤

፮፤ በእንተ: ዝንቱ: ናሁ: የሐ ውሩ: ከመ: ሐሣሮሙ: ለግብፅ፣

ስለዚህ: ነገር: በግብፅ: ይቀበ ሉት: እንደነበረ: ያለ: መከራ: ይቀበላሉ፤

ወይትሜጠውዎሙ: ሜምፎስ፣

ሜምፎስ: ኃያላኑ፤ አንድም: ቤተ: አይጽ፣ ቤተ: አንኣ: ይቀ በሏቸዋል፤ ሠቃይ: ቆሯጭ: ማለት: ነው፤

ወይቀብርዎሙ: ለምክማስ፣

በአምባው፤ አንድም: በጉድፍ: ይቀብሯቸዋል፤

ወርቆሙ: ወብሩሮሙ: በድበደ፣

ወርቃቸውን፣ ብራቸውን: ለነ ዳያን: አንሰጥም: ብለው: ዛገ፣ ብርን: ሲያይ: ነው: እንጂ: በወ ርቅስ: ዝገት: የለበትም፤

www.ethiopianorthodox.org

ወይወርሶ፡ ሶክ፡ ውስተ፡ አብያቲሆሙ፤

በቀበሩበት፡ ቦታ፡ እሾህ፡ ይበቅልበታል፤

፯፤ በጽሐ፡ መዋዕለ፡ በቀል፡ ወፍዳ፤

በቀልን፡ ፍዳን፡ የምትቀበሉበት፡ ወራት፡ ደረሰ፤

ወይደዊ፡ እስራኤል፡ ምስለ፡ ነቢይ፡ ዘይለብስ፡ መንፈስ፡ ሐሰት፤

እስራኤል፡ ሐሰተኛውን፡ ትንቢት፡ እውነተኛ፡ ከሚያደርግ፡ ከነቢየ ሐሰት፡ ጋራ፡ መከራ፡ ይቀበላል፤

በብዝኃ፡ ጌጋይከ፡ አብዛኅከ፡ ቍጥዓከ፤

በኃጢአትህ፡ ብዛት፡ አንተ፡ የምትቆጣውን፤ አንድም፡ ሌሎች፡ የሚቆጡህን፡ ቁጣ፡ አበዛህ፤

፰፤ ኤፍሬም፡ ሰብአ፡ ዓይን፡ ምስለ፡ ነቢየ፡ እግዚአብሔር፤

ንጉሡ፡ በነቢዩ፡ ጉበኛ፡ ሆነበት፤

መሥገርት፡ እኪት፡ ውስተ፡ ኵሉ፡ ፍናዊሁ፤

በሚሠራው፡ ሥራ፡ ሁሉ፡ ክፉ፡ ሥራ፡ አለ፤

ርኵሶሙ፡ አንበሩ፡ ውስተ፡ ቤተ፡ እግዚአብሔር፤

ጣዖቱን፡ ከቤተ፡ እግዚአብሔር፡ አኖሩ፤ ምናሴ፡ ባምስቱና፡ በስድስቱ፡ ቆመ፡ ብእሲ፤ መካከል፡ ጣዖት፡ ሥዕለ፡ ንስር፡ አቁሞ፡ ነበርና፤

፱፤ ወኃሠሩ፡ ከመ፡ አመ፡ መዋዕለ፡ በዓሊም፤

ጣዖት፡ እንዳመለኩበት፡ እንደ፡ ኤግሎም፡ እንደ፡ ኩሳርስቲም፡ ዘመን፡ ተዋረዱ፤

ወናሁ፡ እዜክር፡ ሎሙ፡ ኃጢአቶሙ፡ ወእትቤቀሎሙ፡ በጌጋዮሙ፤

እነሆ፡ ኃጢአታቸውን፡ አስብባቸዋለሁ፤ በኃጢአታቸው፡ ምክንያት፡ አጠፋቸዋለሁ፤

፲፤ ከመ፡ አስካለ፡ ወይን፡ በገዳም፡ ረከብክዎ፡ ለእስራኤል፤

ከዚህ፡ አስቀድሞ፡ በምድረ፡ በዳ፡ ያለ፡ ወይን፡ ደስ፡ እንዲያሰኝ፡ እስራኤልንም፡ ደስ፡ ለማሰኘት፡ ወደድሁት፤

ወከመ፡ በኵረ፡ በለስ፡ በገዳም፡ ክረምተ፡ ርኢክዎሙ፡ ለአበዊሆሙ፤

በክረምት፡ የተገኘ፡ በኵረ፡ በለስ፡ እንዲወደድ፡ አባቶቻቸውን፡ ወደድኋቸው፤

ወእሙንቱሰ፡ ቦኡ፡ ቤተ፡ ብኤል፡ ፌጎር፤

እነሱ ግን፡ ወደጣዖቱ፡ ቤት፡ ገቡ፡ ቤል፡ ጣዖቱ፡ ነው፤ ፌጎር፡ ጣዖት ማምለክ፡ የጀመረው፡ ሰው፡ ጣዖት፡ ማምለክ፡ የተጀመረበት፡ ቦታ፡ በጣዖት፡ ያደረ፡ ሰይጣን፡ ነው፤

ወተናገሩ፡ ለሐሣሮሙ፤

መከራ፡ ሊመጣባቸው፡ ቤልን፤

ዳኅንን፡ አመሰገኑ፤ አንድም፡ ለጣዖቱ፡ ምስጋና፡ አቀረቡ፡



ወኮኑ፡ ሰቆራረ፡ ፍቁራኒ፡ ኤፍሬም፤

የንጉሡ፡ ባለሟሎች፡ የሚያስጠይፉ፡ ሆኑ፤

፲፩፤ ከመ፡ ዖፍ፡ ሠረረ፡ ክብሮሙ፤

ባለጸግነታቸው፡ እንደ፡ ዖፍ፡ ጠፋ፤ ዖፍ፡ ከበረረ፡ ይያዛልን፤ እንግዲህ፡ ወዲህ፡ ወዮ፡ ምን፡ ያግዛል፡ እንዲሉ፤

ይፀንሱ፡ ኃጢአተ፡ ወይወልዱ፡ ሕማመ፤

ኃጢአት፡ ሠርተው፡ መከራ፡ ይቀበላሉ፤

፲፪፤ ወእመኒ፡ አልሐቁ፡ ውሉዶሙ፡ ያጠፍዕዎሙ፡ እምሰብእ፤

ልጆቻቸውንም፡ ቢያሳድጉ፡ ከሰው፡ ለይተው፡ ማርከው፡ ይወስዷቸዋል፤

ወዓዲ፡ አሌ፡ ሎ፡ ሥጋየ፡ ውእቱ፡ ኤፍሬም፡ ዘእምውስቴቶሙ፡ አነ፤

ዳግመኛ፡ እኔ፡ ከሳቸው፡ ወገን፡ ለምሆን፡ ለኤፍሬም፡ ወዮለት፤

፲፫፤ በከመ፡ ርኢኩ፡ ውስተ፡ ማዕገተ፡ እሳት፡ አስተጋብዑ፡ ውሉዶሙ፤

በጦር፡ ተከበው፡ እንዳየኋቸው፡ ልጆቻቸውን፡ ሰበሰቡ፤

ኤፍሬምኒ፡ አውጽአ፡ ደቂቆ፡ ይርግዝዎሙ፤

ኤፍሬም፡ እየወጉ፡ ይጥሏቸው፡ ዘንድ፡ ልጆቹን፡ አቀረበ፤ እሱ፡ የሚያቀርባቸው፡ ሆኖ፡ አይደለም፤ ማዳን፡ ስለ፡ አልተቻለው፡ ምክንያት፡ ሆኖ፡ ስለአስጠፋቸው፡ እንዲህ፡ አለ፤ ወያመጽእዎሙ፡ ዔዋ፡ እንዲል፤

፲፬፤ ሀቦሙ፡ እግዚኦ፤

አቤቱ፡ ስጣቸው፤

ምንተ፡ ትሁቦሙ፤

ምን፡ ትሰጣቸዋለህ፡ እኔስ፡ ምን፡ ስጣቸው፡ እልሃለሁ?

ሀቦሙ፡ ማሕፀነ፡ መካነ፡ ወአጥባተ፡ ይቡሳተ፤

በመከራ፡ እንዳያዝኑ፡ ፅኑ፡ መከራ፡ አታምጣባቸው፤ አንድም፡ አቤቱ፡ ስጣቸው፡ ምን፡ ትሰጣቸዋለህ? እኔስ፡ ምን፡ ስጣቸው፡ እልሃለሁ? ሀቦሙ፡ ማህፀነ፡ መካነ፡ ወአጥባተ፡ ይቡሳተ፤ በመከራ፡ እንዲያዝኑ፡ አድርጋቸው፤ ያልወለደ፡ አንጀት፡ ያላጠባ፡ ጡት፡ እንዲሉ፤

፲፭፤ ኵሉ፡ እከዮሙ፡ በገልገላ፤

በገልገላ፡ የተደረገው፡ ክፉ፡ ሥራቸው፡ ተፈጸመ፤

እስመ፡ በህየ፡ ጸላእክዎሙ፡ በእንተ፡ እከየ፡ ምግባሮሙ፤

ስለክፉ፡ ሥራቸው፡ ጠልቻቸዋለሁና፤

www.ethiopianorthodox.org

ወእሰድዶሙ፡ እምአብያቲሆሙ፤

ከቤታቸው፡ አስወጥቼ፡ እሰዳቸዋለሁ፤

ወኢይደግም፡ እንከ፡ አፍቅሮቶሙ፤

እንግዲህ፡ ዳግመኛ፡ አልወዳቸውም፤

እስመ፡ ኵሎሙ፡ መላእክቲሆሙ፡ ዓላውያን፤

አለቆቻቸው፡ ሁሉ፡ ወንጀለኞች፡ ናቸውና፤

፲፮፤ ደወየ፡ ኤፍሬም፡ ወየብሰ፡ ሥረዊሁ፤

ኤፍሬም፡ መከራ፡ ተቀበለ፤ አባትነቱ፡ ጠፋ፤

ወኢይፈሪ፡ እንከ፡ ዳግመ፤

ዳግመኛ፡ ልጅ፡ አይወልድም፤

ወእመኒ፡ ወለዱ፡ እቀትል፡ ፍሬ፡ ከርሦሙ፤

ልጅም፡ ቢወልድ፡ ልጆቹን፡ አጠፋለሁ፤

፲፯፤ መፍትወ፡ ገደፎሙ፡ እግዚአብሔር፤

እግዚአብሔር፡ በሚገባ፡ አጠፋቸው፤

እስመ፡ አበዩ፡ ሰሚዖቶ፤

ሕጉን፡ አንሰማም፡ ብለዋልና፤

ወይከውኑ፡ መታሕላነ፡ በውስተ፡ አሕዛብ፤

በአሕዛብ፡ ዘንድ፡ የሚቀላውጡ፡ ይሆናሉ፤ አንድም፡ ዘለል፡ ተሰል፡ ይላሉ፤ ወእተሀል፡ እንዳለ፡ ኢዮ. ፪ ቍ.፱።

## - ምዕራፍ ፲ -

፩፤ ዓፀደ፡ ወይን፡ ዘሠረፀ፡ ኤፍሬም፤

ከዚህ፡ አስቀድሞ፡ የሕጉን፡ ማደሪያ፡ ኤፍሬም፡ በረድኤት፡ የለመለመ፡ ነበረ፤

ወሠምረ፡ ፍሬሁ፤

ልጁ፡ ያማረ፡ የተወደደ፡ ነበር፤

ወበከመ፡ ብዝኀ፡ ፍሬሆሙ፡ ከማሁ፡ አብዝኁ፡ መሥዋዕቶሙ፤

እንደልጆቻቸው፡ ብዛት፡ መጠን፡ መሥዋዕታቸውን፡ አብዝተውሠዉ፤

ወበአምጣነ፡ ብሔሩ፡ ሐነፁ፡ ሐውልተ፤

ኃጢአቱ፡ በሀገሩ፡ መበጀት፡ መጠን፡ ነው፤ ምንት፡ ኃጢአቱ፡ ለያዕቆብ፡ ብሎ እንዲያመጣው፤ አንድም፡ በአምጣነ፡ ስፍሐ፡ ምድሩ፡ ይላል፤ በሀገሩ፡ ስፋት፡ መጠን፡ ጣዖት፡ አቆሙ፤ በኍልቈ፡ አህጉሪከ፡ ከማሁ፡ አማልክቲከ፡ ይሁዳ፡ እንዲል፤

፪፤ ወተናፈቀ፡ ልቦሙ፤

ልቡናቸው፡ በሕግ፡ ተለየ፤ አንድም፡ ከሕገ፡ እግዚአብሔር፡ ተለየ፤



ወይእዜኒ፡ ይጠፍዑ፡ ለሊሆሙ፤

አሁን፡ ራሳቸው፡ ይጠፋሉ፡

ወእነሥት፡ ምሥዋዓቲሆሙ፤

ለጣዖት፡ የሚሰዉበትን፡ ምሥዋዑን፡ አጠፋዋለሁ፤

ወየሐሥር፡ ምስሎሙ፤

ጣዖቱን፤ አንድም፡ ምስላቸውን፡ ያጠፋል፤ ምስሌሆሙ፡ ቢል፡ ከጣዖቱ፡ ጋራ፤

፫፤ ናሁ፡ ይእዜ፡ ይብሉ፡ አልብነ፡ ንጉሥ፤

አሁንም፡ ንጉሥ፡ የለንም፡ አሉ፤

እመ፡ ኢፈራህናሁ፡ ለእግዚአብሔር፤

እግዚአብሔርንም፡ ካልፈራነው፤

፬፤ ወንጉሥኒ፡ ምንተ፡ ይረሲ፡ ለነ፡ እንዘ፡ ይትናገር፡ ቃለ፡ ምክንያተ፡ ሐሰት፤

ንጉሡስ፡ የሐሰት፡ ነገር፡ ምክንያት፡ እየተናገረ፡ ምን፡ ያደርገናል፤

ወይትካየድ፡ ኪዳነ፡ ዘምስለ፡ ዓማፂ፡ ወገፋዒ፤

ካመፀኛ፡ ከበደለኛ፡ ጋራ፡ እየተማማለ፡ ምን፡ ያደርገናል፡ አሉ፤

ወኃሥሩ፡ በፍትሕ፤

በፍርድ፡ ጊዜ፡ አፈሩ፤

አምሳለ፡ ነጌያት፡ በውስተ፡ ምድር፡ ብዙኃት፡ አዘቃት፤

በቤተ፡ ጣዖት፡ ዝሆን፡ ከረግረግ፡ ገብቶ፡ እንዲዘገይ፡ ከቤተ፡ ጣዖት፡ ገብተው፡ ዘገዩ፤

፭፤ ከመ፡ ሣዕር፡ ዘመልዓ፡ ውስተ፡ ገራህት፡ ሰላህም፡ ከማሁ፡ ቤቱ፡ ውስተ፡ ቤተ፡ አዎን፡ ሰብአ፡ ሰማርያ፤

በርሻ፡ መካከል፡ ያለ፡ ሣርን፡ አጨናንቆ፡ አግብቶ፡ ሉሳም፡ እንዲያበሉ፡ የሰማርያ፡ ሰዎች፡ እየተጨናነቁ፡ ወደቤተ፡ ጣዖት፡ ገቡ፤

ሰብአ፡ ሰማርያ፡ ለህውም፡ ሕዝብ፤

ሕዝቡ፡ አዘኑለት፡ አለቀሱለት፤

በከመ፡ አእመርዎ፡ ከማሁ፡ ይስሕቁ፡ ዲበ፡ ክብሩ፤

ከዚህ፡ ቀድሞ፡ ክብሩን፡ እንዳወቁት፡ መጠን፡ በክብሩ ጥፋት፡ ይዘብቱበታል፤

እስመ፡ ፈለሰ፡ እምኔሁ፤

ገንዘቡ፡ ከሱ፡ ተለይቶ፡ ይሄዳልና፤

፮፤ ወኪያሁኒ፡ ሐመይዎ፡ ወወሰድዎ፡ ብሐረ፡ ፋርስ፤

እሱንም፡ አሥረው፡ ወደ፡ ፋርስ፡ ወሰዱት፤

አምኃሁ፡ ለኢያሪም፡ ንጉሥ፡ ጸገውዎ፡ ወመጠውዎ፡ ለኤፍሬም፤

ንጉሡን፡ ለስልምናሶር፡ እጅ፡ መንሻ፡ አድርገው፡ ሰጡት፤ አንድም፡ የንጉሡን፡ እጅ፡ መንሻ፡ ለኤፍሬም፡ ሰጡት፡ አለ፤ ፍና፡ ተሣልቆ ነው፤

www.ethiopianorthodox.org

ወተኃፍረ፡ እስራኤል፡ በምክሩ፤

እስራኤል፡ በባለጠግነቱ፡ መከራ፡ መጥቶበት፡ አፈረ፤

፯፤ ገደፈቶ፡ ሰማርያ፡ ለንጉሣ፡ ውስተ፡ ገጸ፡ ማይ፤

በደሴት፡ ያሉ ሰዎች፡ ጥራጊ ውን፡ ትቢያውን ከባሕር፡ እን ዲጥሉት፡ ሰማርያ፡ ንጉሡን፡ ጣለችው፤ አንድም፡ ያ፡ በጣ ሉት፡ ጊዜ፡ እንዲንጓለል፡ አን ጓለለችው፤

፰፤ ወይትከሠት፡ አህጉረ፡ ጣዖቱ፡ ለእስራኤል፤

ጣዖት፡ የሚያመልኩበት፡ ሀገር፡ ሁሉ፡ ከብቱ፡ ሰዉ፡ ተማርኮ፡ ሄዶ፡ ብቻውን፡ ይቀራል፤ አን ድም፡ አውግረ፡ ጣዖቱ፡ ይላል፤ ጣዖት፡ የሚያመልኩበት፡ ኮረ ብታ፡ ይገለጣል፤ አያድናቸ ውም፤ አንድም፡ በተራራ፡ ላይ፡ ያለ፡ ጣዖት፡ አያድናቸውም፤ አንድም፡ አውግረ፡ ዛውዑ፡ ይላል፤ አብነት፡ እንዲህ፡ ያስተ ረጉማል፤

ሶከ፡ ወአሜከላ፡ ይበቍል፡ ውስተ፡ ምሥዋዒሆሙ፤

ለጣዖት፡ መሠዋዕት፡ በሚሠ ዉበት፡ ሁሉ፡ ተፈቶ፡ ሶክ፡ አሜ ከላ፡ ይበቅልበታል፤

ወይብልዎሙ፡ ለአድባር፡ ደቁ፡ ላዕሌነ፡ ወለአውግርኒ፡ ድፍኑነ፤

ከመከራው፡ ጽናት፡ የተነሣ፡ ተራ ራው፡ ኮረብታው፡ ተንዶ፡ ተጭ ኖን ብለው፡ ይመኛሉ፤

፱፤ በእንተ፡ ዘአበሰ፡ እስራኤል፡ በአውግሪሁ፤

እስራኤል፡ ተራራውን፡ ስላመ ለከ፤ አንድም፡ በተራራ፡ ላይ ያለ ውን፡ ጣዖት፡ ስላመለከ፤

ኀበ፡ ቆማ፡ እገሪሆሙ፡ በህየ፡ ይረክ ቦሙ፡ ቀትል፡ በውስተ፡ ወግር፤

እግራቸው፡ ከቆመበት፡ ላይ፡ በተራራው፡ ሰልፍ፡ ያገኛቸዋል፤

፲፤ ወመጽአ፡ ወቀሠፎሙ፡ ለደቂቀ፡ ዓመፃ፡

ይመጽእ፡ ሲል፡ ነው፤ በመ ዓት፡ ይመጣል፤ የበደሉትን፡ ሰዎች፡ ሁሉ፡ ያጠፋቸዋል፤

ወይትጋብዑ፡ ላዕሌሆሙ፡ ኵሎሙ፡ አሕዛብ፡ ከመ፡ ይገሥጽዎሙ፡ በብ ዝኃ፡ ጌጋዮሙ፤

በኃጢአታቸው፡ ብዛት፡ ያጠፏ ቸው፡ ዘንድ፡ አሕዛብ፡ በእሳ ቸው፡ ላይ፡ ይሰበሰባሉ፤

፲፩፤ ኤፍሬም፡ ዕጐልት፡ እንተ፡ ተም ህረት፡ ፀዊረ፡ አርዑት፤

ኤፍሬም፡ ቀምበር፡ መሸከምን፡ ተምራ፡ የገደፈች፡ ጊደር፡ ሆነ፤ ያች፡ እንድትታበይ፡ ታበየ፤



አንድም፡ ኢተምህረት፡ ይላል፤ ኤፍሬም፡ ቀምበር፡ መሸከ ምን፡ ያልተማረች፡ ጊደር፡ ነው፤ ያች፡ እንድትቀናጣ፡ ተቀናጣ፤

ወእዔዕን፡ ሠረገላ፡ ዲበ፡ መሠንየ፡ ክሣዱ፡ ለኤፍሬም፤

በኤፍሬም፡ ባማረ፡ አንገቱ፡ ላይ፡ ሥልጣነ፡ አሕዛብን፡ አመጣበታለሁ፤

ወይከይዶ፡ ይሁዳ፤

ሁለቱ፡ ነገድ፡ ይሰለጥንበታል፤

ወያዕቆብ፡ ያስተዔሪ፡ ንግሠ፤

ዘሩባቤል፡ መንግሥቱን፡ ከዳዊት፡ ከሰሎሞን፡ ያስተካክላል፤ አን ድም፡ አሥሩን፡ ነገድ፡ ሁለቱን፡ ነገድ፡ ይገዛል፤

፲፪፤ ዝርዑ፡ ለክሙ፡ ጽድቀ፡ ወዕ ርሩ፡ ፍሬ፡ ሕይወት፡ ወምሕረት፤

ዝርዑ፡ ግሥ፡ ነው፤ ምግባር፡ ትሩፋት፡ ሠርታችሁ፡ ክብርን፡ ይቅርታን፡ እንድታገኙ፡ ሁኑ፤

ወአኀትዉ፡ ለክሙ፡ ማኅቶተ፡ ጥበብ፤

አኀትዉ፡ ግሥ፡ ነው፤ ጥበ ብን፡ ያዙ፤

ኅሥዎ፡ ለእግዚአብሔር፡ እስከ፡ ይበ ጽሕ፡ ማዕረረ፡ ጽድቅክሙ፤

ይበጽሕ፡ ማዕረረ፡ ግሥ፡ ነው፤ የምግባራችሁን፡ ዋጋ፡ ሚጠ ትን፡ የምታገኙበት፡ እስኪደ ርስ፡ ድረስ፡ እግዚአብሔርን፡ በአምልኮት፡ ሹት፤

፲፫፤ ለምንት፡ ትተክሉ፡ ዓመፃ፡ ወትቀሥሙ፡ ኃጢአተ፡ ወትበልዑ፡ ፍሬ፡ ሞት፤

በነቢብ፡ በገቢር፡ ኃጢአት፡ ሠርታችሁ፡ ሞት፡ እንዲመ ጣባችሁ፡ ለምን፡ ትሆናላችሁ፤

እስመ፡ ተወከልከ፡ በሠረገላከ፡ ኤፍሬም፡ ወበብዝኃ፡ ሠራዊትከ፤

ኤፍሬም፡ በሠረገላህ፡ ተአምነ ሃልና፡ በሠራዊትህ፡ ብዛት፡ ታብየሃልና፤

ይትነሣእ፡ ሞት፡ ላዕለ፡ ሕዝብከ፤

ሞት፡ ስልምናሶር፡ በወገኖ ችህ፡ ላይ፡ ይመጣባቸዋል፤

፲፬፤ ወይወድቁ፡ ኵሉ፡ አረፋቲከ፤

ቅጽሩ፡ ሁሉ፡ ይፈርሣል፤ አን ድም፡ አርበኛው፡ ሁሉ፡ ይጠፋል፤

ከመ፡ ድቀተ፡ ሼሌማ፡ ቤተ፡ አርብ ኤል፡ በመዋዕለ፡ ቀትል፤

ኤዶምያስ፡ በሰልፍ፡ ቀን፡ እንደጠፋች፡ ይጠፋሉ፤ ቤተ፡ ጣዖት፡ ብሎ፡ ለኤዶምያስ፡ ቀጠለ፤ አንድም፡ ሼሌማ፡ ሰሎ ሞን፡ ነው፤ የሰሎሞን፡ አለቃ፤ እንደነበረ፡ እንደሮብአም፡ አለቃ፡ እንደ፡ አዶሪናም፡ አሥሩ፡ ነገድ፡ ሁለቱ፡ ነገድ፡ በተሰለፉበት፡ ቀን፡ ይጠፋሉ፤ ቤተ አሮብኤል፡ አይመችም፤ አንድም፡ በቤተ፡ ጣዖት፡ እንደ፡ ሞተ፤ አንድም፡ አሮብኤል፡ የሮብአም፡ ሎሌ፡ ሲል፤

www.ethiopianorthodox.org

ወነጽሑ፡ እመ፡ ላዕለ፡ ውሉዳ፤

እናቲቱን፡ ከልጇ፡ ጋራ፡ በመ
ከራ፡ ያጠፏታል፤

፲፭፤ ከማሁ፡ እገብረክሙ፡ ቤተ፡ እስራኤል፡ በእንተ፡ ኃጢአትክሙ፤

እስራኤል፡ በኃጢአታችሁ፡ ምክ
ንያት፡ አሁን፡ እንደተናገርሁ፡
ፈጥኜ፡ መከራ፡ አመጣብችኋለሁ፤

በጽባሕ፡ ይነጽሕዎ፡ ለንጉሠ፡ እስራኤል፤

የእስራኤልን፡ ንጉሥ፡ ፈጥ
ነው፡ በመከራ፡ ይጥሉታል።

## - ምዕራፍ ፲፩ -

፩፤ እስመ፡ ሕፃን፡ ውእቱ፡ እስራኤል፤

እስራኤል፡ ሕፃን፡ አእምሮ፡
ነውና፤ አንድም፡ አልተቀ
ጣም፡ አልተሠራምና፤

እስመ፡ አነ፡ አፍቀርክዎ፤

እኔ፡ ወድጄዋለሁና፡ ከግብፅ፡
ጠራሁት፤ አንድም፡ ወድጄዋ
ለሁና፤

እምግብፅ፡ ጸዋዕክዎ፡ ለወልድየ፤

ልጄ፡ ክርስቶስን፡ ወደግብፅ፡
ጠራሁት፤

፪፤ ወበከመ፡ ጸዋዕክዎሙ፡ ከማሁ፡ ርኅቁ፡ እምኔየ፤

እንደጠራኋቸው፡ መጠን፡ ከገጸ፡
ረድኤቴ፡ ራቁ፤

እሙንቱሰ፡ ለበዓል፡ ሦዑ፡ ወለግልፎ፡ ዐጠኑ፤

እነዚህስ፡ ለጣዖት፡ ሠዉ፤
ለተቀረጸ፡ ጣዖት፡ ዐጠኑ፤

፫፤ ወአነ፡ አፍቀርክዎ፡ ለኤፍሬም፤

ከዚህ፡ አስቀድሞ፡ እኔ፡ ኤፍ
ሬምን፡ ወደድሁት፤

ወተመጠውክዎ፡ በመዝራዕትየ፤

በሥልጣኔ፡ ጠበቅሁት፤

ወኢያእመሩ፡ ከመ፡ አነ፡ አድኃንክዎሙ፤

እኔ፡እንደአዳንኋቸው፡አላወቁም፤

፬፤ ወሰሐብክዎሙ፡ በሐብለ፡ ሰብእ፡ ወበማዕሠረ፡ ፍቅር፤

ሙሴ፡ አሮንን፡ በወደድሁበት፡
ፍቅር፡ ወደድኋቸው፤

ኮንክዎሙ፡ ከመ፡ ዘይጸፍዕዎ፡ ለብእሲ፡ መልታሕቶ፡ ወይኔጽር፡ መንገሌሁ፤

የደከመን፡ ሰው፡ ከክፉ፡ ቦታ፡
ፊቱን፡ እየጸፉ፡ እንዲያወጡት፡
ኋላ፡ በዓይነ፡ ፍቅር፡ እንዲያየው፡
ወደድኋቸው፤ አንድም፡ ያ፡ በዓ
ይነ፡ መዓት፡ እንዲያየው፡ አል
ወደዱኝም፤

፭፤ ወእብሉ፡ ነበረ፡ ኤፍሬም፡ ውስተ፡ ግብፅ፡ ወዕሡር፡ ውእቱ፡ ንጉሥ፡ ውስተ፡ ፋርስ፤

እንዘ፡ ዕሡር፡ ሲል፡ ነው፤
በፋርስ፡ ታሥሮ፡ ሳለ፡ በግ



ብፅ፡ ኖረ፡ እለዋለሁ፡ በግብፅ፡
ይቀበለው፡ የነበረውን፡ መከራ፡
ስለተቀበለ፡ እንዲህ፡ አለ፤ አን
ድም፡ ቀድሞ፡ በግብፅ፡ መከራ፡
ሲቀበል፡ ኖረ፤ ዛሬም፡ በፋርስ፡
መከራውን፡ ያያል፤

እስመ፡ ዓበየ፡ ተመይጦ፤

ወደእግዚአብሔር፡ መመለ
ስን፡ እንቢ፡ ብሏልና፤

፮፤ ወደክመት፡ ኵናት፡ በሀገሩ፤

ጦር፡ እሱን፡ በማጥፋት፡ ደከ
መች፤ የሚዋጋው፡ ሰው፡ ጠፋ፤

ወሠዓራ፡ ለደዌሁ፤

ሕግን፡ አፈረሳት፤ ባይጠብ
ቃት፡ ደዌ፡ የምታመጣበት፡ ስለ
ሆነ፡ ደዌ፡ አላት፤

ወኃልቀ፡ ደዌ፡ በላዕሌሁ፤

መከራ፡ በሱ፡ ተፈጸመ፤

ይበልዑ፡ እምፍሬ፡ ምግባሮሙ፤

የኃጢአታቸውን፡ ፍዳ፡ ይቀበላሉ፤

፯፤ ሕዝብየሰ፡ ስቁል፡ እምነ፡ ምንባሪሁ፤

ወገኔ፡ እስራኤል፡ ግን፡ ከተ
ቀመጠበት፡ ተማርኮ፡ ሲሄድ፡
በእግሩ፡ ጫፍ፡ ቁሟል፤ አን
ድም፡ እምግባሪሁ፡ ይላል፤ ከም
ግባሩ፡ የተነሣ፡ መከራ፡ የሚ
ቀበል፡ ነው፤

ወይትመአዕ፡ ላዕለ፡ ክብሩ፤

ባለጸግነቱን፤ ጌትነቱን፡ አጥቶ፡
ይበሳጫል፤

ወእቤ፡ ኃደገ፡ አምልኮትየ፤

አምልኮቴን፡ እንዴት፡ ተውህ፡
አልሁ፤

እፎኑ፡ እሰውቀከ፡ ኤፍሬም፤

ኤፍሬም፡ አምልኮቴን፡ ትተህ፡
በረድኤት፡ እንዴት፡ ልገድ
ፍህ? (ልደግፍህ)?

፰፤ ወእፎኑ፡ እሬስየከ፡ እስራኤል፤

እስራኤል፡ እንደምን፡ ላድርግህ፤

ከመ፡ አዳማኑ፡ ወሚመ፡ ከመ፡ ሱባማ፤

እንደ፡ አዳማ፡ ወይስ፡ እንደሱ
ባማ፡ ላጥፋህን፤

ተሀውከት፡ ልብየ፡ ወአስተርአየት፡ ምሕረትየ፤

እንዳላጠፋህስ፡ ልቡናዬ፡
ራራች፤ ቸርነቴ፡ ተገለጠች፤

፱፤ ወኢይገብር፡ እንከሰ፡ መቅሠፍተ፡ መዓትየ፤

እንግዲህ፡ ወዲህስ፡ ተቆጥቼ፡
በማመጣው፡ መቅሠፍት፡
ሰውን፡ አላጠፋም፤

ወኢየኃድግ፡ ያጥፍዕዎ፡ ለኤፍሬም፤

ኤፍሬምን፡ ያጠፉት፡ ዘንድ፡
አላሰናብትም፤

እስመ፡ አነ፡ እግዚአብሔር፡ ወአኮ፡
ሰብእ፤

እኔ፡ መሐሪ፡ ወመስተሣህል፡
ነኝና፡ ልበ፡ ጽኑ፡ አይደለሁምና፤

ወእትቄደስ፡ በላዕሌከ፤

አንተን፡ አድኜ፡ እመሰገናለሁ፤

ወእቤ፡ ኢይበውዕ፡ ሀገረ፤

ወደቤተ፡ ጣዖት፡ አልገባም፤
አንድም፡ ወደኢየሩሳሌም፡
አልመለስም፤

፲፤ አላ፡ አሐውር፡ እትልዎ፡
ለእግዚአብሔር፡ እግዚእ፤

እግዚአብሔርን፡ በሕግ፡ በአም
ልኮት፡ እከተለው፡ ዘንድ፡ ወደ
ብሔረ፡ አዛፍ፡ እሔዳለሁ፡
እንጂ፤ ከዘጠኙ፡ ነገድ፡ ተው
ጣጥተው፡ ወደብሔረ፡ አዛፍ፡
ዓመት፡ ከመንፈቅ፡ ሄዱ፤ ኤፍ
ራጥስ፡ ከሚባል፡ ወንዝ፡ ደረሱ፤
ውሀው፡ ተከፍሎላቸው፡ ብሔረ፡
አዛፍ፡ ገብተዋል፤ ከዚያ፡ ሺህ፡
ዘመን፡ ይኖራሉ፤ በዚሁ፡
በሺሁ፡ ዘመን፡ ሦስት፡ ልጅ፡
ይወልዳሉ፤ አንዱን፡ ለቤተ፡
እግዚአብሔር፡ ይሰጣሉ፤ ሁለ
ቱን፡ ለዘር፡ ይተዋሉ፤ ከሺህ
ዘመን፡ በኋላ፡ አይበላስ፡ የለም፡
አይፀግብ፡ ይባስ፡ ብለው፡ የሚ
ሞቱ፡ አሉ፤ በሕይወት፡ መኖ
ርን፡ የሚወዱ፡ ወደብሔረ፡
ሕያዋን፡ ይሄዳሉ፤ እነዚህንም፡
ዞሲማስ፡ የሚባል፡ መነኵሴ፡
ገብቶ፡ ሥጋዌውን፡ አስተምሯ
ቸዋል፤ ቅዱስ፡ ገብርኤል፡
(ማቴዎስ)፡ ሥጋዌውን፡ ነግ
ሯቸዋል፤ ጌታም፡ እሑድ፡
እሑድ፡ ሥጋውን፡ ደሙን፡
እንዲቀበሉ፡ ያደርጋቸዋል፤ ያቀ
ብላቸዋል፤ አንድም፡ እስመ፡
እግዚአብሔር፡ አነ፡ ብለህ፡
መልስ፤ እኔ፡ የባሕርይ፡ አም
ላክ፡ ነኝና፡ ሩቅ፡ ብእሲ፡ አይ
ደለሁምና፡ አንተን፡ በነፍስ፡
አድኜ፡ እመሰገናለሁ፤ ወደም
ኵራብ፡ አይሁድ፡ አልገባም፤
እግዚአብሔርን፡ በአምልኮት፡
እከተለው፡ ዘንድ፡ ወደቤተ፡
መቅደስ፡ እሄዳለሁ፡ እንጂ፤

እስመ፡ ያድኅን፡ ከመ፡ አንበሳ፡
ዘይጥኅር፤

እንደሚያገሳ፡ አንበሳ፡ በማስ
ፈራት፡ ያድናልና፤

ወይደነግፁ፡ ውሉድ፡ እማይ፤

እስራኤል፡ ከተደረገላቸው፡ ተኣ
ምራት፡ የተነሣ፡ የደስታ፡ ድን
ጋጤ፡ ይደነግጣሉ፤ ሲወጡ፡
ሰባት፡ ውሀ፡ ተከፍሎላቸዋ
ልና፤ ከፍሎላቸዋልና፤ አን



ድም፡ ከመኖሩ፡ የተነሣ፡ ይደ
ነግፁ፡ ብለህ፡ እሠር፤

፲፩፤ ወያነክሩ፡ ከመ፡ ዖፊ፡ ግብጽ፤

እስራኤል፡ በሚጠት፡ ከልብሳ
ቸው፡ ጽዳት፤ ከድንኳናቸው፡
ነጭነት፡ የተነሣ፡ ሳቢሳ፡ መስ
ለው፡ ይወጣሉ፤

ወከመ፡ ርግብ፡ እምብሔረ፡ ፋርስ፤

ርግብ፡ አደምድማ፡ እንድት
ወጣ፡ አደምድመው፡ ከፋርስ፡
ይወጣሉ፤

ወአገብኦሙ፡ ውስተ፡ አብያቲሆሙ፡
ይቤ፡ እግዚአብሔር፤

እግዚአብሔር፡ ወደሀገራቸው፡
እመልሳቸዋለሁ፡ አለ፤

፲፪፤ ሐፀሩኒ፡ ኤፍሬም፡ በሐሰት፡
ወቤተ፡ እስራኤል፡

ንጉሡ፡ ሕዝቡ፡ በሐሰት፡ በጣ
ዖት፡ ከበቡኝ፤

ወይሁዳ፡ በዓመፃ፤

ሁለቱ፡ ነገድም፡ በደሉኝ፤

ይእዜ፡ አእመርክዎሙ፡ እግዚኦ፤

ይቤ፡ ነቢይ፡ ያለበት፡ ነው፤
አቤቱ፡ ዛሬ፡ ክፋታቸውን፡ አወ
ቅሁባቸው፡ ይላል፡ ነቢዩ፤

ወሕዝበ፡ ቅዱስ፡ ተሰምዩ፡ ለእግዚ
አብሔር፤

ከዚህ፡ አስቀድሞ፡ ለእግዚአብ
ሔር፡ ክቡር፡ ወገን፡ ተባሉ።

## - ምዕራፍ ፲፪ -

፩፤ ኤፍሬምስ፡ ጋኔን፡ እኩይ፡
ዘይዴግን፡ ክብረ፡ ከንቶ፤

ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ያለበት፡
ነው፤ ኤፍሬም፡ ከንቱ፡ ጣዖ
ትን፡ የሚከተል፡ የግብር፡
ጋኔን፡ ሆነ፡ ይላል፡ ጌታ፤

ወሐሰተ፡ አብዝኃ፤

ሐሰት፡ ጣዖትን፡ አበዛ፤

ወተካየደ፡ ኪዳነ፡ ምስለ፡ ፋርስ፤

ልገብር፡ ልቀቅል፡ ብሎ፡ ከፋ
ርስ፡ ጋራ፡ መሐላን፡ ተማማለ፤

ወየሐውር፡ ግብፀ፡ ከመ፡ ይምሀርዎ፤

ይርድእዎ፡ ሲል፡ ነው፤ ይረ
ዱት፡ ዘንድ፡ ወደግብፅ፡ ይሄድ፡
ነበር፤ አንድም፡ እንዳለበት፡
ይሆናል፤ አምልኮተ፡ ጣዖ
ትን፡ ያስተምሩት፡ ዘንድ፡ ወደ
ግብፅ፡ ይሔድ፡ ነበር፤

፪፤ ወይትዋቀስ፡ እግዚአብሔር፡
ምስለ፡ ይሁዳ፤

ከሁለቱ፡ ነገድ፡ ጋራ፡ ይወቃ
ቀሳል፤

ወይትቤቀሎ፡ ለያዕቆብ፡ በፍናዊሁ፤

ያዕቆብን፡ በሥራው፡ ተበቅሎ፡
ያጠፋዋል፤

ወይፈድዮ፡ በከመ፡ ምግባሩ፤

እንደ፡ ሥራው፡ መጠን፡ መከ
ራውን፡ ያመጣበታል፤

www.ethiopianorthodox.org

፫፤ በውስተ፡ ከርሥ፡ አዕቀፆ፡ ለእኁሁ፤

ያዕቆብ፡ ጥንቱን፡ ክፉ፡ ነው፤ ወንድሙን፡ በማኅፀን፡ አሰነካ ከለው፤ እንዲያሰነካክልማ፡ ያደ ረገ፡ እግዚአብሔር፡ አይደለም? ቢሉ፡ እንዲያሰነካክል፡ ያደረ ገው፡ እግዚአብሔርን፡ በደለ፤

ወበየማሁ፡ ክህለ፡ ምስለ፡ እግዚአብሔር፤

በደካማ፡ ባሕርዩ፡ ከእግዚአብ ሔር፡ ጋር፡ መታገል፡ ተቻለው፤

፬፤ ወጸንዓ፡ ወክህለ፡ ምስለ፡ መል አክ፡ በኃይሉ፤

በኃይሉ፡ ከላባ፡ ከኤሳው፡ ጋራ፡ መጣላት፡ ተቻለው፤

በከዩ፡ ወተጋነዩ፡ ሊተ፡ ውስተ፡ ቤት፡ ኀበ፡ ረከቡኒ፤

እኔን፡ ባገኙበት፡ ቦታ፡ አልቅሳ ችሁ፡ለኔ፡ተገዙልኝ፡አልኋቸው፤

ወበህየ፡ ተናገሩኒ፤

ከእግዚአብሔር፡ ዘንድ፡ ለምን ልን፡ አሉኝ፤

፭፤ ወእግዚአብሔር፡ አምላክ፡ ዘኵሉ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ ፈጣሪ፡ እግ ዚአብሔር፡ ነው፡ አልኋቸው፤ አንድም፡ መሐሪ፡ ወመስተሣ ህል፡ነውና፡ይቅር፡ይላችኋል፤

፮፤ አንተሂ፡ ተመየጥ፡ ኀበ፡ እግ ዚአብሔር፡ አምላክከ፤

አንተም፡ ወደፈጣሪህ፡ ወደእግ ዚአብሔር፡ ተመለስ፤

ጽድቀ፡ ወምጽዋተ፡ ዕቀብ፤

ምግባር፡ ሃይማኖትን፡ ያዝ፤

ወቅረብ፡ ኀበ፡ አምላክከ፡ ኵሎ፡ ጊዜ፤

በየጊዜው፡ ሁሉ፡ በአምልኮት፡ ወደፈጣሪህ፡ ተመለስ፤

፯፤ ውስተ፡ እዴከ፡ ዘከነዓን፡ መዳ ልወ፡ ዓመፃ፤

በጅህ፡ ያለ፡ ሐሰተኛ፡ ሚዛንን፡ ትተህ፤

ወአፍቅሮ፡ ትዕግልት፤

ቅሚያን፡ መውደድ፡ ትተህ፡ ተመለስ፤

፰፤ ወይቤ፡ ኤፍሬም፡ ወዳዕኩ፡ ረከብኩ፡ ሊተ፡ ሕማመ፤

ኤፍሬም፡ ፈጽሜ፡ መከራ፡ ተቀበልኩ፡ አለ፤

ወኵሎ፡ ፃማየ፡ ኢየአክለኒ፡ ለኃጢአ ትየ፡ ዘአበስኩ፤

ለበደልሁት፡ ኃጢአት፡ ገንዘቤ፡ ሁሉ፡ ለእግዚአብሔር፡ ካሳ፡ ሊሆን፡ አይበቃኝም፡ አለ፤

፱፤ ወአነ፡ እግዚአብሔር፡ አምላ ክከ፡ ዘአውጻእኩከ፡ እምድረ፡ ግብፅ፤

ከግብፅ፡ ያወጣሁህ፡ ፈጣሪህ፡ እኔ፡ ነኝ፤

ወዓዲ፡ አነ፡ አንበርኩከ፡ ውስተ፡ ምጽ ላላት፡ ከመ፡ አመ፡ መዋዕለ፡ በዓል፤

በዓለ፡ ሰዊትን፡ በዓለ፡ መጸለ ትን፡ እንዳከበርክበት፡ ጊዜ፡ ዳግመኛ፡ በተድላ፡ በደስታ፡ አኖርሁህ፤



፲፤ ወእትናገሮሙ፡ በነቢያት፤

በነቢያት፡ አድሬ፡ እነግራቸ ዋለሁ፤

ወአብዛኅኩ፡ ራእይየ፤

ራእዩን፡ አብዝቼ፡ ገለጥኩላቸው፤

ወተመሰልኩ፡ በእደ፡ ነቢያት፡ ወአኮ፡ በነቢያተ፡ ገለዓድ፡ እለ፡ ያስሕቱ፤

በነቢያት፡ አድሬ፡ አስተማ ርሁ፤ በሚያስቱ፡ በነቢያተ፡ ገለ ዓድ፡ አድሬ፡ አይደለም፤

፲፩፤ ወመላእክትኒ፡ ይሠውዑ፡ መሥዋዕቲሆሙ፡ ከመ፡ ማዕነቅ፡ ውስተ፡ ሣዕረ፡ ገዳም፤

ዋኖስ፡ ከዚያም፡ ከዚያም፡ እን ድትወልድ፡ አሰቆቻቸው፡ ከዚ ያም፡ ከዚያም፡ ይሠዋሉ፤

፲፪፤ ወሖረ፡ ያዕቆብ፡ ውስተ፡ ገዳመ፡ ሶርያ፤

ጥንቱንም፡ አባታቸው፡ ያዕቆብ፡ ከከነዓን፡ ልጆች፡ ጋራ፡ አልጋ ባም፡ ብሎ፡ ወደሶርያ፡ ሄደ፤

ወተቀንየ፡ ያዕቆብ፡ በእንተ፡ ብእሲቱ፡

ያዕቆብ፡ ስለራኄል፡ ተገዛ፤

ወዓቀባ፡ ለብእሲቱ

ያዕቆብ፡ ሚስቱ፡ ራኄልን፡ አሥራ፡አራት፡ዓመት፡ጠበቃት፤

ታሪክ፡ ያዕቆብ፡ ማለዳ፡ ገሥ ግሦ፡ ተነሥቶ፡ ብትልም፡ ከላባ፡ ዘንድ፡ ሄደ፤ አሻግሮ፡ ሲመለ ከት፡ በምድረበዳ፡ የውሃ፡ አዘ ቅት፡ አየ፤ የአዘቅቲቱም፡ አፍ፡ ደንጊያ፡ ተገጥሞ፡ ነበር፤ እረ ኞች፡ ተሰብስበው፡ ደንጊያዪ ቱን፡ አንስተው፡ በጎቻቸውን፡ አጠጥተው፡ መልሰው፡ ይገጥ ሟት፡ ነበር፡ ያዕቆብ፡ እረኞ ችን፡ እናንተ፡ ወንድሞቼ፡ ከወ ዴት፡ መጥታችኋል፡ አላቸው፤ ከካራን፡ አሉት፡ ላባን፡ ታው ቁታላችሁ? አላቸው፤ አዎን፡ አሉት፤ ደኅና፡ ነው? አላቸው፤ አዎን፡ ደኅና፡ ነው፤ አሁን፡ ልጁ፡ ራሄል፡ የአባቷን፡ በጎች፡ ይዛ፡ ትመጣለች፡ አሉት፤ ዓዲ ሁኑ፡ ኢበጽሐ፡ ሰዓት፡ ከመ፡ ይትጋብኡ፡ እንስሳክሙ፡ ከብ ቶቻችሁ፡ ተሰብስበው፡ ውሃ ውን፡ ይጠጡ፡ ዘንድ፡ ጊዜው፡ ገና፡ አልደረሰም? አላቸው፤ ይህንን፡ ሲጨዋወቱ፡ ራሄል፡ የአባቷን፡ በጎች፡ ይዛ፡ መጣች፤ ሂዶ፡ ተገናኛት፤ የርብቃ፡ ልጅ፡ እንደሆነ፡ ነገራት፤ ፈጥና፡ ሂዳ፡ ለአባቷ፡ ለላባ፡ ነገረችው፤ ላባም፡ ሂዶ፡ አንገቱን፡ አቅፎ፡ ሳመው፤ ከቤቱ፡ ወስዶ፡ አነጋ ገረው፤ ከዚያ፡ አንድ፡ ወር፡ ከተቀመጠ፡ በኋላ፡ ኢትትቀ ነይ፡ ሊተ፡ በከ፤ በከንቱ፡ አት ገዛልኝ፡ የምሰጥህን፡ ደመ ወዝ፡ ንገረኝ፡ አለው፤ ለላባ፡ ሁለት፡ ሴቶች፡ ልጆች፡ ነበ ሩት፤ ታላቂቱ፡ ልያ፡ ትባላ ለች፡ ዓይነ፡ ጨምጫማ፤

www.ethiopianorthodox.org

(መጭማጫ) ዓይነ፡ ሸሁራራ፣ መልክ፡ ክፉ፡ ነበረች፤ ታና ሽቱ፡ ራሄል፡ ትባላለች፣ መልክ፡ ከደም፡ ግባት፡ አስተባብራ፡ የያ ዘች፡ መልከ፡ መልካም፡ ነበ ረች፣ እትቀነይ፡ ለከ፡ ፯ተ ዓመተ፡ በእንተ፡ ራኄል፣ ስለ ራሄል፡ ሰባት፡ ዓመት፡ እገዛል ሃለሁ፡ እሷን፡ ስጠኝ፡ አለው፤ ይኄይሰኒ፡ አሀብከ፡ ለማዕም ርየ፣ ለማላውቀው፡ ክሰጣት፡ ለማውቅህ፡ ለአንተ፡ ለባዕድ፡ ክሰጣት፡ ላንተ፡ ለወዳጄ፡ ብሰ ጣት፡ ይሻለኛል፣ ፈቃድህስ፡ ከሆነ፡ እኔም፡ ፈቃዴ፡ ነው፡ ተቀመጥ፡ አለው፣ ወተቀንየ፡ ያዕቆብ፡ በእንተ፡ ራሄል፡ ፯ተ ዓመተ፣ ያዕቆብ፡ ስለራሄል፡ ሰባት፡ ዓመት፡ ተገዛ፣ ወኮና፡ ከመ፡ ሕዳጥ፡ በቅድሜሁ፣ ይወ ዳት፡ ነበርና፡ እንደ፡ ጥቂት፡ ቀን፡ ሆነው፡ ሰባት፡ ዓመት፡ ከተገዛ፡ በኋላ፡ ሚስት፡ ትሆ ነኝ፡ ዘንድ፡ ስጠኝ፡ አለው፣ ላባ፡ ያገሩን፡ ሰዎች፡ ሰብስቦ፡ ሠርግ፡ አደረገ፣ በመሸ፡ ጊዜ፡ አፍኖ፡ ሸፍኖ፡ ልያን፡ ሰጠው፣ ሲጨዋወት፡ አድሮ፡ ሲነጋ፡ ባያት፡ ጊዜ፡ ልያ፡ ሁና፡ አገ ኛት፣ ቢከፍቱ፡ ተልባ፡ እን ዲሉ፣ ምነው፡ እንዲህ፡ አደረ ግኸኝ፡ የተገዛሁልህ፡ ስለ፡ ራሄል፡ አልነበረም፡ አለው፣ በሀገራችንስ፡ ታላቂቱ፡ ሳለች፡ ታናሽቱን፡ አይድሩም፣ ለዛ ቲኒ፣ ፈጽም፡ ላቲ፡ ለዚችም፡ ሰባት፡ ዓመት፡ ተገዛ፡ አለው፣ ወገብረ፡ ከማሁ፣ እሱ፡ እንዳ ለው፡ አድርጓልና፡ ወዓቀባ፡ ለብእሲቱ፡ አለ፤

፲፫፤ በከዊነ፡ ነቢይ፡ አውጽአ፡ እግዚአብሔር፡ ለእስራኤል፡ እምግብፅ፣
ሙሴን፡ መምህር፡ በማድረግ፡ እስራኤልን፡ ከግብፅ፡ አወጣው፤ ዛሬ፡ ግን፡ ወደ፡ እግዚአብሔር፡ አንመለስም፡ አሉ፣

ወበከዊነ፡ ነቢይ፡ አቀበ፣
ሙሴን፡ ነቢይ፡ በማድረግ፡ ጠበቀው፤

፲፬፤ ተምዓ፡ ኤፍሬም፡ ወተ ቆጥዓ፣
ኤፍሬም፡ ፈጽሞ፡ ተቆጣ፣

ወደሙሂ፡ ላዕሌሁ፡ ተክዕወ፣
ኃጢአቱ፡ በዝቶ፡ ተሠራ፤ አን ድም፡ ለጣዖቱ፡ የሚሠዋው፡ ደም፡ በዝቶ፡ ፈሰሰ፣

ወኃሣሩሂ፣
ተዋርዶ፡ ይመጣበታል፣

ወይፈድዮ፡ እግዚአብሔር፡ ለኤፍሬም፣
በኤፍሬም፡ እግዚአብሔር፡ ፍዳ ውን፡ ያመጣበታል።



## - ምዕራፍ ፲፫ -

፩፤ ወእነሥት፡ ሥርዓቶ፡ ለእስራኤል፣
የእስራኤልን፡ ሥርዓተ፡ መን ግሥቱን፣ ሥርዓተ፡ ክህነ ቱን፡ አጠፋለሁ፣

ወእሬስዮ፡ ለበዓል፡ ሞተ፣
ጣዖቱን፡ ምክንያተ፡ ሞት፡ አደርገዋለሁ፣

፪፤ ወዳግመ፡ አበሰ፣
ዳግመኛ፡ በደሉ፣

ወገብሩ፡ ሎሙ፡ ስብኮ፡ ወርቆሙ፡ ወብ ሩሮሙ፡ በአምሳለ፡ ዘይገብሮ፡ ፀራቢ፤
እንጨት፡ ጠራቢ፡ በሚሠራው፡ አምሳል፡ ወርቁን፡ ብሩን፡ ጣዖት፡ አድርገው፡ ሠሩት፤

ወይዘብሑ፡ ሎሙ፣
መሥዋዕቱን፡ ይሠዉላቸዋል፤

ወይብሉ፡ ሠዑ፡ ሰብአ፡ ላህምሰ፡ ሐልቀ፣
ላሙስ፡ አልቋል፣ ሰው፡ እን ሠዋ፡ ይላሉ፤ አንድም፡ የላ ሙስ፡ ወረት፡ አልፏል፡ ሰውን፡ እንሠዋ፡ ይላሉ፣

፫፤ በእንተ፡ ዝንቱ፡ ይከውኑ፡ ከመ፡ ደመና፡ ጽባሕ፡ ወከመ፡ ጠለ፡ ጎህ፡ ዘየሐውር፣
ፈጥኖ፡ እንደሚጠፋ፡ እንደማ ለዳ፡ ዝናም፡ እንደማለዳ፡ ጠል፡ ይጠፋሉ፤

ወከመ፡ ኃሠረ፡ ዓውደ፡ እክል፡ ዘይነ ፍሐ፡ ነፋስ ፡ አውሎ፣
ነፋስ፡ አውሎ፡ እንደሚበት ነው፡ በእህል፡ አውድማ፡ እን ዳለ፡ ገለባ፡ ይጠፋሉ፤

ወከመ፡ ጢስ፡ ዕቶን፣
እንደምድጃ፡ ጢስ፡ ይጠፋሉ፣

፬፤ ወአነ፡ እግዚአብሔር፡ አምላ ክከ፡ ዘአጽንዖን፡ ለሰማያት፣
ሰማያትን፡ ያጸናኋቸው፡ ፈጣሪህ፡ እኔ፡ ነኝ፤ ጠፈርን፡ ሲያይ፡ እን ዲህ፡ አለ፤

ወአነ፡ ፈጠርክዋ፡ ለምድር፣
ምድርንም፡ የፈጠርኋት፡ እኔ፡ ነኝ፤

ወእዴየ፡ ዓቀመ፡ ኵሎ፡ ኃይላተ፡ ሰማይ፣
የሰማይ፡ ሠራዊት፡ የሚሆኑ፡ ፀሐይ፡ ጨረቃ፡ ከዋክብት፡ የተፈጠሩ፡ በኔ፡ ሥልጣን፡ ነው፤

ወአርአይኩከሆሙ፡ ከመ፡ ኢታምልኮሙ፡ ወኢትስግድ፡ ሎሙ፡ አመ፡ አውጻእኩከ፡ እምድረ፡ ግብፅ፣
ከግብፅ፡ በአወጣሁህ፡ ጊዜ፡ እን ዳትሰግድላቸው፡ እንዳታመል ካቸው፡ አሳየሁህ፤

ወኢተአምር፡ እንከ፡ ባዕደ፡ አምላከ፡ ዘእንበሌየ፡ ኢበሰማይ፡ በላዕሉ፡ ወኢበ ምድር፡ በታሕቱ፣
ከምድር፡ በላይ፡ ባለ፡ በሰማ ይም፡ ሆኖ፡ ከሰማይ፡ በታች፡ ባለ፡ በምድርም፡ ሆኖ፡ ከኔ፡ በቀር፡ ሌላ፡ አምላክ፡ እንዳታ መልክ፡ አሳየሁህ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወአልቦ፡ ዘያድኅን፡ ዘእንበሌየ፡

ከኔ በቀር የሚያድን የለም፤

፮፤ አነ፡ ረዐይኩክሙ፡ ውስተ፡ በድው፡ ኅበ፡ ዔልክሙ፡ በበመራዕይክሙ፡፡

በበነገድክሙ፡ ሲል፡ ነው፤ በየ ነገዳችሁ፡ በዘራችሁበት፡ ምድ ረበዳ፡ ሁሉ፡ እኔ፡ ጠበቅኋችሁ፤

ወጸገብክሙ፡ እስከ፡ ያጠልቀክሙ፡፡

እስኪሰለቻችሁ፡ ድረስ፡ መና ውን፡ ጠገባችሁ፤

ወአዕበይክሙ፡ ልበክሙ፡፡

ልቡናችሁን፡ አስታበያችሁ፤

፯፤ በእንተ፡ ዝንቱ፡ ረሳእክሙኒ፡፡

ስለታበያችሁ፡ ረሳችሁኝ፤

፰፤ ወአነኒ፡ እከውኖሙ፡ ከመ፡ አንበሳ፡ ለቤተ፡ ይሁዳ፡፡

እኔም፡ በሁለቱ፡ ነገድ፡ እንደ፡ አንበሳ፡ እሆንባቸዋለሁ፤

ወከመ፡ ነምር፡ ለኤፍሬም፡ ውስተ፡ ፍኖተ፡ ፋርስ፡፡

በፋርስ፡ ጐዳና፡ ሳሉ፡ ባሥሩ፡ ነገድ፡ እንደነምር፡ እሆንባቸዋ ለሁ፤ ትርጓሜው፡ ግን፡ እንዳ ለፈው፡ ነው፡ ባምስት፡ ምዕ ራፍ፡ በአሥራ፡ አንድ፡ ቍጥር፡ ይገኛል፤

፱፤ ወእቀትሎሙ፡ ከመ፡ ድብ፡ ርጉብ፡፡

እንደ፡ ተራብ፡ ድብ፡ አጠፋቸዋለሁ፤

ወእሰብር፡ ዓጽመ፡ ገበዋቲሆሙ፡፡

ገንዘባቸውን፡ አጠፋዋለሁ፤

፱፤ ወበህየ፡ ይበልዕዎሙ፡ አናብ ስተ፡ ገዳም፡ ወአራዊተ፡ ምድር፡ ይት ማሰጥዎሙ፡፡

ስልምናሶር፡ ናቡከደነፆር፡ አሕዛብ፡ ይነጣጠቋቸዋል፤

ለኃሣርከ፡ እስራኤል፡ መኑ፡ ይረድአከ፡፡

ኃጢአትህን፡ ሊያርቅልህ፡ እስ ራኤል፡ ማን፡ ይረዳሃል፤

፲፤ አይቴ፡ ውእቱ፡ ዝኩ፡ ንጉ ሥከ፡ ያድኅንከ፡ በኵሉ፡ አህጉሪከ፡፡

በሀገርህ፡ ሁሉ፡ ያድንህ፡ ዘንድ፡ ንጉሥህ፡ ወዴት፡ ነው፤

፲፩፤ ወይትበቀል፡ ለከ፡ ፀረከ፡፡

ጠላትህን፡ ያጠፋልህ፡ ዘንድ፤

ዝኩ፡ ዘትቤለኒ፡ ሀበኒ፡ መልአከ፡ ወንጉሠ፡፡

ንጉሥ፡ አንግሥልኝ፡ አለቃ፡ ሹምልኝ፡ ያልኸኝ፡ ንጉሡ፡ ወዴት፡ ነው፤

ወወሀብኩከ፡ በመዓትየ፡ ወበቍጥዓየ፡፡

ተቆጥቼ፡ የሰጠሁህ፤

፲፪፤ ወተዓገሥኩዎ፡ ለማዕሴተ፡ ዓመፃከ፡፡

ፍጹም፡ ወንጀልህን፡ ታገሥሁህ፤ አንድም፡ የወንጀልህን፡ ወንጀል፡ ታገስሁህ፡ ንጉሥ፡ አንግሥ ልኝ፡ ማለት፡ ወንጀል፡ ነው፤ ቢያነግሥላቸው፡ ካነገሠማ፡ ትን ቢት፡ ከተነገረለት፡ ከይሁዳ፡ ባላ ነገሠልንም፡ ማለት፡ የወንጀል፡ ወንጀል፡ ነውና፤



ኃጢአቱ፡ ለኤፍሬም፡ ዝጉብ፡፡

ብዙኀ፡ ክቡት፡ ሲል፡ ነው፤ የኤ ፍሬም፡ ኃጢአቱ፡ ብዙ፡ ነው፤ አንድም፡ የተሠወረ፡ ነው፤

፲፫፤ ወይእኀዞ፡ ማሕምም፡ ከመ፡ እንተ፡ ትወልድ፡፡

እንደምትወልድ፡ ሴት፡ ጭንቅ፡ ይይዘዋል፤

ዝንቱ፡ ወልድ፡ አብድ፡ ወአኮ፡ ጠቢብ፡፡

ይህ፡ ልጅ፡ ሰነፍ፡ ነው፡ ብልህ፡ አይደለም፤ አንድም፡ ዘአኮ፡ ጠቢብ፡ ይላል፡ ብልህ፡ ያይ ደለ፡ ሰነፍ፡ ነው፤

ወዘኢይቀውም፡ በተግሣጸ፡ ውሉድ፡፡

በልጆች፡ ተግሣጽ፡ የማይመ ለስ፡ ሰነፍ፡ ነው፤ ልጅ፡ በት ንሽ፡ ቁጣ፡ እንዲመለስ፡ አይ መለስም፤ አንድም፡ የነቢያ ትን፡ ምክር፡ አይሰማም፤

ዝንቱ፡ ወልድ፡ ዘኢይጠብዕ፡ በሞተ፡ ውሉድ፡ ዕሤተ፡ አብ፡ አፍላገ፡ ማየ፡ ሕይወት፡ ይው ኅዝ፡ እምከርሡ፡ የሚል፡ ይገ ኛል፡ በሰማዕታት፡ ሞት፡ ከሚ ያዝን፡ ከወልድ፡ ከባሕርዩ፡ የአብ፡ የባሕርይ፡ ሕይወቱ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ ይገኛል፤

፲፬፤ ወኢያእመሩ፡ ከመ፡ አነ፡ እሞት፡ አድኃንክዎሙ፡ ወእምሲኦል፡ ባላሕክዎሙ፡፡

አድኅንክዎሙ፡ ባላሕክዎሙ፡ አንድ፡ ወገን፡ ከሞት፡ ከመቃ ብር፡ የዳንኋቸው፡ እኔ፡ እንደ ሆንሁ፡ አላወቁም፤ አንድም፡ ከፈርዖን፡ ከዲያብሎስ፡ ያዳን ኋቸው፡ እኔ፡ እንደሆንሁ፡ አላወቁም፤

አይቴ፡ ቀኖትከ፡ ሞት፡፡

ሞት፡ ፈርዖን፡ ዲያብሎስ፡ ይዘህ፡ ማስቀረትህ፡ ወዴት፡ አለ፤

ወአይቴ፡ ውእቱ፡ መዓትከ፡፡

ሲያል፡ ግብፅ፡ መቃብር፡ እስ ራኤልን፡ ነፍሳትን፡ ይዘህ፡ ማስ ቀረትህ፡ ወዴት፡ አለ፤

ተኀብዓ፡ ፍሥሐከ፡ እምአዕይንቲከ፡፡

ተድላህ፡ ደስታህ፡ ከፊትህ፡ ጠፋ፤

፲፭፤ እስመ፡ ውእቱ፡ ይትፈለጥ፡ እማዕከለ፡ አኃዊሁ፡፡

አሥሩ፡ ነገድ፡ ከወንድሞቹ፡ ከሁ ለቱ፡ ነገድ፡ ተለይቶ፡ ይሄዳልና፤

ወያመጽእ፡ እግዚአብሔር፡ ላዕሌሁ፡ እምገዳም፡ ነፋሰ፡ ሐሩር፡፡

ከፋርስ፡ የሚያጠፋ፡ ስልምናሶ ርን፡ በእሱ፡ ያመጣል፤

ወያየብስ፡ ሥረዊሁ፡፡

አባትነቱን፡ ያጠፋልና፤

ወያነጽፍ፡ ዓዘቃቲሁ፡፡

ልጆቹን፡ ያጠፋልና፤ አንድም፡ ገንዘቡን፡ ያጠፋልና፤

ወያየብስ፡ ምድራ፡፡

አገሪቱን፡ ያጠፋልና፤ ተኀብአ፡ ብለህ፡ እሠር፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፮፤ ወያማስን፡ ኵሎ፡ መሠንየ፡ አብያቲሃ፡ ለሰማርያ፤

የሰማርያ፡ ያማረ፡ የተነፀፈ፡ የተ ጋረደ፡ ቤቷን፡ ሁሉ፡ ያጠፋል፤

እስመ፡ ዓለወቶ፡ ለአምላካ፤

ፈጣሪዋን፡ ክዳዋለችና፤

ወይወድቁ፡ በኵናት፡ ኵሎሙ፤

ሁሉም፡ በጦር፡ ይጠፋሉ፤

ወለደቂቆሙኒ፡ ይነጽሕዎሙ፤

አሕዛብ፡ ልጆቻ[illegible]ውን፡ በጦር፡ እየወጉ፡ ይጥሏቸዋልና፤ አንድም፡ እስራኤል፡ ልጆቻቸውን፡ እየ ወጉ፡ ይጥሏቸዋልና፤

ወያነቅዕዎን፡ ለዕኑሣቲሆሙ፤

የፀነሱትንም፡ ሴቶች፡ ይሰነጥ ቋቸዋል፤ ሴትን፡ ወንድን፡ ገደሉ፡ ይሉናል፡ ብለው፤ አንድም፡ አድ ገው፡ ጠላት፡ ይሆኑናል፡ ብለው፡ ይሠነጥቋቸዋልና።

## - ምዕራፍ ፲፬ -

፩፤ ተመየጥ፡ እስራኤል፡ ኀበ፡ እግዚአብሔር፡ አምላክከ፤

እንዲህ፡ ነውና፡ ይህ፡ ሁሉ፡ ሳይደረግብህ፡ እስራኤል፡ በአ ምልኮት፡ ወደፈጣሪህ፡ ተመለስ፤

ለምንት፡ ትተክሉ፡ ኃጢአተ፡ ወትቀ ሥሙ፡ ፍሬ፡ ሞት፤

ኃጢአት፡ ሠርታችሁ፡ ሞት፡ እንዲታዘዝባችሁ፡ ለምን፡ ትሆ ናላችሁ፤

፪፤ ወንሥኡ፡ ሠናያተ፡ ዘነአስዮ፡ ለእግዚአብሔር፡ ፍሬ፡ ከናፍሪነ፤

ሠናያተ፡ ፍሬ፡ ከናፍሪነ፡ ብለህ፡ ግጠም፤ ከከንፈራችን፡ የሚገኝ፡ ለእግዚአብሔር፡ የምናቀርበው፡ በጎ፡ ምስጋናን፡ አመስግኑ፤

፫፤ ወበሉ፡ አሶርሂ፡ ኢያድኅነነ፤

አርበኛውም፡ አላዳነንም፡ በሉ፤

ወአፍራሰሂ፡ ኢንዔአን፤

በፈረስም፡ ተቀምጠን፡ አናመ ልጥም፡ በሉ፤

ወኢንብሎሙ፡ እንከ፡ አማልክተ፡ ለግ ብረ፡ እደዊነ፤

የእጃችን፡ ሥራ፡ የሚሆኑ፡ ጣዖ ታቱን፡ አምላክ፡ አንላቸውም፡ በሉ፤

፬፤ በእንተ፡ ዝንቱ፡ ይሣሃል፡ ዕጓለ፡ ማውታ፤

ስለዚህ፡ ነገር፡ እናት፡ አባቱ፡ የሞቱበትን፡ ይቅር፡ ይላል፤

ወይፌውሶሙ፡ ለሕሙማኒሆሙ፤

የታመሙትን፡ ያድናቸዋል፤

ወያፈቅሮሙ፡ አሙነ፤

በእውነት፡ ያድናቸዋል፤

ወናሁ፡ እመይጥ፡ መዓትየ፡ እም ኔሆሙ፤

እነሆ፡ መዓቴን፡ መቅሠፍቴን፡ ከነዚያ፡ እመልሳለሁ፤

፭፤ ወእከውኖሙ፡ ከመ፡ ዝናም፡ ለእስራኤል፤

ዝናም፡ ደስ፡ እንዲያሰኝ፡ እስ ራኤልን፡ ደስ፡ አሰኛለሁ፤



ወይሠርፅ፡ ከመ፡ ጽጌ፤

ወያየብስ፡ ምድራ፡ ብሎ፡ ነበ ርና፡ በረድኤት፡ ይለመልማል፤

ወይጸንዕ፡ ሥረዊሁ፡ ከመ፡ ዐርዘ፡ ሊባኖስ፤

ወያየብስ፡ ሥረዊሁ፡ ብሎ፡ ነበ ርና፡ አባትነቱ፡ እንደ፡ ደጋ፡ ዛፍ፡ ይጸናል፤

፮፤ ወይወፍር፡ አዕፁቂሁ፤

ወእሰብር፡ አጽመ፡ ገበዋቲሁ፡ ብሎ፡ ነበርና፡ ልጁ፡ ልጅ፡ ይወልዳል፤

ወይከውን፡ ከመ፡ ዘይት፡ ሥሙር፤

እንዳማረ፡ እንደበጀ፡ ዘይት፡ ይሆናል፤

፯፤ ይትመየጡ፡ ወይነብሩ፡ ታሕተ፡ ጽላሎቱ፡ ወየሐውሩ፤

ወደእግዚአብሔር፡ ተመልሰው፡ በጽላሎተ፡ ረድኤቱ፡ ተጠብ ቀው፡ ይኖራሉ፤

ወይፀግቡ፡ እምሥርናይ፤

ስንዴ፡ በልተዉት፡ ደስ፡ እን ዲያሰኝ፡ መዓዛ፡ ረድኤቱ፡ ደስ፡ ያሰኛል፤

ወይሠርፅ፡ ከመ፡ ወይን፡ ዝክሩ፤

በእግዚአብሔር፡ ዘንድ፡ መታ ሰቡ፡ ወይን፡ ደስ፡ እንዲያሰኝ፡ ደስ፡ ያሰኛል፤

ወከመ፡ ወይነ፡ ሊባኖስ፤

ከወይኑም፡ ዘንድ፡ እንደ፡ ደጋ፡ ወይን፡ ደስ፡ ያሰኛል፤

፰፤ ለኤፍሬም፡ ለምንት፡ እንከ፡ ሎቱ፡ ጣዖት፤

ለኤፍሬም፡ ጣዖት፡ ማምለክ፡ ምኑ፡ ነው፤

ወአነ፡ አጽናዕክዎ፤

እኔ፡ ባደክመው፡ እሱ፡ ካላጸ ናው፡ እኔ፡ ባጸናው፡ እሱ፡ ካላ ደከመው፤

ወአነ፡ አፈርዮ፡ ከመ፡ ወይን፡ ሥሙር፤

እኔ፡ እንዳማረ፡ እንደበጀ፡ ባደ ርገው፡ ማለት፡ እሱ፡ እንዳ ይወልድ፡ ቢያደርገው፡ እኔ፡ እንዲወልድ፡ ካደረግሁት፡ ለኤ ፍሬም፡ ጣዖት፡ ማምለክ፡ ለምኑ፡ ነው፤

ወይትረከብ፡ ፍሬሁ፡ በኀቤየ፤

ልጁ፡ በኔ፡ ዘንድ፡ ይገኛል፤

፱፤ መኑ፡ እንከ፡ ጠቢብ፡ ዘይሌ ልዮ፡ ለዝንቱ፡ ወየአምሮ፤

ይህን፡ የሚያስበው፡ ብልህ፡ ሰው፡ ማነው፤ ይህንስ፡ መር ምሮ፡ የሚያውቅ፡ ብልህ፡ ሰው፡ ማነው፤

እስመ፡ ርቱዓት፡ ፍናዊሁ፡ ለእግዚአ ብሔር፡ ጻድቃን፡ የሐውርዎን፡ ወኃጥ አንስ፡ ይስዕንዎን፤

የእግዚአብሔር፡ ሕግጋቱ፡ የቀኑ፡ ናቸውና፡ ጻድቃን፡ ጸንተውባ ቸው፡ ይኖራሉ፤ ኃጥአን፡ ግን፡ በሕግጋቱ፡ ጸንተው፡ መኖር፡ ይሳናቸዋል፤

ተፈጸመ፡ ዘሆሴዕ፡ በረከተ፡ አምላኩ፡ ትኩን፡ ምስሌነ፡ ለዓለመ ዓለም፤ ወስ ብሐት፡ ለእግዚአብሔር፡

ለእግዚአብሔር፡ ክብር፡ ምስ ጋና፡ ይግባው፡ አሜን፡ በውነት።

www.ethiopianorthodox.org